19

# ትግላችን

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የተዘጋጀ

## የበርሊኑ አለም አቀፍ ጉባኤ

የመፅሄት አዘጋጅ ቦርድ፣
P.O.BOX 3198
103 64 STOCKHOLM 3
SWEDEN

ቁጥር **4**
ሰኔ 1965

## መ ግ ቢ ያ::

በቅርቡ በበርሊን ስለ ተደረገው የአለም አቀፍ ማህበራችን 'ጉባኤ':ከአውሮፓው ማህበር ስራ አስኪያጅ ኮሚቴ አንዳንድ ጽሁፎች ተልከውልን ሁላችንም አይተናቸዋል::እነዚህ ጽሁፎች:-

1ኛ. የስብሰባው ረቂቅ/ሚኒት/

2ኛ. የአውሮፓው ማህበር ስለስብሰባው ያወጣው መግለጫ

ናቸው::

ከስብሰባው ረቂቅ እንደምንረዳው:ጉባኤው <u>የንትርክ</u> ሸንጎ ሆኖ እንደነበረ ግልጽ ነው::በዚህ ስብሰባ ላይ ብዙ ስድቦች ተወርወረዋል::በስድቦቹ መሀከል ወሸመጥ እየገቡ ደግሞ በተማሪ ማህበራት ውስጥ ያሉ ብዙ መሰረታዊ ልዩነቶች እውነተኛ መልካቸውን አሳይተዋል::በስብሰባው ላይ ሆነ ከዚህ በፊት በልዩ ልዩ ባንዲራ ስም ሲወረወሩ 'የከረሙት' ስድቦች የነዚህ መሰረታዊ ልዩነቶች አጧፋሪያች እንጂ ዋናዎቹ የልዩነት መሰረቶች እንዳልሆኑ ግልጽ ሆኗአል::

እንደዚሁም በረቂቁም ላይ ሆነ በመግለጫው ላይ እንደሚታየው በዚሁ ስብሰባ ላይ:-

1ኛ/ ለጊዜው የተማሪዎቹ ማህበራት ሁኔታ የሚደሰማማ ህገ ማህበር 'በመጽደቁ'

2ኛ/ በዚህ ህገማህበር መሰረት ከአባላት ማህበራት በላይ ከፍተኛ ስልጣን ያለው

የአለምአቀፍ ቢሮ በመቋቋሙና ይህም 125ኛው ያውሮፓ ማህበር ጉባኤ ለስራአስኪያጅ ኮሚቴው ከሰጠው ማሳሰቢያ በላይ በመሆኑ

የአውሮፓው ማህበር የስራአስኪያጅ ኮሚቴ፡ህገማህበሩን ከመቀበሉና ቢሮውን ከማወቁ በፊት፡ጉዳዩን ከነህገማህበሩ ለ135ኛው ጉባኤ ማቅረብ እንዳለበት በትክክል አሳስቦ ለጊዜው በተቋቋመው የ'አለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪያች ፌደሬሽን' አባል ከመሆን ተቆጥቧል::

እነዚህን ነገሮች ሁሉ በዝርዝር የሚገልጽ አንድ ጽሁፍ በስብሰባው ላይ ከነበረ ተመልካች ደርሶን፡ይኸው ከዚህ በታች ለአንቦቢያች አቅርበነዋል::

ጽሁፉ የሌላ ውዝግብ መነሻ እንደማይሆን ተስፋ እናደርጋለን::ብዙ ቀዳሚ ተግባሮች በፊታችን ተደቅነው ሳለ የውዝግብ አርእስት እየፈለጉ እንካ–ሰላንታ በማቅረብ ጊዜያችንን ማሳለፍ ትክክል አይመስለንም::

በዚህ አመት የውዝግብ ጽሁፎችን ደጋግመን አውጥተናል::ይህም አንባቢያቻችንን ሳያሰለችና ሳያስገርም እንደማይቀር ይሰማናል::ሆኖም በአሁኑ ጊዜ ሌላ ምንም ምርጫ የለንም::በየአቀጣጫው ልዩ ልዩ ሰበቦች እየተፈለጉና እየተፈጠሩ በአውሮፓው ማህበር ላይ የሀሰት ክሶች ሲዘንባሉ::ክሶቹ ከጀመሩ ይኸው በቀላሉ 2–3 አመታት ማለፋቸው ነው::በነዚህ ጊዜ ውስጥ ሁሉ የአውሮፓው ማህበር በጥሞና ለመወያየትና ለምቀው ትክክለናውን ቴምፐሬቸር ለመስጠት መጣሩን የመጽሄቶቻችን አንባቢያች ሁሉ የሚስቱት አይመስለንም::



አሁን በበርሊኑ በብሰባ ላይ ከተገኙት ከአውሮፓ ማህበር አባሎች አንዱ ከዚህ በታች የምናስፍረውን ጽሁፍ ሲያቀርብ የግድ እስካሁን በተሰነዘሩት የሀሰት ክሶችና ሲደረግ በነበረው የተዛባ ዘመቻ ተገፍቶ መሆኑ ይገባናል::ጽሁፉ ብዙ ጠቃሚ ትምህርቶችን ይዟል::አንዳንዱ የሀሰት ክሶችን ለማቃናት ሞክሯል::ወደፊት በትክክል እንዲሰራ ከተፈለገ መቃናትም አለባቸው::በስብሰባው ላይ የነበረውን ውዝግብ በተብራራ መልክ ለአንባቢያች አቅርቧል::አንባቢዎች ሁሉ ከዚህ ጽሁፍ ጠቃሚ ትምህርትን ለመውሰድ እንደሚችሉ እናምናለን::አጨፋሪ በሆኑ አርእስቶች ላይ የሚደረገ ውዝግብንም ይዘጋል ብለን ተስፋ እናደርጋለን::

ሰኔ 1965

ት ግ ላ ች ን

# የበርሊኑ የአለምአቀፍ ጉባኤ

## ያንዱ ተመልካች አስተያየት

ለብዙ ጊዜ ሲጠበቅ የነበረው የአለምአቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች 'ጉባኤ' በበርሊን ከተማ ከ21 አስከ 28 'ኤፕሪል' ተደረገ::በዚህ ስብሰባ በተሳታፊነትም ሆነ በተመልካችነት የነበሩት የማህበራት አባሎች — በተለይም በተመልካችነት የነበሩት — ትልቅ ትምህርት አንዳገኙ ፈጽሞ አይጠረጠርም::በበኩሌ አስካሁን ድረስ በማህበሮቻችን ውስጥ 'የዚህ አይነቱን' ስብሰባ ፈጽሞ አይቼ አላውቅም::'የዚህ አይነት' ያልኩበትን ምክንያት አንባቢያች ጥቂት ገጾች ወረድ እንዳሉ ሊገነዘቡት እንደሚችሉ ተስፋ አደርጋለሁ::

የስብሰባውን ሁኔታ በዝርዝር ለማስረዳት አንዱ መጽሀፍ መድረስ ያስፈልጋል::ጊዜውና አቅሙ ስለማይፈቅድልኝ:በበኩሌ የስብሰባውን አንዳንድ ጉልህ ሁኔታዎችና ውጤቶች ብቻ ለማቅረብ እፈልጋለሁ::

ስብሰባው የተጀመረው በ21 ኤፕሪል:1973 ጧት ሲሆን:አጀማመሩም ከውሮጳውና ካሜሪካው ማህበራት የቀረቡትን 15 ያጀንዳ ነጥቦች በሶስት ቀን ውስጥ ለመጨረስ ነበር::ምናልባት ከሁሉ አስቀድሞ ስለዚህ አጀንዳ አንዳንድ አስተያየት ማቅረብ ያስፈልጋል::

አጀንዳው በግልጽ የሚያሳየው ለጉባኤው ጥብቅ ዝግጅት አንዳልተደረገ ነው::ከነጥቦቹ ብዙዎቹ ተጠቃለው ባንድነት ሊቀርቡ የሚችሉ ነበሩ::ለምሳሌ ያህል 'አለም

አቶ ፍ የኢት. ተማ. ማ. ድርጅታዊ መለክ"፡"ዋና ዋና
አላማዎች"፡"ህገማህበር"፡"ጠቅላላ ጉባኤ"፡"የገንዘብ
ምንጮች"...፡፡እነዚህ ሁሉ ያጀንዳው ነጥቦች "ህገማህ
በር" በሚለው ስር ሊጠቃለሉ ይችሉ ነበር፡፡በሌላ በኩል
ደግሞ፡ባጀንዳው ውስጥ ያልገቡ /በኋላ በስብሰባው ላይ
የተወመረና ሳይወመሩም የቀሩ/፡አስቀድሞ በጥብቅ ሊታሰብ
ባቸው ይገቡ የነበሩ ነጥቦች ነበሩ፡፡ለምሳሌ "የኢት ዬዶ
ያ ተማሪዎች ማህበራት ጊዜያዊ ሁኔታ"፡"የጸረፊውዳልና
— ጸረኢምፔሪያሊስት የፖለቲካ መስመር ይዘት"፡፡በኋላ
በስብሰባው ላይ እንደታየውና ከዚህ በታች እንደምንመለከ
ተው ሁሉ፡የአጀንዳው ውጥንቅጥነት ራሱ ብዙ ወዝገብ እን
ዲከተል አድርጓል፡፡

ሌላው የጉባኤውን ስራ ያምታታውና ውይይቱን ወገ
ያባጣው ግን በማን ስም ተከታፊ እንደሆነ በገለጸ አለመ
ነገሩ ነው፡፡ስብሰባውን ያውሮፓው ማህበር ሊቀመንበር ከ
ከፈተ በኋላ የጉባኤው ስልጣንም ሆነ ከጉባኤው የሚጠበቀ
ው ውጤት ምን እንደሆነ ተጠይቆ ነበር፡፡አባል ማህበራት
ለመሆን የሚችሉ የትኞቹ ማህበራት ነበሩ? የስብሰባው ስራ
ህገማህበሩን አስናድቶ ለአባል ማህበራት ጉባኤያች ማቅረ
ብ ነበር? ስራአስኪያጅ ኮሚቴ እዚያው መምረጥ ነበር?
በ12ኛው የአውሮፓው ማህበር ጉባኤ ላይ የጸደቀውንና በኋ
ላም በ20ኛው የሰሜን አሜሪካኑ ማህበር ላይ ተቀባይነት
ያገኘውን የበር አቋም ሊለውጥ ይችላል? ለነዚህ ጥያቄዎ
ች በቂና ገለጸ የሆነ መልስ አልተሰጠም፡፡በጉባኤው ላይ
የተገኘ ማንም ሰው አሳብ ለማቅረብና ለመከራከር መብት እ
ንዳለው፡ድምጽ መስጠት ግን የአባላት ማህበራት ወኪሎች



ብቻ መብት እንደነበረ በደፈናው ስምምነት የተደረሰ ይመ
ስል ነበር፡፡ይሁንናም፡ከወኪሎች በስተቀር በስብሰባው ላ
ይ የነበሩት የማህበር አባላት፡የጉባኤውን ዋና ስራ በሚ
መለከተው በኩል፡የአሳብ መስጠት መብታቸውን ጭምር እንደተ
ገፈፉ ከዚህ በታች እናያለን፡፡

ያውሮፓው ማህበር ሊቀመንበር በ21 ጧት ለጉባኤው
የተላኩትን መልእክቶች ካነበበ በኋላ፡በቤቱ ውስጥ የጉባኤ
ው ሊቀመንበር እንዲመረጥ ተደረገ፡፡የዚህም ትርጉም በዚያ
ን ሰአት በስብሰባው ላይ የነበሩት ጓዶች ሁሉ ሙሉ የጉባ
ኤው አባላት መሆናቸው በህግ ሳይሆን በስራ/ደፋክቶ/ ተ
ረጋገጠ ነበር ማለት ነው፡፡

በ21 ጧት ከቤቱ ውስጥ ያንዳንዶች ጓዶች ስም ለሊ
ቀመንበርነት ቀረበ፡፡ከተጠቀሱት ጓዶች ብዙዎቹ ሊቀመንበ
ርነቱን አንቀበልም ስላሉ፡ስሙ በሌስቱ ላይ የቀረው የቤ.
ኔሉኮስ ቀ. ማ. መልእክተኛ ብቻ ሆነ፡፡የርሱን ሊቀመን
በርነት የሚቃወም እንዳለ ተጠይቆ ሲጠፋ፡በቀጥታ የጉባኤው
ሊቀመንበር ሆነ፡፡ቀጥሎም ከቤቱ ውስጥ ሁለት ጸሀፊዎች ተ
መረጡ፡፡

የጉባኤው የመጀመሪያ ድርጊት አጀንዳውን ማሻሻል ነ
በር፡፡በዚህ መሰረት መጀመሪያ ላይ የቀረቡት ነጥቦች 1ኛ/
የአለም አቀፍ ማ. ታሪካዊ አመጣጥ፣2ኛ/የአባል ማህበራ
ት ጊዜያዊ ሁኔታ፡፡እነዚህ ሁለት ነጥቦች በ21 እና በ
22 ኤፕሪል ለተደረጉት ሙሉ ስብሰባዎች መነጋገሪያ አ
ርእስቶች ሆኑ፡፡በነዚህ በሁለት ነጥቦች — በተለይም በሁ
ለተኛው ነጥብ — ላይ የተደረገው ውይይት በቤቱ ሁለት

በአስተያየት የተለያዩ ወገኖች መኖራቸውን ቁልጭ አድርጎ አሳዩ::አንደኛው ወገን ያውሮፓ ማህበርን አስፈጻሚ ኮሚቴ: ቀደም በማህበሩ አመራር ውስጥ የነበሩ አንዳንድ ጓደኞችና የሊባኖስን ወኪል ይይዛል::ሁለተኛው ደግሞ ያሜሪካውን ማህበርና የሴቶችን የጥናት ክበብ ወኪሎች:ለሊቀመንበርነት የተመረጠውን ጓዱና የስዊስን ቅ.ማ. መልእክተኛ ይይዛል:: እዚህ ላይ በደንብ መገንዘብ የሚያስፈልገው ለሁለቱ ወገኖች መታያ ምክንያት የሆኑትን የፖለቲካ አስተያየትና የትንተና ልዩነቶች ነው::ደግሞም እነዚህ ልዩነቶች ከስብሰባውም በፊት የነበሩ መሆናቸውን ማስታወስ ተገቢ ነው:: ይህንን ነጥብ በደንብ ካልተረዳን የጉባኤውን ድርጊቶችና ውጤቶች በሚገባ ለመገንዘብ አይቻልም::

የአባል ማህበራት — ፀበ ሂራዊ ማህበር:ያሜሪካውንና ያውሮፓውን ማህበሮች — ሁኔታ መመልከት:በውስጣቸው የነበሩትን:ያሉትን:ርእዮተአለማዊና ፖለቲካዊ አዝማሚያዎች /ቴንዴሲያች/ ማመዛዘን የግድ አስፈላጊ ነበር::እንደርሱ ካልተደረገ:ለጠቅላላው የኢት. ተማ. እንቅስቃሴ <u>አንዱ</u> የፖለቲካ መስመር:ችሎታውን:አሳማውንና ተገቢሩን በተጨበጠ አኳኋን ለማየትና ለመወሰን እንደማይቻል ግልጽ ነው:: ጉባኤው ይህንን የውይይት አርእስት እንዲቀበለው የተደረገው በዚህ ምክንያት ነው::

## 1. የሁለቱ ወገኖች ያስተያየት ልዩነቶች::

እነዚህ ወገኖች በስብሰባው ላይ በገሀዱ ቢታዩም ከሁለት—ሶስት አመታት ጀምሮ የነበሩ ናቸው::በልዩነቶቹ መሰረት ላይ እንደገና እመለስበታለሁ::አሁን ግን በስብሰባው ላይ የታየውን እንመልከት::



በመጀመሪያ ያገርቤቱ የተማሪዎች ንቅናቄ እንዴት እንደነበረና አሁን ያለበትን ሁኔታ መተንተን ተጀመረ::ያሜሪካውን ወገን አመዛዘን የሚያጠቃልለው ሊቀመንበር የሆነው:የቤኔሉሱ ጓዱ:ስላገርቤቱ የሰጠው ሰፊ ማብራሪያና መደምደሚያ ነው::ከታህሳሱ አልቴት በፊት የነበረውን ያገርቤት ተማሪዎችን እንቅስቃሴና ጥንካሬ ይህ ጓዱ በሰፊው ከገለጸ በኋላ 'ከመንግስቱ ጋር በአይዲዮሎጂና በፖለቲካ /ረገድ/ ይደረግ የነበረው ትግል/ልክ/ በሁለት መንግስታት መሀከል ይደረግ የነበረ የፖለቲካ ትግል አስመስሎት ነበር' በማለት ደመደመ::/ቃለጉባኤ ገጽ 4/ሌሎችም ያሜሪካኑ ወገን ጓደች በየተራቸው እንደዚሁ ያገርቤቱን እንቅስቃሴ ትልቅነትና ጠንካራነት በማሞገስ አስተያየት ሰጡ::በጠቅላላው ከነዚህ ጓደች የቀረቡት 'ሚዛኖች' የንቅስቃሴውን አንዱ ወገን ብቻ — በቁራጥነት:በጀግንነት: በድፍረት ስርአቱን መቋቋሙን:አይን የሚስቡ/ስፔክታኩላር/ ድርጊቶችን ብቻ — አጋነነው:ደካማ ጎኖቹን ሳይጠቅሱ:ጉድለቶቹን ሳያሳዩ ሊያልፉ ይፈልጉ እንደነበረ ግልጽ ሆነ::

ያውሮፓው ወገን:ያገርቤቱ እንቅስቃሴ ትልቅ መስዋእቶችን ማድረጉን ፈጽሞ አይክድም::እንዲያውም ያገርቤቱ እንቅስቃሴ ማገናውንም እርምጃ በወሰደ ቁጥር ያውሮፓና ያሜሪካ ማህበራት ያላንዳች ማመንታት በሙሉ ልብ ይደግፉት እንደነበረ የነዚህ ማህበራት ታሪክ እንደሚያሳዩ አስታወሰ::ይሁን እንጂ:በተለይ ከ1969ኙ አልቴት ትንሽ ቀደም ብሎና ከዚያም በኋላ:እንቅስቃሴውን "ግራ ቀደምነት" እንዳጠቃው መገንዘብ ተገቢ መሆኑን አሳሰበ::በተለይም ከተማሪው ውስጥ ከፍተኛ የፖለቲካ ንቃት አላቸው ተብለው የተገመ

ቶት ጓደቸ፡ስርአቱ ባጭር ጊዜ ውስጥ ሊገለበጥ ይችላል በለው በማመን የጦርነት ስልት ለመማር ካሁኑ ወደውጭ አገር መሰደዳቸው የዚህ 'ገራ ቀደምነት' ምልክት መሆኑን ገለጸ፡፡በተረፈም በየጊዜው ባገርቤቱ ማህበር የተወሰዱት እርምጃዎች በዚህ'ገራ ቀደምነት' የተበከሉ ለመሆናቸው ምንም ጥርጥር የለውም የሚል አስተያየት አቀረበ፡፡

ይህንን አስተያየት ያሚሪካው ወገን ጓደቸ በሃይል መቃወም ጀመሩ፡፡በጽሁፍ የታዩ ማስረጃዎችን ጠየቁ፡፡ክርክሩን በማጠመም 'መሬት ላራሹ'፡'ትምህርት ለሁሉ' የሚሉት ስሉጋኖች 'ገራ ቀደም'ና ቸው ወይ ብሉ ይከራከር ጀመር፡፡በመጨረሻም፡የሴቶቹ ማህበር ወኪል፡አሁን የአ.አ.ማ. ፕሬዚዳንት የሆነቸው ጓዲት፡'እናንተ እዚህ ተቀምጣችሁ ባገርቤቱ ላይ ሂስ ለማቀረብ ምንም መብት የላችሁም' በማለት በቁጣ ክርክሩን ባጭሩ ለመቁጨት ሞከረች፡፡ሚዛን ለማውጣት ያህል ሲደረግ የነበረው ውይይት በሴቶቹ ወኪል አመኻኘነት ወደመብት ጥያቄ ተለወጠ፡፡ከዚያ ወዲያ አንዳችም ዲሞክራሲያዊ ክርክር ሊደረግ አልቻለም፡፡

ከሁሉ የሚያስገርመው ያሚሪካው ማህበር ወኪሎች አቋም ነበር፡፡ቀደም ብሉ፡ የዛሬን አያድርገውና፡እነርሱ እራሳቸው ባገርቤቱ እንቅስቃሴ ላይ ያቀርቡ የነበረው ሂስ ይህንን 'ገራ ቀደም' የሚለውን አስተያየት የሚያጸድቅ እንጂ የሚያስተባብል አልነበረም፡፡ለማመስል ያህል፡—

በNEWSLETTER,Vol. I, No. 2, Dec. 1970 ገጽ 9-10 እራሱ በተምታታና በገራ ቀደምነት በተጠቃ ርእስአንቀጽ ውስጥ በለአገርቤቱ እንቅስቃሴ የሚከተለውን አስፍረው ነበር፡፡



"Although it was clearly recognised that only revolutionary violence can overthrow the yokes of feudo-fascism and imperialism, there was not serious organisation with a political programme based on a scientific analysis of the objective conditions in Ethiopia. Whatever organisation existed it responded only to the immediate necessity of leading the struggle through a particular episode and confrontaion. It is precisely because of its essentially spontaneous disorderly infantile nature that the movement remained exposed and defenseless during the three months propaganda just before the December massacre." /ስርዝ የተጨመረ/፡፡

እንደዚሁም Struggle, vol. 1, No. 4, June 1971 በበኩሉ እንዲህ ይላል፡፡

"... the Ethiopian student movement holds dangerous illusions in this regard( ie. regarding the role of the proletariat); failing to scientifically analyse the particular and peculiar conditions of the Ethiopian society that have temporarily thrown up the student movement into the vanguard of the urban political movement, the student movement has mistaken its transitional role of avanguard for one that is "permanent". Objectively the ESM has tried to "usurp" the role of the Proletariat!"/ስርዝ የተጨመረ/፡፡

ያሚሪካኑ ማህበር ወኪሎች በ1970-71 ስለአገር

ቤቱ የተማሪ ንቅናቄ የነበራቸው ግምትና ሚዛን ከዚህ በላ ይ እንደተጠቀሰው ነበር::በበርሊኑ ስብሰባ ላይ ከዚህ አ ቋም አሽግሽገዋል::በዚህ ስብሰባ ላይ ቀኝ ኋላ ዞረው ያገርቤትን ተማሪዎች እንቅስቃሴ ከአንድ መንግስት ሃይል ጋር እስከማስተካከል ደርሰዋል::በስብሰባው ላይ ደጋግመው እንዳሉት ከሆነ የነርሱን <u>የመጨረሻ አቋም</u> የሚገልጸው አሁ ን የወጣው:"ኮምባት" የሚባለው ጽሁፍ ነው::በ"ኮምባት" ላይ ወደፊት ለመመለስ ይቻላል::ይሁን እንጂ "ኮምባት" ውስጥ ያለውንም ለሚመጣው አመት <u>አያስተባበሉትም</u> ብሎ ለማ መን አስቸጋሪ ነው::

ወደጉባኤው ስራ ለመመለስ:የብሄራዊውን እንቅስቃሴ: ያሜሪካውንና ያውሮፓውን ማህበራት አቅጣጫዎች ለመመርመር የተደረገው ሙከራ ያገለገለው ላንዱ ነገር ብቻ ሆነ::ይ ህውም ያሜሪካው ወገን ያውሮፓውን ማህበር ለማሳጣት:ለመ ንቀፍና ያለአግባብ ለመክሰስ ያቀደውን ከስራ ላይ ለማዋል ነበር::ባውሮፓው ማህበር ውስጥ ዲሞክራሲ የለም ተባለ:: በ12ኛው የማህበሩ ጉባኤ ላይ መሪዎች የተመረጡት በመደ ለት/በኢንትሪግ/ ከጉባኤው ውጭ ነው ተባለ::በዚህ አመቱ <u>ትግላችን</u> ቁጥር1 ውስጥ "ማህበሩ የሚመራበት መርህ ማ እከላዊ ዲሞክራሲ መሆን አለበት" የሚል ሰላ:አመራሩ ማህበሩን እንደፓርቲ ይወስደዋል፣"ጸረኢምፔሪያሊዝም-ጸረ ፊወዳሊዝም ምን ማለት እንደሆነ አልገባውም":"ግራ ቀደም ነት አለበት" ተባለ::ትንሽ ቆይቶም:ያውሮፓው ማህበር "መስመር መቀልበስን"/ሪቪየሽን/:"የቀኝ አፖርቹኒዝምን" "ጭራነትን"/ቴይሊዝም/:"ተሸናፊነትን"/ዲፊቲዝም/ የሚ ሳስሉ ፖለቲካ በሽታዎች አሉበት ተባለ::ያሜሪካው ማህበ



ር ወገን ላውሮፓው ማህበር የደረደራቸው ቅጽሎች እርስበ ርስ የሚቃረኑ መሆናቸውን እንኳን ለመገንዘብ ፋታ አልነ በረውም::ዋናው ነገር በሆነውና ባልሆነው ያውሮፓውን ማህ በር መሪዎችና ደጋፊዎች ማዋከብ ሆኖ ተገኘ::

በ21 እና በ22 ኤፕሪል የተደረጉት "ውይይቶች" በጠቅላላው ስብሰባ ላይ ሊረባ የማይችል ምልክት ጥለው ሄደዋል::ስብሰባው ፈጽሞ ተመርዞ ነበር::ያሜሪካው ማህ በር:የሴቶች ማህበርና የስዊሱ ቅርንጫፍ ማህበር ወኪል: እንደዚሁም አንዳንድ የቅርንጫፍ ማህበራት አባሎች ሀሜቱ ን መሰረት በማድረግ:በሀሰት ያውሮፓን ማህበር የፖለቲካ መስመር ለማሳጣት ሞከሩ::ሌላው ቀርቶ:ባለፈው 12ኛ ያው ሮፓ ማህበር ጉባኤ ላይ የነበሩትን ሁኔታዎች በሀሰትና በሀሜት አጣምሞ ለማቅረብ ሞከረ::ባ12ኛው ጉባኤ ስራ በሙሉ ተሳትፎ የነበረቸው:አሁን የሴቶች ወኪል ሁና ወደ ስብሰባው በመምጣት ለአለም አቀፉ ፕሬዚዳንት የተመረጠች ው ጓዲት:በደፈናው አይኗን ጨፍና "ባለፈው ጉባኤ ላይ ካሜሪካን የመጣን ወኪሎች ድምጽ እንዳንሰጥ ተከለከልን" አለች::በስብሰባው ላይ የነበሩ ጓዶች ሁሉ እንደሚያስታ ውሱት ለ<u>ሲቢ ነአግ</u> የተሰጠውን ድጋፍ በሚመለከተው በኩል የመጽሄት ቦርዱን ራፖር የሚቃወም እንቅስቃሴ:ያውም ካን ዱ የመጽሄት ቦርድ አባል:ቀርቦ በማያሻማ ብልጫ ተሸነፈ:: ከዚያ ራፖሩ ለድምጽ ቀርቦ የማያወላውል ብልጫ አገኘ:: በበርሊኑ የአለምአቀፍ ጉባኤ ላይ:ያውሮፓ ማህበር መሪዎች የመጽሄት ቦርዱ ራፖር ለድምጽ ብልጫ እንዳይቀርብ አደረ ጉ 'የሚል ፍጹም አይን-አውጣ ውሸት ተነገረ::እነዚህና ሌ ሎችም በአውሮፓው ማህበር አመራር ላይ በሀሰት ተመርተው

ይሰራዉ የነበሩት ሀሜቶች በጉባኤው ላይ በግልጽ በከስ መ
ሰከ ቀረቡ::ከዚያ ወዲያ የቀጠሉትን የጉባኤ ስራዎች በ
ሚገባ ለመረዳትና በደንብ ለመከታተል የተዘረዘሩትን ያስ
ተያየት ገጭቶች፡የነበረውን ‘የታወከ’ አካባቢ ሁልጊዜ
ማስታወስ ያስፈልጋል::

## 2. የ23 ኤፕሪል አዲስ አጀንዳና ስምምነቶች፣

በ23 ኤፕሪል ጧት፡ስብሰባው በዚህ አኳኋን ወደፊ
ት ለመገፋትና የበፊቱን አጀንዳ ሊያከናውን የማይችል መ
ሆኑ ግልጽ ስለሆነ፡የአባል ማህበራት ወኪሎች ተሰብስበው
አዲስ አጀንዳ ለቤቱ እንዲያቀርቡ ተጠየቀ::በዚህ መሰረት
የአምስት አባል ማህበራት ወኪሎች ስምምነት የተገኘበት አ
ጀንዳ በ23 ኤፕሪል ከሰአት በኋላ ለጠቅላላው ስብሰባ
ቀረበ::አምስት የሆኑበት ያልጀሪያው ወኪል የዚያኑለት
ጧት ደርሶ ስለነበር ነው::አውሮፓ፡አሜሪካ፡ሴቶች፡ሊባኖ
ስ፡አልጀሪያ/::የወኪሎቹ ስምምነት ለቤቱ ሲነበብ፡ሁለት
ነጥቦች በማያሻማ አኳኋን ቀረቡ::

አንደኛው የስምምነት ነጥብ አባልነትንና ውክልናን
የሚመለከት ነበር::ለጊዜው ስምንት ማህበራት የአለምአቀፍ
ማህበር አባላት እንዲሆኑ::እነዚህም ብሄራዊ ማህበር፡የ
ውሮፓ ማህበር፡የሜሪካ ማህበር፡የሴቶች የጥናት ክበብ፡የ
ሊባኖስ፡የግብጽ፡ያልጀሪያ፡የሱዳን ማህበራት ናቸው::ያሁኑ
ን ጉባኤ በሚመለከተው በኩል፡ብሄራዊው ማህበር አልተወከለ
ም::ሱዳንን አልጀሪያ፡ግብጽን ሊባኖስ ይወክላሉ::ወደፊት
ግን ሁለቱም — ግብጽና ሱዳን — ራሳቸውን ችለው ይገ
ባሉ::



ሁለተኛው የስምምነት ነጥብ አዲሱ አጀንዳ ነበር::
ይህም የሚከተሉትን ነጥቦች ይይዛል::

1. የአለምአቀፍ ማህበር አላማና ተግባሮች
2. ስለድርጅታዊ መልኩ
3. ህገማህበር/ይህም በሌሎች አርእስቶች ተከፋፍሎ
4. በአ.አ.ማ. መሀከል ለሚኖሩት ቅራኔዎች
   የአ፡አ.ማ. የሚኖረው ስልጣን
5. ስለተመላሽ ተማሪዎች መደራጀት
6. ጊዜያዊ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ሁኔታ
7. የጽህፈትቤቱ ምርጫ

7ኛው ነጥብ በህገማህበሩ ውስጥ የሚወሰን ስለሆነ
ለጊዜው ወደጎን ይተዋል ተባለ::የተረፉትን ስድስት ነጥብ
ች ቤቱ መቀበሉን አስታወቀ::በሌላ በኩል ግን ስለድምጽ
አሰጣጥ ወኪሎች የወሰኑት ነገር እንዳለ ተጠየቀ::ወኪሎቹ
በዚህ ነጥብ ላይ እንዳልተነጋገሩበት ሲገልጹ ከቤቱ ውስ
ጥ ልዩ ልዩ አሳቦች ቀረቡ::እነዚህ ነጥቦች በውሳኔ የ
ሚያልፉት በቀላል ድምጽ ብልጫ፡በሙሉ ድምጽ/በዩናኒሚቲ/፡
በሁለት—ሶስተኛ፡በአራት—አምስተኛ፡እንዲሁም ያለድምጽ ‘በ
ስምምነት’ ብቻ ይሁን የሚሉ ልዩ ልዩ አሳቦች ቀረቡ::በመ
ጨረሻ ወኪሎቹ እራሳቸው እንደገና ተመካክረው የደረሱበት
ን ውሳኔ ለቤቱ እንዲያቀርቡ ተጠየቀ::በዚህ አኳኋን የተ
ባሉት ወኪሎች ለጥቂት ጊዜ ከተሰበሰቡ በኋላ፡ያጀንዳው
የመጀመሪያ አራት ነጥቦች በአራት—አምስተኛ ድምጽ፡የቀሩት
ሁለቱ በቀላል ድምጽ ብልጫ እንዲወሰኑ መስማማታቸውን፡እን
ዲያውም ሙሉ ድምጽ/ዩናኒሚቲ/ እንዲኖር የሚጣጣሩ መሆናቸ
ውን አስታወቁ::/ይህንን ውሳኔ በደንብ ማስታወስ ያስፈል

ጋል::ከዚህ በታች እንደምናየው፡ያሜሪካኑ ወገን ያጭበረበ
ረበት እንዱ ነጥብ ይህ ነውና::/

እንገዲህ ለማጠቃለል ያህል::በ23 ኤፕሪል ከስአት
በኋላ ቤቱ የተስማማባቸው ሶስት ነጥቦች ነበሩ ማለት ነው::

ሀ/ ለዚህ ጉባኤ በአባልነት የሚቀጠሩት ስምንት ማ
ህበራት ናቸው::ከነዚህ ውስጥ ብሄራዊው ማህበ
ር አልተወከለም::ግብጽንና ሱዳንን ሊባኖስና
አልጀሪያ ይወክሏቸዋል::/ይህ ውክልና ምን ማ
ለት እንደሆነ አልተብራራም::/

ለ/ የጉባኤው አጀንዳ እላይ የተጠቀሱት ስድስቱ ነ
ጥቦች ይሆናሉ::

ሐ/ ከነዚህ ነጥቦች ውስጥ መጀመሪያ አራቱ በ4/5
ድምጽ ይወሰናሉ::የቀሩት ሁለቱ በቀላል ድምጽ
ብልጫ::

እንዱ ሌላ የኮነሰርአት ውሳኔ ነበር::ግን እርሱን
ከማየታችን በፊት እዚህ ላይ ስለአባልነትና ስለድምጽ አሰ
ጣጡ ጉዳይ አንዳንዱ ነገሮችን ማብራራት ያሻል::

ባውሮፓው ማህበር 12ኛ ጉባኤና በአሜሪካው ማህበር
20ኛው ጉባኤ ላይ — በመጀመሪያው ቦታ በሙሉ በጭብጨባ፡
በሁለተኛው ደግሞ 'በወንፈሉ' እንደዚሁ በጭብጨባ — ጉባኤ
ያቹ የተቀበሉት አንዱ ወረቀትና የሱዳን ማህበር ያቀረበው
አንዱ ሌላ ጽሁፍ ለዚሁ ጉባኤ ቀርበው ነበር::እነዚህ ጽ
ሁፎች ስለአባልነትና ድምጽ አሰጣጥ የሚያቀርቧቸው
አሳቦች ያልተጣሩ ነበሩ::ሁለቱ ወረቀቶች የሚሉትን እንመ
ለከት::



'ለአለም አቀፍ ድርጅት ህገማህበር የቀረቡ ማሻሻያ
ሀሳቦች' በሚለው ከሱዳን ማህበር በቀረበው ወረቀት ውስጥ

ሀ/ አባልነት

1. የአለምአቀፍ ድርጅት ህገማህበር አላማን የተ
ቀበሉና በቻፕተር/የቀበሌ ማህበር/ የተደራጁ
ኢትዮጵያን ተማሪዎች የአለም አቀፍ ድርጅት
አባሎች ናቸው::

2. የአ.አ. ድርጅትን ሁለት አይነት ማህበሮች
/ቻፕተሮች/ ይመሰርታሉ::

— የቀበሌ ማህበር/ሎካል ቻፕተር/

— የአህጉር ማህበር

የቀበሌ ማህበር ማለት በማንኛውም ቦታ የአ.አ. ድ
ርጅትን ህገማህበር በማይቃረን አላማ የተመሰረቱና የሚመሰ
ረቱ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራት እያንዳንዳቸው የቀበሌ
ማህበራት ይሰናሉ::ለምሳሌ ያህል በልዩ ልዩ የአውሮፓ
አገሮች የሚገኙ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራት::በልዩ ልዩ
የአሜሪካ ስቴቶች የሚገኙ ማህበራት፡በአልጀሪያ፡በግብጽ፡
በሱዳን፡በሊቢያ፡በሊባኖስ የሚገኙ ማህበራት፡የሴቶች 'ማ
ህበር':እያንዳንዳቸው የቀበሌ ማህበር ናቸው::

የአህጉር ማህበር/ሪጅናል ቻፕተር/ በአንዱ አካባቢ
የሚገኙ የቀበሌ ማህበራት ባንድነት የሚመሰርቱት ማህበር
የአህጉር ማህበር ይሰናል::ለምሳሌ ያህል በሰሜን አሜሪካ
የኢት. ተማ. ማ.:በአውሮፓ የኢት.ተማ.ማ. የአህጉር ማ
ህበራት ናቸው::

3. በአለምአቀፍ ድርጅት ውስጥ 4 የአህጉር ማህበራት ይኖራሉ፡፡
   - የኢትዮጵያ ብሄራዊ ማህበር
   - የሰሜን አሜሪካ ተማ. ማ.
   - የአውሮፓ ተማ. ማ.
   - የሰሜን አፍሪካና መካከለኛው ምስራቅ ተማ.ማ.
4. የአለምአቀፍ የመጨረሻ ዝቅተኛ አካል የቀበሌ ማህበር ነው፡፡'

በተራ ቁጥር 3 የተጠቀሰው በ1 እና 2፡እንደዚሁም በ4 የተጠቀሱትን እንደሚቃረን ግልጽ ነው፡፡1፡2 እና 4 እንደዚሁ በደፈናው — በቲዎሪ — 'አባል' ለመሆን የሚችሉ ማህበራት አነማን እንደሆኑ ያወራሉ፡፡ለዚያውም ውዥንብር አለባቸው፡፡ ቁጥር 3 ግን አሁን ባለው ሁኔታ አነማን አባሎች እንደሚሆኑ ይወስናል፡፡በነገራችን ላይ በቁጥር 3 የሴቶች ጥናት ክበብ ተረስቷል፡፡ከሁለቱ መንገዶች አንዱን መምረጥ ያስፈልግ ነበር፡፡ወይ 'የቀበሌ' የተባሉትን — ያውሮፓውን ቀ. ማህበራትና ያሜሪካውን ቻፕተሮች ጨምሮ — ሙሉ አባላት ማድረግ፡ወይንም 'የአህጉር' የተባሉትን፡በስተኛው ቁጥር እንደተመለከተው፤አባላት አድርጎ መውሰድ፡፡ ግን የነገር መምታታት ነበርና ይህም ባሁኑ ጉባኤ ላይ የሰጠው ውጤት ታይቶአል፡፡እንደአልጀሪያ ያለው ያምስት ወይም የስድስት ጓዶች ማህበር ግልጽ ባልሆነ ሁናቴ ከአውሮፓው ማህበር አባልነት ወጥቶ/ እስከ 12ኛው ጉባኤ ድረስ፡



ቢያንስ ቢያንስ፡የአውሮፓው ማህበር ቅርንጫፍ ነበር// የአለም አቀፍ ቅርንጫፍ ሆኖአል፡፡'እንደሴቶች የጥናት ቡድን' ያለ ገና በደንብ ለራሱ ያልተቋቋመ አካልም እንደዚሁ 'አባል' ሆኖአል፡፡ወደፊትም፡በዚህ ሁኔታ ለምሳሌ ስዊስ ወይንም ቤኔሉክስ ካውሮፓው ማህበር ወጥተው በቀጥታ የአለም አቀፉ ማህበር አባል የማይሆኑበት ምክንያት ያለ አይመስለም

'3. የድምጽ አሰጣጥ

የቀበሌ ማህበርና የአህጉር ማህበር ወኪሎች በጉባኤው ውስጥ የሚኖራቸው ድምጽ በማህበረተኞቻቸው ብዛት ይወሰናል፡፡

ለምሳሌ ያህል ለአምስት የቀበሌ ማህበርተኞች አንድ ድምጽ ቢሰጣቸው፤20 ማህበርተኞች ያሉት የቀበሌ ማህበር በጉባኤው ላይ 4 ድምጽ ይኖረዋል፡፡አንድ የአህጉር ማህበር 'ቀ'፡'በ'፡'ተ' የቀበሌ ማህበራት የኖሩት እንደሆነና የ'ቀ'ማህበር 50፡የ'በ' ማህበር 30፡የ'ተ' ማህበር 10 አባሎች የኖሯቸው እንደሆነ የአህጉሩ ማህበር በአ.አ. ጉባኤ ላይ የሚኖረው ድምጽ 18 ይሆናል፡፡

በበርሊኑ ጉባኤ ላይ የአባል ማህበራት ወኪሎች ተብለው ስለድምጽ አሰጣጥ የወሰኑት ጓዶች በዚህ ወረቀት ላይ ተነጋግረውበት እንደሁ አላውቅም፡፡ለማንኛውም ጉባኤው — ሙሉ ስብሰባው — አልተነጋገረበትም፡፡በመጨረሻ ተወስኖ የተባለው፡የነበሩት ወኪሎች — አውሮፓ፡አሜሪካ፡ሊባኖስ፡አልጀሪያ፡ሴቶች — እኩል ድምጽ፡ማለት አንዳንድ ድምጽ እንዲኖራቸውና ያሉ አጀንዳ የመጀመሪያ 4 ነጥቦች በ4/5 ድምጽ እንዲጸድቁ ነበር፡፡

ስለአባልነት ከመዘጋታችን በፊት፡ሁለተኛው ወረቀት — 'አለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር' የሚለው፡በ125ኛው የአውሮፓው ማህበር ጉባኤ ላይ ጸድቆ ያውሮፓው የስራ አስኪያጅ ኮሚቴ ለበርሊኑ ስብሰባ ያቀረበው — ስለዚሁ የሚለውን እንይ::

'አዳዲስ ማህበራት' በሚል አርእስት ስር፡ የሚቀጥለው ሰፍሮአል::

1/ የአለም አቀፍ የኢትዮጵያ ሴቶች የጥናት ክበብ ባቀረበው ጥያቄ መሰረት በአለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማ. ማ. አባል እንዲሆን ያውሮፓው ማህበር ይደግፋል::

2/ በሊባኖስ፡በግብጽ፡በሱዳን፡በሊቢያ፡ባልጀሪያ፡ ያሉት የኢትዮጵያ ተማ. ማህበራትና ሌሎችም ወደፊት የሚደራጁ በአካባቢው የሚገኙ የኢት. ተማ. ማ. አንድ ጠቅላላ ማህበር አቋቁመው የአለም አቀፍ አባል እንዲሆኑ ያሳስባል::

3/ ይህ እስኪሆን ድረስ ጥያቄውን ያቀረበው በሊባኖስ የኢት. ተማ. ማ. የአለም አቀፍ አባል እንዲሆን ይደግፋል::

ይህ አባባል እላይ ከተጠቀሰው ወረቀት ቁጥር 3 ጋር የሚስማማ ግልጽ አባባል ነው::ይሁን እንጂ፡በዚህም ላይ ጉባኤው አልተነጋገረበትም::የተነጋገሩትና ውሳኔ ያደረጉት የአምስት አባል ማህበራት ወኪሎች ብቻ ነበሩ::ጉዳዩ ተለቅና ዲሞክራሲያዊ አሰራርን የሚመለከት ሆኖ ባለ፡ለሙሉ



ስብሰባው እንዳይቀርብ የተደረገበት ምክንያት ፈጽሞ ግልጽ አልነበረም::

ወደ23 ኤፕሪል አጀንዳ እንመለስ::እንደተባለው፡ አጀንዳውን ተቀበለው::ከዚያ ውስጥ ስድስተኛው ነጥብ ተመርጦ ወዲያው በሙሉ ስብሰባው ውይይት ተደረገበት::በዚህም ውይይት ላይ የሁለቱ ወገኖች የተለያዩ አቋሞች እንደገና ቁልጭ ብለው ወጡ::ጊዜና ቦታ ስለሚያንስ በይዘቱ ላይ አልመለስበትም::በጠቅላላው የአውሮፓው ወገን በኢትዮጵያ ያለው ነባራዊ/አብጀክቲቭ/ ሁኔታ ለሪቮሉሽናዊ ስራ የተመቸ ነው::ህሊናዊ/ሰብጀክቲቭ/ ሁኔታው ግን እጅግ በጣም ወደኋላ የቀረ ነው::በኢትዮጵያ ዙሪያ ያለው ሁኔታም በጥንቃቄ መታየት አለበት የሚል አቋም ወሰደአል::ያሜሪካው ወገን፡በመጀመሪያው ነጥብ ላይ ይስማማል::ሁለተኛው ነጥብ/ሰብጀክቲቭ ሁኔታ የሚለው/ መነሳት የለበትም ይላል::ሶስተኛው ነጥብ ግን 'በጣም የተመቼ/'ኤክሰለንት'/ ሁኔታ ነው ይላል::... በዚህ የሁኔታ ትንተና ላይ ወደፊት መመለስ ያስፈልጋል::

እዚህ ላይ ማስታወስ የሚያስፈልገው፡ስለስነስርአት ተደርጉ የነበረውን — እላይ ከተጠቀሱት ሶስት ስምምነቶች ጋር የሚሄደውን — ውሳኔ ነው::ስድስተኛው የውይይት ነጥብ እንደተዘጋ፡ጉባኤው በሁለት ኮሚሲዮኖች ይከፈል ተባለ::የመጀመሪያው ኮሚሲዮን ያጀንዳውን 3ኛ ነጥብ — ህገማህበሩን — የሚያዘጋጅ፡የወኪሎች ኮሚሲዮን::ሁለተኛው ኮሚሲዮን ደግሞ በመቀደም መልክ 1ኛውን ነጥብ የሚያዘጋጅ::ሁለቱ ኮሚሲዮኖች የስራቸውን ውጤት ለሙሉ ስብሰባው ያቀርቡና ጠቅላላ ጉባኤው ተነጋግሮባቸው፡እንደተባለው ወኪሎቹ ስበሰ

ባው ላይ ድምጽ ይሰጡበታል:: የድምጹም አሰጣጥ 4/5 ይሆ
ናል::ይህንን ተከትለና ዲሞክራሲያዊ ውሳኔ ቤቱ ተቀብሎት
የኮሚሲዮኖቹ ስራ ተጀመረ::ይሁን እንጂ:ከዚህ በታች እን
ደምናየው ይህም ፈጽሞ እንዳይሰራበት ተደርጓል::

## 3. 24 ኤፕሪል — የጉልበተኞች ክርክር

በመሰረቱ ጉባኤው በ24 ኤፕሪል ማለቅ ነበረበት::
ነገር ግን:በዚህ ቀን:ህገማህበሩን የሚያዘጋጀው የወኪሎች
ኮሚሲዮን:ስራ ገና በደንብ መጀመሩ ነበር:: የመቀደም ኮሚ
ሲዮን ስራውን በ23 ማታ ጨረሰ::በዚህ ሁኔታ:በ24 ኤፕ
ሪል ቧት:ከወኪሎቹ በስተቀር የቀረው ሰው ሁሉ ስራ አልነ
በረውም::በወኪሎቹ ክርክር ለመሳተፍ ቃል የጠየቁት አንዳ
ንዱ ጓዶች:'የለም:ይህ የኮሚሲዮን ስራ ነው' ተብለው ተ
ከለከሉ::በለዚህም:በገዱ ተመልካቾች:ታዛቢያች ሆነው ቀጥ
አሉ::

በመካከሉ በዚሁለት የሱዳን ወኪል ተብሉ አንድ ጓዶ
መጥተ ነበር::ይህ ጓዶ ለስብሰባው የደረሰው አገረመንገዱ
ን ነው::አይጠበቅም ነበር::አሁንም ወደሱዳን አይመለስም::
<u>ለትምህርት</u> አውሮፓ መቀረቱ ነው::እንግዲህ በ24 ማታ
'ክርክሩ' ይካሄድ የነበረው ባንድ በኩል ባውሮፓው ማህበ
ር ወኪሎችና በሊባኖስ ወኪል፣በሌላ በኩል ደግሞ ባሜሪካ:
በሴቶች:ባልጀሪያና በሱዳን መካከል ነበር::የነበረውን አ
ካባቢ ለማሳየት ያህል በመጠኑ ክርክሩን አጠቅሳለሁ::
በ24 ኤፕሪል ቀኑን በሙሉ:በኮሚሲዮኑ ውስጥ:ስለሚፈጠረው
የአለም አቀፍ ማህበር አካልና ስልጣን ክርክር ሲደረግ ው
ሏል::ያልጀሪያው ወኪል ባቀረበው 'ጠንካራ አመራር' መፍ



ጠር አሳብ አውሮፓና ሊባኖስ አልተስማሙም::የተቀሩት ወኪ
ሎች — አሜሪካ:ሴቶች:ሱዳን — በደንብ ደገፈውታል::በደ
ፈናው 'ጠንካራ አመራር' ሲባል ቀዩ እንጂ በወረቀት ተጽ
ፍ የቀረበ ንድፍ አልነበረም::ሁኔታው ፈጽሞ ለመስማማት
የማይቻልበት ሆነ::በዚህ ሁኔታ:ያውሮፓው ማህበር ወኪሎች
የኢትዮጵያ ተማሪዎች ጊዜያዊ ሁኔታ እንደዚህ ያለውን ጠን
ካራ አመራር ለማቋቋም የማይፈቅድ መሆኑን:ባሁኑ ጊዜ 'ጠን
ካራ አመራር' ለመፍጠር አስቸጋሪ መሆኑን በመግለጽ በዚህ
ሀሳብ እንደማይስማሙ አመለከቱ::ክርክሩ እንደሚከተለው ይ
ቀጥላል::ይህንን ቃለጉባኤ ከኦፊሲየል ቃለጉባኤ ጋር ለማ
መሳሰል ይቻላል::ተከራካሪዎች ካውሮፓ ሁለት:ካሜሪካ ሁለ
ት:ከሴቶች ሁለት:ካልጀሪያ:ከሱዳንና ከሊባኖስ አንዳንዱ
ና ቸው::

አልጀሪያ: ጸረፊውዳል–ጸረኢምፔሪያሊስት በተባለው መ
ሰረት ላይ ስምምነት አለን::ይህ ከሆነ
አሁን 'ሊደርሽን' የማንፈጥርበት ምንም
ምክንያት አለ::ለዚህ እያንዳንዱ 'ጊሊጊሸ
ን' መልስ እንዲሰጠኝና መልሱ 'ሪከርዱ'
እንዲሆን እፈልጋለሁ::

አውሮፓ 1: አመራር አይፈጠር አላልንም:: የምንለው የ
ዚህ አይነቱን ጠንካራ አመራር ለማቋቋም
'አስቸጋሪ ነው' ነው::

ሱዳን: ይህ ከሆነ ይህ ስብሰባ ምንም ትርጉም የለውም::
በዚህ ላይ የምትቆሙ ከሆነ እና የተሰበሰብንበት
ምክንያት አይታየኝም::

አውርጂ 2: የመሰባቸንን 'ፍራግሜንት' በቃል ሰጥተናል::በተረፈ በጽሁፍ መልስ እንሰጣለን::

ሱዳን: 'አውቶራይዝድ' ስልሆነ:ም የምትሉት የአለም አቀፍን 'ፍርም' ለመወሰን ብቻ ነው ትላላችሁወይ?

አውርጂ 2: ጉዳዩን መልሰን ለጉባኤያችን እና ቀርባለን ነው የምንለው::

አውርጂ 1: /ባውርጂው ማህበር ጉባኤ ላይ በጭብጨባ ያለፈውን ውሳኔ ያነባል::ውሳኔው የሚለው 'አስፈጻሚው ኮሚቴ የሚያስፈልጉትን እርምጃዎች ይወስዳል' ነው:

አለጀሪያ: በ'አንቲፊውዳሊስት–አንቲኢምፔሪያሊስት' መሰረታችን ላይ 'ሊደርሸፕ' ለመፍጠር እንችለም ነው ያላችሁት::

ሴቶች 1: 'አለምአቀፍ የራሱ ጽህፈት ቤት ያስፈልገዋል' ይላል ውሳኔው::

አሜሪካ 1:I have a right to comment. Systematically the spirit of good will sabotaged ሆኗል:: yestrday unprecedented የሆነ እርምጃ ወስዳችሁ::... ይህ የራሴ 'ኦፒኒየን' ነው::ግን ይህ it is a clear sabotage.

ሴቶች 2: ማድረግም ካስፈለገ ማደር እንችላለን: 'ዲስከሽኑ' መቀጠል አለበት:

አለጀሪያ: /ተመልሶ ገብቶ/ I acuse ያውርጂውን



ማህበር ኮሚቴ::በጉባኤው የተሰጠውን ሀላፊነት አፍርሷል::እኔ እንዲያውም 'አስፈጻሚ ኮሚቴ' የሚለውን ውሳኔ አላየሁትም ነበር:: ያውርጂው ማህበር ጉባኤ 'አስፈጻሚ ኮሚቴ' እንዲቋቋም ስልጣን ሰጥቶአቸዋል::/አሜሪካ 1 – ዝቅባለ ድምጽ – 'ይህ ጭቃራስ ነው/ በማጭበርበርም በውሸትም ቀኑን በሙሉ ሲያስረን ውለዋል::

አሜሪካ 1: 'ስቴትሜንት' አለኝ ...

አሜሪካ 2: ከንግዲህ አንድ 'ኦፊሸያል ሪኮርድ' የሚያደርግ ሰው ያስፈልገናል::

አለጀሪያ: /ያውርጂውን ውሳኔ አነበበ/ 'ማንዴትድ' ሆናችኋል::...

አሜሪካ 1: 'ስቴትሜንት' አለኝ::ሪኮርድዱ እንዲሀ ንልኝ::'ኢ ቬሪ ኢምፖርታንት ስቴትሜንት'

አለጀሪያ: /አቋርጦ/ የ'ኢንዲቪጁዋል ስቴትሜንት' አንቀበልም::የ'ዴሊጌሽን' ብቻ ነው

ከእንግሊዝ: 'ሪኮርድ የሚያደርግ ሰው ከፈለጋችሁ ይኸው' ይልና የፈረንሳይን መልእክተኛ ያቀርባል:: 'ያለበለዚያም እራሳችሁ ሪኮርድ አድርጉ' ይላል::

አሜሪካ 1: It should be understood that we are engaged in a great spirit to form this organisation. I do not believe that Ethiopia needs people

who intrigue and collide. It needs
honest people.What I have seen
here is a serious sabotage - a
dishonest means. This is done by
Europe's deligation and people of
Lebanon. This is my personal
opinion.... I did whatever could
be done - to do good for our
young.... To tell you the truth
I am heart-broken ....It is incu-
mbent on every deligation to say
what happened. /ይልና ከሰቡ እንባው
ን እያፈሰሰ ያለቅሳል/

አለጀሪያ: ውሸት ባይቀር ጨምረው ተናገረዋል::ይህ ለ
ከ መለስ እያሌው ስላንዳችሁ ያለው አይነት
'ባይዛንቲን ፖሊቲክስ' ነው::

ሱዳን: /ለሊቀመንበሩ/ Instead of understanding
and leading,you let loose discussions
... vote እናድርግ ስንል ለምን አላቀረብከም

አለጀሪያ: የራስወርቅ ካንተ ጋር እንነጋገር

አውርጂ 2: ለስደብ ከሆነ ይቀርብኝ::/ረዘም ያለ ጸ
ጥታ/

ከዚህ በኋላ የስዊሱ መልእክተኛ 'ጌዱ አበበና ስሎ
ሞን እንዳረዳችሁ ስለጠየቁኝ ለረዳችሁ ዝግጁ ነኝ' ይልና:
የሚያወም ተጠይቀ ሲጠፋ:ሊቀመንበር ነቶን ይወስዳል::

የንገሊዞ መልእክተኛ በግሉ - ከኮሚሲዮኑ ውጭ የሆ
ነ ሰው - 'ስቴትሜንት' ያደርጋል::"... We are going
to hold you responsible for this action. The
kinds of arguments you are making - each and
everyone of you will be responsible. I assure
you, I'll hold each of you responsible.



አውርጂ 2 ለጥቂት ጊዜ ይወጣል::

አለጀሪያ: 'ስቴትሜንት' እሰጣለሁ::አውርጂ 2 ባለበ
ትና ስብሰባው ከተጀመረ በኋላ::/አውርጂ
2 ይመለሳል/ ያውርጂው ማህበር 'ዲሊገሽን'
በውሸት አጭበርበሯል ብየ ነበር::ይህ ወቀ
ሳየ ሁኔታውን ሳላውቅ ያቀረብሁት ነው::አ
ዝናለሁ::'ዊዝድሮው' አደርጋለሁ::ይህንን
ያደረግሁት 'ጽሀፈትቤት' የሚለውና 'ሰራአ
ስፈጻሚ ኮሚቴ' የሚለው አንድ መሆናቸውን
ባለማወቄ ነው::አሁን ተረዳሁ::ይሁንና ይ
ህን ወረቀት 'ድራፍት' ያደረጉት ተባስተዋ
ል::/ማለት:በውርጂና ባሜሪካ ጉባኤያቸ ላ
ይ የጸደቀትን ወረቀቶች/

ቤቶች 1: ያን ጊዜ 'ዲስከስ' ስናደርግ 'በላከቦርዱ'
ላይ የተሰራው 'ፒክቸር ሴክሬታሪያት' ያሳ
ያል/ትልና ደፍተሯን ከፍ አድርጋ ለሁሉም
ለማሳየት ትሞክራለች/

አለጀሪያ: ይህም ከሆነ 'ስቴል' 'ሴክሬታሪያት' የሚ
ለውን 'አንደርስታንድ' ያደርጋል::'ድራፍት'
ያደረጉት ተሳስተዋል::እነርሱ የሚሉት ጽህ
ፈት ቤት በመሆኑ:

ሊባኖስ: እንገዲያው በዚህ 'ሴክሬታሪያት' በሚለው መ
ንፈስ እንስማማ::

አለጀሪያ: የለም እንደሱ ከሆነ "errneous" ነው::

ሊቀመንበር: እዲስ ስለሆንኩ ነገሩን አላውቅምና ይብበ
ራራልኝ::

የንገሊዝ: አበበ ነበርና ሊቀመንበር እርሱ ይናገር

አውሮፓ 1: አልጀሪያ በለአመራሩ ያቀረበው አሳብ ነበ
ር::አል ተስማማንበትም::

አልጀሪያ: ያቀረብሁት ጥያቄ 'ጸረፊውዳሊዝምና ጸረኢም
ፔሪያሊዝም በሚለው መሰረት ላይ ስምምነት
አለን::በዚህ መሰረት ላይ በታማኝነት የሚ
ሰራ "ሊደርሸፕ" የማንፈጥርበት ምን ምክን
ያት አለ' የሚል ነው::'አፊሸያሊ' እያን
ዳንዱ የሚሰጠው መልስ 'ሪኮርዱ' ይሁንል
ኝ::/ወኪሎቹ መልሳቸውን እንዱ ባንዱ መስ
ጠት ጀመሩ::/

ሊቀመንበር: ከሴቶች እንጀምር::

ሴት 2: ምንም ምክንያት የለም::

አሜሪካ 2: የኢትዮጵያን ተማሪዎች ማህበራት በከፍተኛ
ደረጃ ለመምራት:ከውጭ ማህበራትና መንግስ
ታት ጋር ግንኙነት የሚያደርግ:ባገርቤት
ካሉት የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት
ለማድረግ የሚችል ... Federation of
Ethiopian Students ለማቋቋም የምን
ችል ይመስለናል::በ'እንቲ-ፊውዳል -እን
ቲ-ኢምፔሪያሊስት' መሰረት ላይ ስምምነት
አለ::እርግጥ ያይዲዮሎጂ ልዩነቶች አሉ::
ግን ይህ አይከፋፍለም::አሁን ድርጅቱ ሊ
ቋቋም ካልቻለ:ሀላፊነቱ ያውሮፓው ማህበር
ሀላፊዎቹ ይመስለናል::ይህንን የምለበት



ሀሳባችንን ለማቀራረብ ብዙ 'ሰጀስቸንስ':
'አሜንድሜንትስ' ቀርበዋል::በነርሱ በኩል
on the contrary ብዙ contradictory
arguments አይተናል::በጠቅላላው የሰጡት
'ኢምፔረሽን' በ12ኛው ጉባኤ ላይ ከተሰጠው
ሌላ ምንም አናለፍም የሚል ነው::'ኢሌጋል'
የሆኑ ምክንያቶች አቅርበዋል::...

አውሮፓ 2: 1ኛ/ የማህበሩን ተግባሮች — እነርሱም በ
ውሳኔው ላይ የተጠቀሱ ናቸው — በመገመት
2ኛ/ ዋናው ጸረፊውዳል-ጸረኢምፔሪያሊስት
አቋማችን አንድ ቢሆንም አንዳንድ ትንንሽ
ልዩነቶች መኖራቸውን በመገመት
3ኛ/ የጂኦግራፊ አቀማመጣችንን:ያለንን
ጉልበት በመገመት
የአባል ማህበራትን ስራ ከማቀነባበር:ከ
ኢትዮጵያና ከውጭ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት
ን ከማድረግ በላይ ስልጣን ያለው:የጠነከ
ረ:ከማህበሮች ጠቅላላ ጉባኤዎች በላይ የ
ሆነ መሪ አቋም እንዲፈጠር ተጠየቀ::ይህ
የማህበራችንን መብት ስለሚነካ:የጉባኤን
ስልጣን ስለሚደመስስ:እንደዚሁም ጉባኤዎች
ን ለኛ ከሰጠን ስልጣን በላይ በመሆኑ:የ
ማህበራችንን ውሳኔ መንፈስ ሸረን ከዚያ
ውጭ የሆነ ድርጅት አንፈጥርም::

አልጀሪያ: ያውሮፓ ጓዶች 'ኢሲዩ' የሚያደርጉት ነገ
ር አለ::ስለዚህ በጥያቄ ላይ 'አፒንዮንስ'

ሆኖ የሚጠመር አለኝ::/ሊቀመንበሩ የተ[illegible] ውን 'አፔንዲክስ' አልጀሪያ እንዲያዘጋጅ ይፈቀዱለትና እርሱ እስኪጸፍ ደረስ ጸጥታ ይደረጋል::/

/ያልጄሪያ 'አፔንዲክስ የሚለው፣ ድርጅቶችን ና መንግስታትን ለመገናኘት መብት ያለው የአለምአቀፉ አመራር ብቻ መሆኑን፡ የዚህን ግንኙነት ፖሊሲ የሚያወጣው ይኸው አመራር ብቻ መሆኑንና አመራሩ ስልጣኑን አንዳንዴ እንዳስፈለገ ለአባል ማህበራት በውክልና እንደሚያስተላልፍ የሚገልጽ ነው::/

አውሮፓ 2: ይህንን ያመራር ጉዳይ አልጀሪያ ቀደም አቅርቦታል::ተወያይተንበታል::አልጀሪያም የአባል ማህበሮችን sovereignty limit እንደሚያደርግ ደጋግሞ ተናግሯል::በና 'አንደርስታንዲንግ' የዚህ አይነቱን 'ሊሚቴሽን' የሚያመጣ፡ የጠነከረ አቋም አያስፈልግም::እንግዲህ እኛም ለ'አፔንዲክሱ' መልስ መስጠት ይኖርብናል::በኋላ ቃል ይሰጠን::

ሊቀመንበር: እዚህ አንድ ጥያቄ ቀረበልኝ::ሰዎቹ መለሱልኝ::እናንተ ዘንድ ደረሰኩ::'አመራር' ለሚለው ያውሮፓው ማህበር መልስ 'ፖዚቲቭ' ወይስ 'ኔጌቲቭ'::

አውሮፓ 2: ቀራኒያቸ በሳለበት አሳቡን እንቃወማለን::



ሱዳን: 'ሊደርሽኝ' የማንፈጥርበት ምንም ምክንያት የለም::እንዲያውም በካርቱም ያለው ማህበር አስፈላጊነቱን በጽሁፍ አቅርቧል::በአለምአቀፍ ደረጃ በጠነከረ አመራር ላይ የተመሰረተ ድርጅት መፍጠር ለትግላችን አዲስ ምእራፍ ይከፍታል:: ነገር ግን በዚህ ስብሰባ ላይ እንደተገነዘብኩት ከሆነ ያለው 'ስፒሪት' በጣም ዝቅተኛ ነው:: ብዙ 'አብስትረክሽን' ይታያሉ::'አኝንማይገ ዱዱኔስ' የለም::

ሊባኖስ: እኔ መጀመሪያውኑ ይህንን ያመራር 'ኮንሰንት' ተቃውሚአለሁ....

ሊቀመንበር: /አቋርጦት/ ጥያቄው አሁን እዚህ የቀረበልኝ ነው::'አመራር' የሚለው ተገልጿል::

አልጀሪያ: 'አመራር' የሚለው እዚህ ላይ በ'አፔንዲክስ' ተገልጿል::

ሊቀመንበር: /እንደገና ያልጄሪያውን ጥያቄ ያነባል::/ ይህንን ጥያቄ ከፈለግህ 'ኔጌቲቭሊ' ለመመለስ ትቻላለህ::ግን ጥያቄውን ለመመለስ አትቸልም::/ይለዋል ለሊባኖስ/

አልጀሪያ: 'ኢንፎርሜሽን'፣'አመራር' የሚለው ከዚህ እኔ በ'ፉትኖት' ካቀረብሁት ሌላ አይደለም::

አውሮፓ 2: ጥያቄ ተጠይቀን መልስ ሰጥተናል::አልጀሪያ ስለአመራር በ'ፉትኖት' ገባል ብሏል:: እኛም ለዚህ 'ፉትኖት' መልስ እለን ብለ

ን አስታውቀን ነበር::

ሊቀመንበር: እናንተ ባትናገሩ በፊት ነበር 'ፊትኖቱን' አልጀሪያ የጀመረው:

/እዚህ ላይ ተመልካቾች ጭምር 'የለም' ብለው በመጮህ ይቃወማሉ::ነገሩን ጸሀፊው እንዲያጣራ ይጠየቅና የተባለው 'ፊትኖት' ያውሮፓው ማህበር ወኪል ለመጀመሪያው ጥያቄ መልስ ከሰጠ በኋላ የተጨመረ መሆኑን ያረጋግጣል::በዚህ ጊዜ አውሮፓ 2 'ተገሸ ጊዜ ይሰጠንና ለ'ፊትኖት' መልሳቸንን 'ፍርሙሌት' እናደርጋለን ይላል::/

ቤቶች 1: የለም::አሁኑኑ መናገር አለብህ/ትለዋለች አውሮፓ 2ን/

አልጀሪያ: ከሰአት በኋላ በሙሉ ስለአመራሩ ያለኝን አስተያየት ስገልጽ ውያለሁ::አሁን በ'ፊትኖት' ላይ እንዴት እንደምተጣላ አልገባኝም::

/ከዚህ በኋላ:ሊቀመንበሩ ቃሉ ተቋርጦበት ወደነበረው ወደሊባኖስ ይመለሳል::/

ሊባኖስ: በመሰረቱ 'አንቲ-ፊውዳል - አንቲ-ኢምፔሪያሊስት' በሚለው ላይ ከተስማማን አመራር የምንመሰርትበት ምክንያት የለም::ግን አማካይ አመራር:አማካይ ስራአስኪያጅ ከሚቴ ለመፍጠር ድርጅታዊ አንድነትን ይጠይቃል::የራሳቸው ህገማህበር:የራሳቸው መጽሄቶች:የራሳቸው አመራር ያላቸው:በጅአገራዊ የተለያዩ ማህበራት አሉ::



እነዚህን ባንድ ጠንካራ ስራአስኪያጅ አካል ስር ማድረግ አስቸጋሪ ነው::ለምሳሌ:'ጸረፊውዳልና ጸረኢምፔሪያሊዝም' የሚለውን በልዩ ልዩ ለመተርጎም የሚቻልበት ሁኔታ ዛሬ አለ::እያንዳንዱ ማህበር የራሱን ውሳኔዎች ለማሳለፍ ይቸላል::ይህም የአለምአቀፍን አቋም ሊያፈልስ ይቸላል::ባሁኑ ጊዜ በተነሱት ጥያቄዎች ላይ :ወደፊት በሚነሱት ላይ እያንዳንዱ ጉባኤ መለያየትን ሊያመጣ ይቸላል::...
ስለዚህ የማቀርበው አሳብ:የአባል ማህበራትን ስራ የሚያቀራርብና በጉባኤዎች ውሳኔ መሰረት ግንኙነት የሚፈጥር ጽ/ቤት እንዲቋቋም ነው::
/እዚህ ከተጻፈው ረዘም አድርጎ ነበር የገለጸው::/

ሊቀመንበር: ስለዚህ ለጥያቄው መልስህ 'ኔጌቲቭ' ነው ማለት ነው::

ሊባኖስ: አይደለም::እኔ የማቀርበው አይነት አመራር ይለያል ማለት ነው::

/ከንግሊዝ ወኪል በቤኔሉክስ ወኪል አማካይነት አንድ ማስታወሻ ለሊቀመንበሩ ይተላለፋል::/

ሊቀመንበር፡ /ማስታወሻውን ካነበበ በኋላ/ እናንተን ነው የምንጠብቀው/ይላል ለአውሮፓ/

አውሮፓ 2: ጊዜ ይሰጠን::'ፍርሙሌት' እስትናደርግ ሌላ 'ዲስከሽን' ይቀጥል::

ቤቶች 1: አሁኑኑ 'ስቴትሜንት' ካልሰጡ በኋላ እንዳይሰጡ ይከለከሉ::

አሜሪካ 1: መልሱ 'አፊሽያሊ' በአለምአቀፍ ወረቀት እንዲገለበጥ እጠይቃለሁ::እዚሁ ተባዝቶ ለሁሉም ይሰጥ::

አውሮጳ 2: ባጭሩ:አልጀሪያ የድርጅቱ አቋም ምን መልክ እንደሚኖረው ያቀረበውን አሳብ በዝርዝርና በአትኩሮት ስንመለከተው:ስንወያይበት የቀየነው የድርጅቱ አመራር በአባላት ማህበራት ላይ የሚኖረውን ስልጣን ይገልጻል:: ይህም ከማህበራችን ውሳኔ ጋር የሚቃረን የአለም አቀፍ የድርጅት አቅድ ነው::ይህ አሁን ያልሁት ቀደም ከሰጠሁት ፊት ይገባ::

ሱዳን: ጥያቄ::'ስንወያይበት የቀየነው' የሚለው የትኛው ነው:

አውሮጳ 2: እዚህ ስንወያይበት የቀየነው ነው::

ሱዳን: ታኒያ ተከከለኛ መልስ ሰጥ ተሀል::

ሊቀመንበር: /በድንገት/ የቀረበው ጥያቄ በ2/3 ድምጽ ተደገፍአል::ስለዚህ አልፍአል ማለት ነው::

ሊባኖስ: እቃወማለሁ::አመራር የሚለው...

ሊቀመንበር: /እቋርጦ/ ስለዚህ ያንተ መልስ 'ፖዚቲቭ' ነው::/ወደአልጀሪያ ዞሮ/ ለድምጽ ታቀርባለህ ወይስ አታቀርብም::

አልጀሪያ: 'አመራር' የሚለውን እኔ ባልሁት መንገድ ጓዶቸ ተረድተውት እንደሆነ መጀመሪያ ይጠየቁልኝ::ጓድ ሊባኖስ አመራር የሚለውን ተቀ



ብሎ 'ፖዚቲቭ' የሆነ 'አሚንድሚንት' የሚያቀርብ ከሆነ ይጠየቀልኝ::

ሊባኖስ: አመራር ምን ማለት እንደሆነ ተነምከንያቱ 'ኳሊፋይ' አድርጌ አቀርባለሁ::

ሊቀመንበር: ከዚህ ለመውጨ አንተ/ሊባኖስ/ 'አሚንድሚንት' ካመጣህ ... ያለዚያ አንተ/አልጀሪያ/ ድምጽ እንዲሰጥበት ከጠየቅህ...

አልጀሪያ: 'ፎርማሊ' በ'ሞሽን' መልክ ላቀርበው::

አውሮጳ 1: ከ'ሞሽን' በፊት ስለድምጽ አሰጣጡ ውይይት እናድርግ::/ትንሽ ከጮሁበት በኋላ/ ሳበራራ::2/3 ድምጽ አሁን 'ፕሮፖርሽናል ዴሞክራቲክ' አይደለም::/እንደገና ይጮሁበታል/ የሚቻል ከሆነ በሙሉ ድምጽ በናባልፍ ይሻላል::ያለበለዚያ ሌላ 'ዴሞክራቲክ' የሆነ አሰጣጥ ይፈለግ::/ሱዳን ይጮህበታል::/

አውሮጳ 2: በትናንት ሁኔታ ላይ ስምምነት ነበረን:: በዛሬው ሁኔታ ስምምነት የለንም::ዛሬ አዲስ ሁኔታ ተፈጥሮአል::/እንግሊዝ 'ሸት' እያለ ተቆጥቶ ይወጣል/ አሁን እንግዲህ ባለው ሁኔታ 'ሚድል ኢስት' ሰስት ድምጾቸ ይኖሩታል::በዚህ ላይ የሴቶቸ አለ:: ይህ ሁኔታ የአባላትን ቁጥር into account አይወስድም::

ያሜሪካው ወገን ጓደች ¨ 'ሳቦቴጅ'
ከዚህ በኋላ ""ኢንትሪግ' አድርጋ
ታደርጋላችሁ¨:"ውሸታሞች ናችሁ¨:ያሉ በሁለቱ ጓደች ላይ ይወርዱባ
ቸኋል¨ ...ወዘተ. እያሉ በሁለቱ ጓደች ላይ ይወርዱባ
ቸቀሉ::በዚህ አኳኋን የድምጽ አሰጣጥ ነገር እንደገና ሳ
ይነሳ ታለፈ::

ይህንን 'የክርክሩን' ክፍል በሰፊው የጠቀስሁት የ
ክርክሩ ዘዴ ምን አይነት እንደነበረ ላንባቢው ትንሽ ስእ
ል ይሰጣል በማለት ነው::ከዚህ ክርክር አንዳንድ ለማንም
በግልጽ የሚታዩ ሁኔታዎችን ለመገንዘብ ይቻላል::

አንደኛ/ ያልደረሰው ጓድ ጥያቄ በይዘቱም ሆነ ባቀ
ራረቡ ያውሮፓውን ወኪሎች ለማስፈራራት ብቻ የቀረበ ነው::
የአለምአቀፍ ማህበር 'አመራር' ፈጽሞ አይፈጠር ያለ ሰው
አልነበረም::ያውሮፓው ማህበር ወኪሎችና የሊባኖሱ ወኪል
ያሉት:የሚፈጠረው 'አመራር' ጽ/ቤት ሆኖ:ተግባሮቹ የአባ
ል ማህበራትን ስራ ማቀናበርና ከውጭ ድርጅቶች ጋር ግንኙ
ነት በመፍጠር:የተሰደዱትን ተማሪዎች ጉዳይ በመከታተልና
ፓስፖርት የሚገኝበትን ዘዴ በመፈለግ የተወሰነ:ባጭሩ:የግ
ል ማህበራትን የሚያቀናብር እንጂ ከነርሱ በላይ ሆኖ 'የ
ግንኙነት ፖሊሲ የሚያወጣ:አባል ማህበራትን የሚቆጣጠር'
አካል እንዳይፈጠር ነው::በዚህ ሁኔታ ጽ/ቤት ይቋም ከሚ
ለው ስምምነት ላይ ደርሶ:የዚህን ጽ/ቤት ተግባሮች መዘር
ዘር ይበቃ ነበር::ያውሮፓውን ማህበርና የሊባኖስን ግልጽ
አስተሳሰብ አጣምሞ 'ሊደርሽን የማንፈጥርበት ምክንያት አ
ለወይ'ብሎ መጠየቅ ጓደችን 'እንዳችም አካል እንዳይፈጠር
ትፈልጋላችሁ' ብሎ:ባላሉት:በባዶ ቦታ:መከሰስ ነው::ለ
ማንኛውም:ወኪሎቹ በሙሉ ድምጽ 'ምንም ምክንያት የለም'



ብለው በመለሱም ኖሮ እንኳን:የተባለው አካል ቅርጽ:ተግባ
ርና ስልጣን እንደገና ለውይይት መቅረቡ ፈጽሞ የማይቀር
ነገር ነበር::ደግሞም በኋላ እንደዚሁ ተደርጓል::

ሁለተኛ/ ሊቀመንበሩ — የስዊስ ቅርንጫፍ ማህበር
መልእክተኛ — ህገወጥ በሆነ መንገድ ከመስራቱም በላይ ያ
ውሮፓውን ማህበርና የሊባኖስን ወኪሎች በማዉናገፍ ለመጨቀ
ን ሞክሯል::

አንድ ጊዜ ያልደረሰው ጓድ ጥያቄውን ካሰፈረ በኋላ
ና የሴቶች ወኪል:ያሜሪካ ወኪል:ያውሮፓ ወኪል መልስ ከሰ
ጡበት በኋላ:ባለጥያቄው ጓድ የ'አፔንዲክስ' ጉዳይ ሲያመ
ጣ:ሊቀመንበሩ ይህንን መፍቀድ አይገባውም ነበር::መፍቀዱ
ስህተተኛ መሆኑን ስለተገነዘበው ስህተቱን ለመሸፈን 'ፋት
ኖት የተጨመረው እናንተ ባትናገሩ በፊት ነው' ብሎ ያውሮ
ፓውን ማህበር ወኪሎች አይን ባይን ለማጭበርበር መሞከሩ
ፍጹም አስጠያፊ ድርጊት ነው::

ሁሉም ወኪሎች በተባለው ጥያቄ ላይ መልስ ከሰጡ በ
ኋላ:ሊቀመንበሩ በገዛ ፈቃዱ:ድምጽ ያልተሰጠበትን:አንቀስ
ቃሴ ያልሆነ:በመዝገብ ብቻ እንዲሰፍር የተጠየቀውን:ያልደ
ረሰውን ጓድ ጥያቄ:'በ2/3 ድምጽ ተደገፍአል::አልፍአል'
ብሎ ማወጁ ህገወጥ ብቻ ሳይሆን:ትርጉም የሌለው:የሊቀመን
በሩን <u>ቸኩል ስሜት</u> ብቻ የሚያባብስ <u>አቋም</u> ነበር::እንደገና
ስህተት ማድረጉን ስለተገነዘበ:ጓዱ ተመልሶ አልደረሰያን
'ለድምጽ ታቀርባለህ ወይስ አታቀርብም' የመጀመሪያውን ስ
ህተት ለመሸፈን መሞከሩ አሁንም አስጠያፊ ድርጊት ነው::
በተጨማሪ ይሄው ሊቀመንበር በግልጽ ያውሮፓንና የሊባኖስን

ወኪሎች ቃል እያቋረጠ:እየተቀጣ:'ነው' ወይም 'አይደለም' የሚል መልስ ብቻ እንዲሰጡ ያጣድፋቸው ነበር::ይህም ፈጽሞ <u>ከዲሞክራሲያዊ</u> የጉባኤ አመራር የራቀ አሰራር ነበር:: የዲሞክራሲ ነገር ከተነሳ::በጠቅላላው የበርሊኑ ስብሰባ ጓዶች የዲሞክራሲን ባንዲራ ለይስሙላ ጥላ በማድረግ ዲሞክራሲን የረገጡበት:ዲሞክራሲን ያፈዙበት ስብሰባ ነበር::

ስድስተኛ/ በ23ቱ ኤፕሪል ስምምነት መሰረት:በኮሚሲዮኑ ስራ ላይ ድምጽ መስጠት ሊኖር አይችልም ነበር::ከዚህ በላይ እንደሚታየው የተባለውን ጥያቄ ያልጀሪያው ጓድ በእንቅስቃሴ መስክ እንዲያቀርብ የገፋፋው ሊቀመንበሩ ነው:: ይህም ፈጽሞ ህገወጥ ነበር::ህገወጥነቱን ሊቀመንበሩም:አልጀሪያም የባቱት አይመስለኝም::ምናልባት የ23ቱን ስምምነት ማንም አያስታውሰውም የሚል እምነት ኖሮባቸው ሊሆን ይችላል::ጉባኤው ህጋዊና ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ የሚካሄድ ቢሆን ኖሮ:የዚህን ትልቅ ውሳኔ መኖር ለኮሚሲዮኑ አባሎች ማስታወቅና በደንቡ/በስምምነቱ/ መሰረት እንዲሰራ ማድረግ ከሁሉ አስቀድሞ የሊቀመንበሩ:በተለይም ለጠቅላላ ጉባኤ የተመረጠው ሊቀመንበር:የቤኔሉክሱ መልክተኛ: ግዴታ ነበር::

አራተኛ/ ሊቀመንበሩ 2/3 የሚለውን የድምጽ ብልጫ መጥቀሱ ፈጽሞ ህገወጥ ነበር::ከዚህ በላይ እንዳየነው በ4/5 ድምጽ ያልፋል የሚል ስምምነት ነበር::ያውሮፓው ማህበር ጓዶች የድምጽ አሰጣጡን ጥያቄ እንደገና ሲያነሱ 'አጭበርባሪዎች':ውሸታሞች' እየተባሉ 'ቀንድ ቀንዳቸውን የተባሉት' የተደረገው ስምምነት ከስራ ላይ እንዳይውል ለማገድ ብቻ ነበር::ያሜሪካው ወገን ጓዶች በኋላ ምክንያት ቢሰጡ '4/5 የሚለውን የተስማማንበት አምስት ወኪሎች ስለነበሩና ያምስት ድምጾች 2/3 አራት ስለሆነ ነው::ስለዚህም መጀመሪያውኑ የተስማማነው በ2/3 ድምጽ ነበር::' እያሉ በአራት—መደብ ሂሳብ አጭበርብረዋል::ማንም እንደሚያውቀው የአምስት 2/3 <u>ሶስት</u> እንጂ <u>አራት</u> አይደለም::በርግጥ በ2/3 የድምጽ አሰጣጥ ስምምነት ተደርጎ ቢሆን ኖሮ 4/5 ማለት ባላስፈለገም ነበር::ይህ የማጭበርበር ስራ ከሪቮሉሽናዊያን የአሰራር ዘዴ የራቀ አሳፋሪ ድርጊት ነው::

አምስተኛ/ በጠቅላላው ከሴቶች የጥናት ቡድን — በተለይም አሁን ኘሬዚዳንት ከሆነቸው ጓዲት:ካሜሪካው ማህበር:ካልጀሪያና ከሱዳን:ከሊቀመንበሩና ካንዳንድ የኮሚሲዮኑ አባሎች ካልሆኑ ጓዶች:በተሸፋፈነ ድምጽም ሆነ በግልጽ የተሰነዘሩት ስድቦችና ቁጣዎች: የተወረወሩት ተሳልቆ ቃላት — 'ሳቦታጅ:አብስትረክሽን:ኢንተሪግ'...ወዘተ. — ያውሮፓውን ወኪሎች 'ቀንድ ቀንድ ለማለት':'ጭቃ ለማስኘት' የታቀዱ:ፈጽሞ ከዲሞክራሲያዊ አሰራር የራቀ <u>የጉልበተኛ</u> 'የክርክር' ቴክኒኮች ነበሩ::

ያሜሪካው ማህበር 'ኤክስኩቲቭ ካውንስል'/አሁን ሴንትራል ኮሚቴ ተብሏል/ በነሀሴ 1972 Handbook on Elementary notes on Revolution and Organisation የሚል ጽሁፍ አሳትሟል::ይህ ከሌላ መጽሀፍ የተገለበጠ: "the highest achievement of the year in the whole Ethiopian Student Movement" /የጽሁፉ ርእስ አንቀጽ/ የተባለ ጽሁፍ:ከተማሪ ማህበር የሚጠበቅ አይደለም::ብቻ ይህንን ለጊዜው እንተወውና:በዚህ ጽሁፍ ውስጥ እንደዚህ የሚል አለ::

"... a revolutionary morality - like
all his stands - is of a class nature,
ie. based on a class analysis. Thus
it does not mean that a revolutionary
will not missinform, trick and expro-
priate the enemies of the peoples.
In such cases he is acting(lying,
cheating, expropriating,indulging in
flattery of the enemy in certain cases)
in the interest of the organisation.
and the labouring masses"(page 32)

ይህ አነጋገር በራሱ፡በቦታውና በሁኔታው — ማለት የተባለው በርግጥ ባንድ ሪቮሉሽናዊ ድርጅት ውስጥ በሪቮሉሽናዊ ድርጊት ተሰማርቶ በሚገኙበት ጊዜ ከሆነ — እውነትና ተገቢ መሆኑ አይካድም፡፡ይሁን እንጂ፡በበርሊኑ ስብሰባ ላይ፡በነሱው አሳሳቢነትና ሰብሳቢነት አንድ 'አመራር' ለመፍጠር በተገኙበት ስብሰባ ላይ ያውርጃው ጓዶች <u>እንደጠላት ተወስደው</u>፡ይህ ዘዴ ከስራ ላይ ውሎአል ቢባል ከሀቅ የራቀ አይሆንም፡፡አይን-ባይን ማጭበርበር፡መዋሸት፡መደለል፡ነገርን ማምታታት፡ማዋከብ፡ሌሎችም ቴክኒኮች ከስራ ላይ ሲውሉ ታይተዋል፡፡ይህም ከሪቮሉሽናዊ ግብረገብነት አሰራር የራቀ፡የጉልበተኛ አሰራር እንደነበረ ገለጽ ነው፡፡

በተማሪ ማህበራችን ውስጥ <u>የዚህ አይነቱ አሰራር እ</u>ንዳይደገም መታገል የያንዳንዱ አባል ፈንታና ተግባር ነው ብየ አምናለሁ፡;

## <u>4. የልዩነቶች ስረመሰረት</u>

ባንጻ ወገን የተፈለገው ጠንካራ 'አመራር' እንዲፈጠር፡ከዚህ በላይ በተመለከተው ዘዴ ጥርጊያ ጉዳናው፡አሰፈላ



ጊው የመዋከቢያ፡የመወናበጃ አካባቢ/አትሞስፌር/ ከተዘጋጀ በኋላ፡ኮሚሲዩኑ ስራውን ቀጥሎ በ27 ኤፕሪል ንጋት ላይ ህገማህበሩ በአራት ድምጾች ደጋፊነት/አሜሪካ፡ሲቶች፡አልጀሪያ፡ሱዳን/፡በሁለት ድምጾች ተቃዋሚነት/አውርጃ፡ሊባኖስ/ 'ጸደቀ'፡፡ይህ እንደሆነ ወደአለምአቀፍ አመራር ምርጫ ሊታለፍ ሲባል፡ከቤት ውስጥ ከተመልካቾቹ አንዱ ጓዱ የ23ቱን ኤፕሪል ስምምነት ለሊቀመንበሩ አስታወሰ፡፡በዚያ ስምምነት መሰረት አለመሰራቱ በመዝገብ እንዲሰፍርለት ጠየቀ፡፡በዚህ ጊዜ የኮሚሲዩኑ ሊቀመንበር፡የስዊሱ ቀ.ማ. መልእክተኛ፡ 'አሁንም ቢሆን ጊዜ አለ፡፡ለ20 ደቂቃ ያህል ልትነጋገሩ ትችላላችሁ፡፡ለማንኛውም መነጋገሩ የሚለውጠው ነገር የለም' አለ፡፡ኮሚሲዩኑ ሶስት ቀንና ሌሊት 'ተከራክሮበት' ህገወጥ በሆነ መንገድ ድምጽ የሰጠበትን ህገማህበር፡የጉባኤው ተሳታፊ ናቸው ተብለው በግድ ወደተመልካቾችነት የተለወጡት ጓዶች ሁሉ በ20 ደቂቃ ውስጥ እንዲነጋገሩበት — ለዚያውም መነጋገራቸው የማይለውጠዉ ነገር እንዲለለ እየተነገራቸው — መጋበዙ ፍጹም በጉባኤው ተሳታፊያች ላይ መቀለድ ነበር፡፡ በ23 ኤፕሪል ህገማህበሩም ሆነ መቀደሙ በጠቅላላ ስብሰባ ላይ ውይይት ተደርጉባቸው ለድምጽ ይቀርባሉ መባሉ ትክክለኛ ዲሞክራሲያዊ ውሳኔ ነበር፡፡እንደዚያ እንዲሰራ የተባለው፡ወኪሎቹ ድምጽ ከመስጠታቸው በፊት፡ከቤቱ የሚሰነዘሩትን ማሻሻያዎች፡አሳቦችና አስተያየቶች እንዲሰሙና ይህም በድምጽ አሰጣጣቸው ላይ ተጽእኖ እንዲኖረው ነበር፡፡ይህ አልተደረገም፡፡ስለዚህ የአለምአቀፍ ጠቅላላ ጉባኤ በመጨረሻ የወኪሎች ጉባኤ ሆነ፡፡ነገሩ እንደዚህ እንደሚሆን በቅድሚያ ቢታወቅ ኖሮ ብዙ አገር አቋርጠው በርሊን ድረስ ባልሄዱ ነበር፡፡

አንዳንድ ያሜሪካ ወገን ጓዶች ለዚህ ሁኔታ ምክንያት ሲጠየቁ፡ ጊዜ በሳጠረ ነው ይላሉ፡፡ በ23 ኤፕሪል ቀርቶ በ21 ኤፕሪል መጨረሻ ላይ እንኳን — ለዚያውም ምንና ምን ያህል እንደሚሸፍን ባይወሰን በፊት — ጊዜ እንደሚያጥር ገለጸ ነበር፡፡ ሙሉ ስብሰባው ተነጋገርበት ነበርና፡፡ በዚህ ሁኔታ፡ ሀቀኛና ዲሞክራሲያዊ አሰራር ይሆን የነበረው፡ በ23 ኤፕሪል ማታ የመቀደሙ ኮሚቴውን ስራውን እንደጨረሰና ከወኪሎች በስተቀር የቀረው ለጉባኤው የመጣው ሰው ስራ መፍታቱ፡ አዳማጭ ብቻ መሆኑ ሲታይ፡ ክርክሩ በጠቅላላ ስብሰባ እንዲቀጥል ማድረግ ነበር፡፡ የተመረጠው አሰራር፡ በጊዜ ማጠር አመካኝቶ ሌሎች ጓዶች — በተለይም የአውሮጳውን ማህበር አቋም ይደገፉ የነበሩት — በክርክሩ እንዳይሳተፉ ማስወገጃ ዘዴ እንደነበረ ገለጸ ይመስለናል፡፡

የሆነ ሆኖ፡ የተባለው ጓድ የ23ቱን ኤፕሪል ስምምነት ካስታወሰና ይመዝገብልኝ ካለ በኋላ፡ የጓዱ ሊቀመንበር መቀለኝ፡ የ20 ደቂቃ 'ረፍድ' መስጠት ተቀባይነት ካጣ በኋላ፡ ሊቀመንበሩ በታላቅ ቁጣ ቦታውን ለቀቀ ወጣ፡፡ በርሱ ፈንታ ቀደሞ የጠቅላላው ስብሰባ ሊቀመንበር የነበረው፡ የቤኒኑ ጓድ፡ ተተካ፡፡ ስብሰባው በዚህ ሁኔታ እንደገና ጠቅላላ ሆኖ አንድ ቀን ሰራ፡፡ ከ23ቱ ኤፕሪል አጀንዳ ሁለት ነጥቦች ለውይይት ሳይቀርቡ ቀሩ፡፡

ከ24 እስከ 27 በነበሩት ክርክሮች ላይ እዚህ አለመለስባቸውም፡፡ ሀገማህበሩንም ያውሮጳው ማህበር ጉባኤ ይወያይበታል ብለንና እዚህ ላይ ስለርሱ አላተትም፡፡ እንዲሁ በጠቅላላው፡ ጉባኤው ወደፊት እንደሚገነዘበው ሁሉ፡ ይህ ሀገማህበር ከዲሞክራሲ መንፈስ የራቀ፡ በቀራኒዎች የተሞላ፡



ለጊዜው የተማሪ ማህበራት ሁኔታ የማይስማማ፡ መከፋፈሉን በቀላሉ ለማስከተል የሚችል መሆኑን ጠቅሶ ማለፍ ግን አስፈላጊ ይመስለናል፡፡ እዚህ ለማሳየት የምፈልገው በሁለቱ ወገኖች መካከል ያሉትን መሰረታዊ ልዩነቶች ነው፡፡ ከዚያ በፊት ግን አንድ የመጨረሻ ነገር፡፡

የተባለው ያሜሪካ ማህበር ወገን በሰራው ስራ እራሱ እምነት እንዳለነበረው፡ ልክ ምርጫ ከመደረጉ በፊት አሳይቶአል፡፡ በጉባኤው መፈጸሚያ ላይ ከዚህ የሚቀጥለው፡ የሱዳኑ ጓዱ ያቀረበው፡ የተምታታ ውሳኔ እንዲወሰድ አድርጓል፡፡

> •ይህ አሁን የሚፈጠረው የአለምአቀፍ አስተዳደር ጊዜያዊ ይሆናል፡፡ ይህም የሚሆነበት ምክንያት በኢት.ተማ. እንቅስቃሴ ውስጥ አንድ ትልቅ አካል መሪያቻቸው የመወከላቸን መብት የተወሰነ ነው ብለው ባቀረቡት ምክንያት ጉዳዩ በኢሱየ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ቀርቦ ውሳኔ እንዲሰጥበትና በአለም አቀፍ ውስጥ ተገቢ ቦታቸውን እንዲይዙ እድል ለመስጠት ነው፡፡ ያውሮጳውን ጉባኤ የተሰጠውን አባልነቱን ካልተቀበለ አሁን የተፈጠረው አስተዳደር ለዚህ አመት ይቀጥላል፡፡ ግን ያውሮጳው ማህበር ጉባኤ አባልነቱን ከተቀበለ እዚስ አስቸኳይ የአለምአቀፍ ጉባኤ ይጠራል፡ ነገር ግን ያውሮጳው ማህበር መሪዎች በዚህ አሁን በሚጠራው አመራር ላይ እምነት ካላቸው አመራሩ እስከሚቀጥለው ስብሰባ ድረስ በቦታው ይቆያል፡፡•

በ'ኦፊሲየል' ቃለጉባኤው ላይ የሰፈረው ከዚህም ይበልጥ የተምታታ ነው፡፡ ይህ አባባል ምን ማለት እንደሆነ

ለመረዳት የጠየቁ ጓደኞች 'ይህማ 'ሳቦታጅ' ማድረግ ነው' ተብለው አፋቸውን እንዲዘጉ ተደረጉ::

በስብሰባው ላይ ምን ሊባል እንደተፈለገ ለማጣራት ቈኮር:ጓደኞቹ እንደለማዳቸው ሀይ-ሀይ በለው ሁኔታው ባይጣራ ታለፈ::ይሁንና ከዚህ አባባል ለመረዳት የሚቻለው:ያውሮፓው ማህበር በጉባኤው ላይ የበርሊኖን ውጤት ካላጸደቀ ሳንዱ አመት አባልነቱን ያጣል ማለት ይመስለኛል::ግን ደግሞ የመጨረሻው አረፍተነገር ይህንን አሳብ የሚቃረን ይመስላል::ጓደኞቹ የፈለጉት ግልጽ አይደለም::ዋናው እዚህ ላይ በግልጽ የሚታየው የተመረጠው 'አስተዳደር'እስከሚመጣው ነሀሴ እራሱን እንደጊዜያዊ መቀጠሩ ነው::/በነገራችን ላይ:በኛን መጀመሪያ ገጹም የወጣው:ቀን ያልተጻፈበት:ያዲሱ አመራር መግለጫበደፈናው ስለአለም ታሪክ እርምጃ ሲያወራ:ይህንን የጉባኤውን የመጨረሻ'ውሳኔ' ሳይጠቅሰው አልፏል::

ወደዋናው አርእስት እንመለስ::የልዩነቶቹ መሰረቶች የትኞቹ ናቸው::

ከዚህ በላይ ባንድ ቦታ:ሁለቱ ያስተያየት ልዩነቶች ከስብሰባውም በፊት የነበሩ ናቸው ብያለሁ::በስብሰባውም ላይ:ገና ከመጀመሪያው:ከሁለቱም ወገን በርከት ያሉ ጓደኞች 'ትናንሽ ልዩነቶች' እንዳሉ ደጋግመው ጠቅሰዋል::ከ1970 ወዲህ ባውሮፓው ማህበር የፖለቲካ መስመር ላይ — በተለይም በቀድሞ የማህበሩ መሪዎች ላይ — ሀይለኛ ዘመቻ ሲደረግ እንደቆየ በመጽሄት የወጡት ጽሁፎች ያሳያሉ::ባሁኑ የበርሊኑ ስብሰባ ላይም ፍጹም ታይቶ በማይታወቅ አኳኋን ባውሮፓው ማህበር መስመር ላይ የተቀናበረ ዘመቻ ተደርጓል::



ልዩነቶች አሉ::ይህ የማይካድ ነገር ነው::ነገር ግን:እንደሚባለው:እነዚህ ልዩነቶች ይህን ያህልም 'ትናንሽ' አይደሉም::ባሁኑ ጊዜ የተማሪውን እንቅስቃሴ የወደፊት እድገትና የኢትዮጵያንም የወደፊት ሪቮሉሽን የሚመለከቱ ልዩነቶች ሆነዋል::እስከዛሬ ድረስ 'ትናንሽ' ያስመሰላቸው:ባውሮፓው ማህበር መስመር ላይ ሲደረግ የቆየውና አሁንም የሚደረገው ዘመቻ:እውነተኛ መልኩን ይዞ ባለመቅረቡ ነው::በ1970 'ሶሻልሾቪኒስቶችን መውጋት' የሚል ባንዲራ ይዞ ቀረበ::በ1971 አንድ የታጠቀ ጽሁፍን መሸፈኛ አድርጎ 'የወንበር ሪቮሉሽናዊያንን ማጋለጥ' በሚል መምሪያ መጣ::በ1972 ያውሮፓ ማህበር ጉባኤ ላይ 'የዲሞክራሲን መጥፋት':'የኢብነአግን መደገፍ' ሰበቦች አድርጎ ተዋጋ::አሁን በ1973:በበርሊኑ ስብሰባ ላይ 'የቀኝ ኦፖርቹኒዝምን' መውጋት የሚል አሳማ አንስቶአል::ያሁኑ ያውሮፓ ማህበር የፖለቲካ መስመር እስካለ ድረስ:የዘመቻ ፈረሱን ስም ለውጦ እንደገና መምጣቱ አይቀርም::ግን እነዚህ ሁሉ ሰበቦች ናቸው::የእውነተኛው ልዩነት ምልክቶች እንጂ ልዩነቱ እራሱ አይደሉም::የበርሊኑ ስብሰባ አንዱ ጥቅም የእውነተኛውን ልዩነት አንዱ መልክ በመጨረሻ ላይ ማሳየቱ ነው::በዚህ ላይ ከዚህ በታች እመለስበታለሁ::ግን ከዚያ በፊት ይህንን የዘመቻ አሳማ የሆነውን ያውሮፓውን ማህበር የፖለቲካ መስመር እዚህ ላይ ባጭሩ መጥቀስ ያስፈልጋል::ይህ መስመር ከዛሬ ሶስት-አራት አመታት ጀምረው በሚወጡት የማህበሩ መጽሄቶች ውስጥ ከስራ ውሎ ስለሚታይ:የበለጠ መረጃ የሚፈልግ አንባቢ የመጽሄቶቹን ይዘት እንደገና ማመዛዘን የሚያስፈልገው ይመስለኛል::እንደዚሁም የየጉባኤያቹን ውሳኔያቸ ማየት ይጠቅማል::

እንደና/ ያውሮፓው ማህበር መቀሚያ መሰረት ጸረፊውዳሊዝም–ጸረእምፔሪያሊዝም ነው::/"ጸረፊውዳሊዝም–ጸረእምፔሪያሊዝም በለው ባፋቸው ይናገራሉ እንጂ ትርጉሙ አልገባቸውም" ይላል:ካሜሪካ ጋዱ እንዱ::/ ይህ አቋም የሚያስከተለው ፖለቲካዊና ውርደታዊ ግዴታዎች አሉ::ከአሜሪካኑ ወገን ጋዶች ጋር ያልተስማማንበት መሰረታዊ ነገር ፖለቲካዊ ግዴታው ስለሆነ እርሱን እንመለከት::

በፖለቲካ በኩል:አሁን በኢትዮጵያም ሆነ በተማሪ ውስጥ ያለውን የፖለቲካ ንቃት ከፍ ማድረግ የመጀመሪያው ግዴታ ነው::ያውሮፓው ማህበር ዋና ስራ ፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳ ስለሆነ "የፖለቲካ ንቃት ከፍ ማድረግ" ማለት :በጊዜያዊው የኢትዮጵያ ሁኔታ ትንተና ላይ ተመስርቶ:በፕሮፓጋንዳ መሳሪያዎች – በመጽሄቶች – ዲሞክራሲያዊ ጥያቄዎች እንዲነሱና እንዲስፋፉ ማድረግ ማለት ነው::እንዱ እውነተኛ የልዩነት ነጥብ የዚህ ፕሮፓጋንዳ ይዘት ነው::ያውሮፓው ማህበር መስመር በሚቀጥሉት አጠቃላይ ሀሳቦች ሊገለጽ ይችላል::

ሀ/ ጠቅላላውን ያገሪቱን ሁኔታ በሚመለከተው በኩል:–

1. ፊላጭ ቆራጩ የንጉሰነገስት መንግስት ይጥፋ:: ያሜሪካን እጅአዙር ቅኝ አገዛዝ ይጥፋ::ያሜሪካና የእስራኤል የጦር ሰፈሮች ካገር ይውጡ:: የህዝብ መንግስት ይመስረት::
2. መሬት ላራሹ::
3. መሰረታዊ የህዝብ መብቶች ይከበሩ
   – የመሰብሰብ:የመናገር የመጻፍ ነጻነቶች ይኑሩ



– የብሄሮች እኩልነት ይኑር::የብሄሮች የራሳቸውን እድል የመወሰን መብት:እስከመነጠል ድረስ:ይታወቅ::

– የሃይማኖት እኩልነት ይኑር::

– የጾታ እኩልነት ይኑር

4. የሰርቶአደሩ ህዝብ መብት ይጠበቅ
   – ነጻ የላብአደር ማህበር ይኑር
   – የላብአደሩ ደመወዝና የስራ ሁኔታ ይሻሻል
   – ሰርቶአደሩ የስራ ዋስትና ይኑረው
5. ትምህርት ለሁሉ:"የጤና አገልግሎት ለሁሉ::
6. ያገሪቱ ሀብት አይዘረፍ::ያገሪው ነጋዴና ባለእንዱስትሪ አይጨቆን፣አይታፈን::

ለ/ የኤርትራን ህዝብ ትግል በሚመለከተው በኩል

1. የኤርትራ ህዝብ የራሱን እድል የመወሰን መብቱ ይታወቅ::
2. የኤርትራ ነጻነት ተዋጊዎች አንድነታቸው ይጠንክር::
3. የኤርትራና የኢትዮጵያ ተዋጊዎች አንድነታቸውን ያጠንክሩ:

ሐ/ የተማሪ ማህበራትንና ምሁራንን በሚመለከተው በኩል

1. ሰፊው ተማሪ ለጸረፊውዳል–ጸረእምፔሪያሊስት ትግል ባንድነት ይሰለፍ
2. ጸረፊውዳልና ጸረእምፔሪያሊስት ሃይሎችን ሁሉ እንደገፍ::

3. ተማሪና ምሁር ከሰፊው ህዝብ ጋር ተዋሀዱ
4. የተራማጆች ጊዜያዊ ተግባር በሰፊው ህዝብ
እንቅስቃሴ ላይ የተመሰረተ ድርጅት እንዲቋ
ቋም ማገዝ ነው::

ይህ መስመር ባለፉት ሶስት–አራት አመታት የተደረጉ
ት የማህበሩ ጉባኤዎች ካሳለፉዋቸው ውሳኔዎች ተጨምቆ የወ
ጣ ነው::እዚህ ላይ የማቀርበው የተሟላ ነው በማለት እን
ዳልሆነ አገባቡ አይስተውም ብዬ እገምታለሁ::ወደፊት በዩ
በሰጥ ስ የተሟላና እውነተኞችን የህዝብ ጥያቄዎች እያብራራ እንደሚሄ
ዱ እምናለሁ::ግን ዋናው መስመር እነዚህ ነጥቦች ከሚያመ
ለክቱት መስመር እምብዛም አይለይም::

የማህበሩ መጽሄቶች ስለወሎ ገበሬዎች ማመጽ:ስለአሰ
ራጉዳና ባለስልጣን ሰራተኞች ትግል:ስለኤቢ ነስግ ወይንም
ስለአዲስአበባ የመንደር ወሬ በሚጽፉበት ጊዜ የሚያንጸባር
ቁት ይህንን መስመር ነው::እያንዳንዱ የፕሮፓጋንዳና የቅ
ስቀሳ ጽሁፍ ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት:ከዚህ በላ
ይ ከተጠቀሱት ነጥቦች አንደኛውን:ወይም ሁለቱን:ወይንም
ሁለት–ስስቱን በጥቅል ከስራ ላይ ያውላል::ይህንን ለመረ
ዳት:እንደተባለው:ማንም ሰው የመጽሄቶቹን ይዘት መተንተን
ና የያዙትን መልእክት ማስተዋል ይቻላል::ይሁን እንጂ:
"ጸረፊውዳል–ጸረኢምፔሪያሊስት" የሚለው መስመር በዚህ ይ
ዘትና አኳኋን ከስራ ላይ ሲውል:ስህተት አይደረግም ማለት
አይደለም::ጉድለቶችና ድክመቶች አሉ::ደግሞም ሊሰሩ የሚገ
ባቸው መስት ነገሮች አሉ::ለምሳሌ:መጽሄቶችን በሌሎች ያ
ገር ቋንቋዎች ማውጣት::በኢትዮጵያ ህብረተሰብ ተጨባጭ ሁ
ኔታ ላይ የተመሰረቱ ሪቮሉሽናዊ ስነጽሁፎችን ማዘጋጀት:የ



መጽሄቶችን አሰረጫጨት ማሻሻል... ወዘተ. ::እነዚህን
ድክመቶችና ጉድለቶች ለማሸነፍ መጣጣር የያንዳንዱ አባል ሀ
ላፊነት ነው::

የተቃዋሚው ወገን ጓዶች ያውሮፓውን ማህበር በመቃወ
ም "የቀኝ ኦፖርቹኒዝም": "ሺቪየሽን"... ሲሉ በፕሮፓጋን
ዳ በኩል የሚፈልጉት በየመጽሄቱ ገጽ ላይ "ስለማርክሲዝም
–ሌኒንዝም–የማኦትሴቱንግ አሳብ" እንዲገለበጥ ከሆነ –
ክርክራቸው ይህንን ነውና የሚያመለክተው – ያውሮፓው ማህ
በር በ1967–68 ትቶት ወዳለፈው የእድገት ደረጃ ወደኋላ
ይመለስ ማለታቸው ነው::ጓዶች:ሪቮሉሽናዊ ክላሲክስ ስነጽ
ሁፎችን የማህበር አባሎቻችን ራሳቸው በእንግሊዝናም ሆነ በ
ሌላ የውጭ አገር ቋንቋ ሊያነቧቸው ይችላሉ::ያነባሉም::
ይልቁንስ ያሜሪካው ማህበር መሪዎች ጸረፊውዳልና ጸረኢምፔ
ሪያሊስት ፖለቲካ:ያገሪቷን ሁኔታ ሳይረሳ:በፕሮፓጋንዳ ደ
ረጃ እንዴት ከስራ ላይ እንደሚውል በጥሞና ቢያሰላስሉ ደ
ግ ይመስለኛል::ለምሳሌ ያህል:በዲሰምበር 1972 የወጣው
ቻሌንጅ በለማርክሲዝም–ሌኒንዝም ትሉቅነትና/ይህ አይከፋም/
የኢትዮጵያ ተማሪዎች/ከመጽሄቱ አዘጋጅ ጀምሮ/ እንዴት ወ
ደርሱ እንደተሳቡ:እንዲሁም በዚሁ መጽሄት መጨረሻ ላይ ስ
ለሰራተኛው መደብ ጠባዮች የተደረደሩትን የልምጭ ንግግሮች
/ክሊሼዎች:ስትሪፕታይዞች/ ከጸረፊውዳልና ጸረኢምፔሪያሊስ
ት የፕሮፓጋንዳ ይዘት ጋር ማመሳሰል ጥሩ ነው::እንደዚሁ
ም ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን "ህንድቡክ" ሁለተኛ ክፍልና
በ"ኮምባት" ውስጥ ስለሰራተኛው ፓርቲ –"ከማርክሲዝም–
ሌኒንዝም–ማኦትሴቱንግ አሳብ ላይ የተመሰረተ" – የተደረደ
ረውን::ጓዶች:ባንዱ በኩል የተማሪ ማህበር ህዝባዊ ድርጅ

ት ነው:መቀሚያው ፀረፊውዳል–ፀረኢምፔሪያሊዝም ነው እያለ
ን እያወጡን:በሌላ በኩል ደግሞ ይህንኑ የተማሪ ማህበር
በፕሮፓጋንዳና በቅስቀሳችን የላብአደሩ የፖለቲካ ፓርቲ አ
ናስመሰለው::'ማርክሲዝም–ሌኒንዝም እንዴት ጥሩ ነው' በ
ለን በሚያሸበርቁ ቃላት ስላመገስን:ማርክሲስት–ሌኒንስቶች
ሆንን ማለት አይደለም::የላብአደሩን ፓርቲ አቀነባበርና
አሰራር በጽሁፍ ስለደረደርን 'ፕሮሌታሪያዊ ሪቮሉሽናዊያን'
ሆንን ማለት አይደለም::የለባችን ምኞትና ተጨባጩ ሁኔታቸ
ን የተራራቁ ናቸውና እናስበበት::

ሁለተኛ/ በአስራሁለተኛው የአውሮፓው ማህበር ጉባኤ
ላይ የኢትዮጵያ ሁኔታ ከተጠና በኋላ:ይህንን ሁኔታ የሚያ
ጠቃልል አንድ መደምደሚያ ወጣ::ይህም 'ያገሪቷ ነባራዊ
/አብደከቱ/ ሁኔታ ለሪቮሉሽን ምቹ ሆኖ ሳለ:ህሊናዊ/ስ
በደከቱ/ ሁኔታው ግን ወደኋላ ቀርቷል' የሚል ነበር::
ያውሮፓውን ማህበር መስመር የሚቃወሙት ጓደኞች በበርሊኑ ስ
ብሰባ ላይ ስለ'ህሊናዊ ሁኔታ' እንዲያውም እንዳይጠቀስ
ይፈልጉ ነበር::'እኛ እያለን እንዴት እንደዚህ ይባላል'
የሚሉ ይመስል ነበር::/በነገራችን ላይ:ያሜሪካም ወኪሎች
ይህንኑ አቋም ማሳየታቸው በጣም ይደንቃል::በተባለው 'ሀ
ንድቡክ':ገጽ 22 ላይ:ከዚህ በታች የምጠቅሰውን አቋም
ወስደው ነበር::

"The most important reason why we need a political organisation is to give political education to the masses and thus make an organised preparation for a protracted struggle against the feudalists and imperialists. In Ethiopia where there has never existed a political party, freedom of speech, assembly or the press, where feudal ideology reigns supreme over an illiterate population, the need for political education must be extremely emphasized. Our peoples are totally ignorant of the most elementary political concept. Hence the need for teaching the masses starting from the most elementary, patiently working up to enable them to understand their society and to embrace socialism. ..."



ይህ ሁሉ በጠቅላላው ልክ ነው::ግን ይህንንና በጉ
ባኤው ላይ ጓደኞች የወሰዱትን አቋም ሰመሳሰል:እራሳቸው የ
ጻፉትን አልተረዱትም:ወይንም ሊያምኑበትም ከሚል በስተቀር
ሌላ መደምደሚያ አላገኘም::/

አስከዛሬ በኢትዮጵያ መሬት ላይ የፖለቲካ ፓርቲ ታ
ይቶ አይታወቅም::አስከዛሬ የህዝቡ አንድ ክፍል:ወይም መ
ደብ:ወይም የሙያ ማህበር ባንድ የተቀናበረ የፖለቲካ ድር
ጅት ስር ተሰልፎ ስራ ሲያቆም:ማመልከቻ/ፔቲሽን/ ሲጽፍ:
ሰላማዊ ሰልፍ ሲያደርግ:ከፖሊስ ጋር ሲጋጭ አልታየም::የ
ተማሪዎች ትግል ራሱ በተቀናበረ:የጊዜውን ሁኔታና የትግሉ
ን ጊዜያዊ ግብ በየደረጃው ለይቶ በከለለ የፖለቲካ ድርጅ
ት ስር አልተሰለፈም::በየቦታውና በየሁኔታው:በከተማም ሆ
ነ በገጠር:በልዩ ልዩ ጥያቄዎች ላይ ተመርኩዘው የተነሱት
ህዝባዊ ትግሎች ያልተደራጁ:ግንፍል/ስፖንታኒየስ/ ግጭቶች
ነበሩ::ናቸው::/'ተጨባጭ ሁኔታው ምቹ ነው' ሲባል አንዱ
ትርጉም ይህ ነው::ማለት:ህዝባዊ ትግሎች መኖራቸው::/ስ
ለዚህም:ከዚህ ሁሉ የሚፈልቀው መደምደሚያ የህሊናዊ ሁኔታ
ወደኋላ መቀረት ነው::ይህም:ለተማሪ ማህበርም ሆነ ላንዱ

የፖለቲካ ድርጅት ባሁኑ ጊዜ የሚያቀርበው ግዴታ አለ::
ፖለቲካዊ ህሊናን ማዳበር::በኢትዮጵያ ሪቮሉሽናዊ ህዝባዊ
ጦርነት ከመደረጉ በፊት ገና ህዝቡ የፖለቲካ ትግሎችን
ማድረግና ከነርሱ መማር ይኖርባቸዋል::

ያውሮፓውን ማህበር መስመር የሚቃወሙት ጓዶች ዋና
ምኞት ገን በጥድፊያ ወደመሳሪያ ትግል ለመሸጋገር ነው::ለዚ
ህ ማስረጃ በጉባኤው ፍጻሜ ላይ ስለኤርትራ ግንባር ወስደ
ው የነበረትን አቋምና በየጊዜው የጻፉዋቸውንና የሚጽፏዋቸ
ውን ድርሰቶች ማጥናት ይበቃል::በጉባኤው ላይ ስለኤርትራ
ግንባር የነበረትን ውይይቶች ይዘት አንባቢው ከቃለጉባኤው
ላይ ሊያገኘው ይችላል::እዚህ ላይ በለሱ አላወራም::አሁ
ን ጓዶች የጻፉትን ብቻ እንመለከት::ሆኖም ወደዚህኛው ነ
ጥብ ከመግባቴ በፊት ስለኤርትራ ተዋጊዎች ማህበሮቻችን መ
ውሰድ ይገባቸዋል ብዬ የማምነውን አቋም እንደገና ለማመል
ከት እወዳለሁ::በዚህ በኩል ማህበሮቻችን መከተል የሚገባ
ቸው የፖለቲካ መስመር በጉባኤው ላይ ተጠቀሷል:.ከዚህም
በላይ ተመልክቷል::የኤርትራ ግንባር ድርጅቶችና ማህበሮቻቸ
ን በብዙ መንገድ ሊደግፉ ይችላሉ::ባለፈው ነሀሴ ወር:
ባውሮፓው ማህበርና በኤርትራ ተማሪዎች ማህበር መካከል የ
ተደረገው ስምምነት ለዚህ መረዳዳትና አብሮ መስራት ጥሩ
ምሳሌ ነው::ይህ ስምምነት ከስራ ላይ እንዲውል መታገል
ያስፈልጋል::በተጨማሪ የኤርትራ ግንባር ድርጅቶች የርስ
በርስ ግጭታቸውን አቁመው አንድነታቸውን እንዲፈጥሩ በጥብ
ቅ ማሳሰብ አለብን::

አሁን ወደጓዶቹ ጽሁፍ ልመለስ::ያሜሪካው ማህበር
ጓዶች ስለፖለቲካ ትምህርትና ስለፓርቲ መፍጠር ቀዳሚነት



የጻፉትን ከዚህ በላይ አይተናል::በሌላ በኩ:በለዚሁ ጉዳ
ይ የሚቀጥለውን ያሰፍራሉ::

" But", some revolutionary students say, "the party can grow and develop mainly through revolutionary practice - through the cource of the armed struggle." It is true. But we say: remember, there is no Proletarian Party without the proletariat. Furthermore, under Ethiopia's present concrete condition, it would be suicidal and petty-bourgeois adventurism if individual revolutionaries tried to launch armed struggle without a minimum political party. ... A proletarian party is indispesable."

ካሉ በኋላ:ዝቅ ብለው ደግሞ:-

"However, the revolutionary students must equally reject the revisionist 'theory of productive forces' as well as the right opportunism of some comrades who want to let revolutionary situation slip while they leisurely and 'cautiously' balk of creating a political party. The armed struggle cannot be postponed indefinitly, or until a'powerful, mature and disiplined' party is created; it is not necessary that the party should have thousands or even hundreds, of members before it initiats armed struggle. To wait until such a party is created would be treason. ... " (Struggle,vol.1 No. 4. ገጽ 57 — 58:ስርዝ የተጨመረ/

ከዚህ በላይ የሰፈረትን መስመሮች ሁለት-ሶስት ጊዜ
አንብቦ በደንብ መመርመር ያስፈልጋል::ባንዱ በኩል ለይስ
ሙላ ለህዝቡ የፖለቲካ ትምህርት መስጠት ያስፈልጋል:የስራ

ተኛ መደብ ፓርቲ መፍጠር ያስፈልጋል ይላሉ::እውነተኛው
ፍላጎታቸው ግን በቶሎ የመሳሪያ ትግሉን ለመጀመር ነው::
ለዚህ ትግል በነርሱ አስተያየት ጥቂት መቶ ሰዎች ይበቃሉ::

አንዳውርጃ ማህበር ያለው የፖለቲካ መስመር — ማለት
በጸረፊውዳል–ጸረኢምፔሪያሊዝም አስተሳሰብ ህዝቡን ለማስተ
ማር በመሞከር ጊዜ ማጥፋት — ከጓዶች አቋምና ፍላጎት ጋር
እንደሚቃረን ግልጽ ነው::ዋናው የጊዜው አላማ መሳሪያዊ
ትግልን መጀመር ከሆነና ለዚህም ጥቂት መቶ ሰዎች የሚበቃ
ከሆነ:የተማሪን ማህበር በማመለከተው በኩል:ዋናው የጊዜው
ግብ ማህበሩ እነዚህን ጥቂት ሰዎች እንዲያፈራ ማድረግ ነው::
ያውርጃው ማህበር ይህንን እንደዋናው ግብ ስለማይወስድ ለ
ጓዶች የጊዜ ማጥፊያ ሆኖ እንደሚታያቸው ግልጽ ነው::ስለ
ዚህ ነው 'የቀኝ ኦፖርቹኒስት ነህ' እያሉ የሚጮሁበት::
የስድነቶቹ ሌላው ዋና መሰረት ይህ ነው::

መሳሪያዊ ትግል ከሁሉ ከፍተኛ የሆነው የፖለቲካ ት
ግል ነው::ጓዶች:በአንድ በኩል በአገራችን
የፖለቲካ ልምዱ አለመኖሩን እየተናገራችሁ:ህዝባችን የፖለ
ቲካ መሀይምን መሆኑንና ብዙ የፖለቲካ ትምህርት እንደሚያ
ስፈልገው እያወቃችሁ:በሌላ በኩል ጠብመንጃ ለመንከስ ምን
ያጣድፋችኋል::በኔ አስተያየት የዚህ አይነቱ እርምጃ ከመ
ወሰዱ በፊት ገና ብዙ ሌሎች ትግሎች መደረግ አለባቸው::
ገና ከገበሬውና ከሰራተኛው ጋር መዋሀድ ያስፈልጋል::ገና
በሰፊው ህዝብ እንቅስቃሴ ላይ የተመሰረተ ድርጅት መቋቋም
አለበት::ስለዚህም የዘረው የተራማጆች ዋና ተግባር ከገበ
ሬውና ከሰራተኛው ጋር መዋሀድ:አብሮ መሰለፍና ሪቮሉሽናዊ
ድርጅት እንዲቋቋም መስራት ነው እንጂ ይህን አስቸጋሪ ተ



ግባር /አስቸጋሪም ቢሆን መደረግ ያለበት ነው/ ወደጉን
ትቶና አንዱ እፍኝ የማይሞሉ ሁኖ የመሳሪያ ትግል መጀመር
አይደለም::

ለማንኛውም:ወጣም ወረደም:መሳሪያዊ ትግል የተማሪዎች
ማህበር ጉዳይ አይደለም::እንደተባለው የተማሪዎች ማህበራ
ት ዋና ግብ የህዝቡን ፍላጎት የሚመለከት የፖለቲካ ትምህ
ርትን ማስፋፋት:የማህበሮቻቸውን መሰረት ማንሰራራት...
ነው::ስለዚህም ባጭር ጊዜ ውስጥ በጣት የሚቆጠሩ ምርጥ
ተዋጊዎቸን ለማፍራት ሲባል ስለሚሰጠው የፖለቲካ ትምህር
ት ይዘትና ስለተማሪ ማህበራት 'ህዝባዊ ድርጅቶች' መሆን
አለመሆን አለመቸገር ፍጹም ጸረሪቮሉሽናዊ መሆን ነው::በ
ማህበሩ ስም ለመጠቀም ሲባል/ የበርሊኑ ስብሰባ ውዝግብ ይ
ህንን ጥምር አሳይቷል/ በተማሪ ማህበራት ስብሰባ ላይ ይ
ህን ያህል ማጭበርበር የሪቮሉሽናዊ ግበረገብነት ጠር መሆ
ን ነው::መሳሪያዊ ትግልን ለመጀመር በመጣደፍ:ነገ ከሰራ
ተኛውና ከገበሬው ጋር ተዋሀደው እውነተኛ ሪቮሉሽናዊ ድር
ጅትን ለመፍጠር በጣም አስፈላጊ የሆኑትን ገና እፍኝ ያል
ሞሉ ወጣት ሪቮሉሽናዊያን ኢትዮጵያዊያንን ወደማያወጣ መን
ገድ መምራት በኢትዮጵያ ሪቮሉሽን ላይ ወንጀል/'ተሪዝን/
መፈጸም ነው::እነዚህን ነጥቦች ሁሉ በጥሞና አሰላስሉ እ
ውጭውን መንገድ በቶሎ መገንዘብ ያስፈልጋል::

ለመደምደም ያህል:– ተቃዋሚዎች ከዚህ በላይ የሰፈ
ረትን አሳቦች ሲያዩ:እንደልማዳቸው 'የወንበር ሪቮሉሽናዊ:
የንኡስከበርቴ ጫሎከራት:የቀኝ ኦፖርቹኒስት...ወዘተ.'
እያሉ ቀጽል መደርደራቸው እንደማይቀር ይሰማኛል::ይሁንና

ም ድርጊት ያስተሳሰበን ትክክለኛነት ወይም ስህተተኛነት ማሳየቱ ስለማይቀር፡ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን የ[illegible] ነጥቦች እውነተኝነት የሚመጡት ሁለት-ሶስት አመታት እንደሚያሳዩ በበኩሌ ምንም አልጠራጠርም::

የበርሊኑን ጉባኤ በሚመለከተው በኩል በመጨረሻ ለማሳሰብ የምፈልገው፡ለያንዳንዱ አባል ግልጽ መሆን ያለባቸው ጥያቄዎች እንዳሉ ነው::በተለይ እያንዳንዱ አባል ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቂና ግልጽ መልስ ማግኘት ያለበት ይመስለኛል::

1. የጉባኤው አጀንዳ፡ስልጣንና ግብ ከመጀመሪያው ለምን ተጣርተው አልቀረቡም?
2. የአለምአቀፍ ማህበር አባልነትና የድምጽ አሰጣጥ የተወሰኑት በምን ሁኔታ ነው? ለምሳሌ፡አምስት አባላት ያህል ያሉት ያልጀሪያው ማህበር ከአውሮፓው ማህበር አባልነት ወደአለምአቀፉ ማህበር አባልነት እንዴትና ለምን ተለወጠ?፡አስር የማይሞሉ አባላት ያሉት የሱዳኑ ማህበር እንዴት አባል ሊሆን ቻለ? የሴቶች የጥናት ክበብ እንዴት አባል ሆነ? እነዚህ 'አባላት' እንዴት እኩል ድምጽ ተሰጣቸው?
3. የጉባኤው የስራ አካሄድ እንዴት ነበር? ህገወጥና ጸረዲሞክራሲያዊ የሆኑ አሰራሮች አልነበሩምወይ? ለነዚህ ሀላፊነቱ የማን ነው?
4. የኤርትራን ግንባር ድርጅቶች በሚመለከተው በኩል የማህበሮቻችን አቋም ምን መሆን አለበት?
5. በጠቅላላው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራት የጊዜው



የፖለቲካ መስመር ምን መሆን አለበት?፡የጸረፊውዳሊዝም-ጸረኢምፔሪያሊዝም አቋም ይዘት ምንድን ነው::በምንስ መገለጽ አለበት?

6. በተለይ በህገማህበሩ ስራ ውስጥ ጠቅላላ ስብሰባው እንዳይሳተፍ የተደረገው ለምንድን ነው?፡የወጣው ህገማህበር ለጊዜያዊው የተማሪዎች ማህበራት ተስማሚ ነወይ?

እነዚህ ጥያቄዎች ሀቀኛና አጥጋቢ መልስ ካገኙ ለማህበሮቻችን ጥንካሬን ያስከትላሉ ብዬ አምናለሁ::በማጭበርበርና በማድበስበስ ከታለፉ ማህበሮቻችን ይዳከማሉ::ይህም በተጨበጠ አኳኋን ለኢትዮጵያ አድሃሪ ስርአትና ለኢምፔሪያሊዝም-ጽዮኒዝም ትልቅ እርዳታ ይሆናል::በበኩሌ ማህበሮቻችን የጊዜውን ችግርና ውዝግብ ማሸነፋቸው እንደማይቀር ሙሉ እምነት አለኝ::

አስራት ገርማ

ግንቦት 1965



# ትግላችን

አለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር

ወርሃዊ መፅሄት

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የተዘጋጀ

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር
የ10ረኛው ጠቅላላ ጉባኤ ዜና

የመፅሄት አዘጋጅ ቦርድ
P. O. BOX 3198
103 64 Stockholm 3
SWEDEN

ልዩ ቁጥር
መስከረም 1963

ዋጋው፡- 1.50 ብር

## ይዘት


| | ገጽ |
|---|---|
| የተማሪዎች ትግልና አሥረኛው ጉባዔ | 1 |
| የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴው ሪፖር | 19 |
| በሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር ወኪል ንግግር | 30 |
| የአንድነት ድጋፍ | 36 |
| የማጋለጥ ትግል | 50 |
| የመሰነባበቻ ምሽት | 62 |


## የተማሪዎች ትግልና አሥረኛው ጉባዔ

ዓለም የትግል መስክ ናት፡፡ፍጥረት በሙሉ በዙሪያው ከሚገኘውና ከራሱ ጭምር ሲታገል ኖሮአል፤ትግሉንም ይቀጥላል፡፡ለጊዜው የጠቀሳሳውን ፍጥረት ታሪክ ወደጉን ትተን የሰውን ልጅ ታሪክ ብቻ ብንመረምር በታሪኩ ገጽ በሙሉ ሠፍሮ የምናገኘው "የዚህ ትግል" ዜና ነው፡፡

የሰው ልጅ ለመኖር መብላት፡መልበስና መጠለል ሲኖርበት ፍጥረት ደግሞ ለነዚህ የሚያስፈልጉትን ሁሉ በተሰናዳ መልክ አታቀርብለትም፡፡እነዚህን ዓቢይ ፍላጎቶች ለማርካት መሥራትና ከዙሪያው ጋር መታገል አለበት፡፡ይህ ሥራው አዲስ ብልሀትን፡አዲስ ፍላጎትን እያስከተለ ስለሚሔድ ትግሉን ከዝቅተኛ ወደከፍተኛ ደረጃ እንዲራመድ ያደርገዋል፡፡አዱርጉታልም፡፡

በዙሪያችን የምናየው የዕቃ ክምር፡የጥበብ ምርት...የዚህ ተግባርና ትግል ውጤት ነው፡፡የሰው ልጅ፡በደረሰበት የዕውቀት ደረጃ መጠን፡መሬትን የአስፈላጊዎች ሁሉ ምንጭ ለማድረግ የቻለው፡ሰማይን የጉዞ ማቋረጫ ያደረገው፡ውቅያኖስን ለመንሸራሸሪያና ለብዙ ጥቅሞች ያዋለው በዚሁ ትግሉ እየተመራ ባገኘው ዕውቀት አማካይነት ነው፡፡በሽታ በመድሐኒት፡ድንቁርና በዕውቀት፡ጥንቆላና ሕልም በሳይንስ የተሸነፉት በዚሁ ትግል ነው፡፡

ትግሉ ከፍጥረት ጋር ብቻ ተወስኖ አይቀርም፡፡ከፍጥረት ጋር የሚደረገው ትግል የሚያመነጨው ዕውቀትሰዎች እርስ በርሳቸው መግባባት፡መያያዝና መተሣሠር እንደሚገባቸው ያስስባቸዋል፡፡በነጠላ ሳይሆን አብሮ መኖር፡ለብቻ ሳይሆን አብሮ መሥራት የተሻለ መሆኑን ያስገነዝባቸዋል፡፡

አብሮ መኖር ደግሞ፡ከጊዜ በኋላ፡የአንዱን ጥቅም ከሌ

ሳው ስለሚያጋጭ እርስ በርስ መታገልን ያስከትላል::ሰው
ከ"ብቸኛነት" ተነስቶ:አብሮ በመኖር:መጀመሪያ ቋንቋን፣ከ
ዚያ ልዩ ልዩ ሥርዓተ ማኅበራትን በየተራ መገንባት የቻለ
ው በዚህ "ጠቅላላ ትግሉ"አማካይነት ነው::የጋርዮሽ:የባ
ርነት:የባላባት:የካፒታሊዝም ሥርዓተ ማኅበር እየተከታተሉ
የመጡት በዚህ ትግልና በሚያስከትለው ዕውቀት በመመራት እ
ንጂ በቀደምትነት በማንም ሰው አዕምሮ በመፀነስ አይደለም

ዛሬ የደረስንበት የሶሻሊዝም — የእኩልነት — ሥርዓ
ተ ማኅበር ከሰማይ ዱብ ያለ አይደለም::የሰው ልጆች ጭን
ቅላታቸውን በመፍለጥ ብቻ የፈለሰፉት አይደለም::አንዳንድ
አሳቢ ፈላስፋዎች ጠቅላላው ትግል ያስገኘውን ሰፊ ዕውቀት
በመመርኮዝ:በዙሪያቸው የሚያዩትን በማቀናበርና በማሻሻል
የመሠረቱት ሥርዓት እንጂ::

የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበራትም የተከተሉት ጎዳና ከዚሁ
ጠቅላላ የታሪክ መስመር አይለይም::ዛሬ የኢትዮጵያ ተማሪ
ዎች እንቅስቃሴ ከፍ ያለ የትግል ደረጃ ላይ ደርሶአል::
ግን መዘንጋት የሌለበት ይህ ደረጃ በአንድ ቀን እንዳልተ
ደረሰበት ነው::የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበራት አሁን አሉ
በት አቋም ከመድረሳቸው በፊት ብዙ የትግል ደረጃዎችን አ
ልፈዋል::ዛሬ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበራት ረቮሉሽናዊ
ናቸው::መረሳት የሌለበት ግን ረቮሉሽናዊ ሆነው እንዳልተ
ወለዱ ነው::ረቮሉሽናዊ የሆኑት በማወቅና ባለማወቅ:በዱሃ
ሪና በወደፊት ተራማጅ ርዕዮተዓለም መካከል የተደረገው ረ
ጅም ትግል ሰፊ ያለ የዕውቀት ቅርስ ጥሉላቸው ከሔደ በኋ
ላ ነው::

የአውሮፓው ማኅበራችን ከተቋቋመ አሥር ዓመት አለፈው
በነዚህ ዓመታት ውስጥ የአውሮፓው ማኅበራችን ብዙ ትግሎች
ን አከናውኗል፣ብዙ ዕውቀቶችን አፍርቷል፣ብዙ ድሎችን ተጐ
ናጽፏል::አድጓል::



በዚች አጭር ጽሑፋችን ውስጥ ስለጠቅላላ ታሪኩ ዝርዝ
ዝር ሀተታ ለማቅረብ አልተነሣንም::ባለፉት ዓመታት ውስጥ
በ"ታጠቅና" በ"ትግላችን" ስለኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበራ
ትና ስለእንቅስቃሴያቸው ሰፊ ሀተታ አቅርበናል::አንባቢዎ
ች እነዚህን ጽሑፎች እንዲያነቡ እያሳሰብን እዚህ ላይ
"በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር" ከተመሠረተ ጀም
ሮ ያከናወናቸውን ዋና ዋና የርዕዮተዓለምና የፖለቲካ ትግሎ
ች ብቻ ባጭሩ እናቀርባለን::

በርከት ያሉ ተማሪዎች ለከፍተኛ ትምህርት ወደባሕር
ማዶ የወጡት በ1950 —(1960:እአአ) መሀከል ነው::
አገራችን በነበርንበት ጊዜ የሚለፈፍልን ፕሮፓጋንዳ ሁላች
ንም ሳይገርፈን እንዳላለፈ ይገመታል::"ሀብታሚቱ ኢትዮ
ጵያ":"በሥልጣኔ ላይ የምትራመደው ኢትዮጵያ" የሚለው የ
ተዛባ ፕሮፓጋንዳ ጆሮ ከማቁሰሉና ዓይን ከመጋረዱ በላይ
ትዕቢትንም ሳያሳድር አልቀረም::በዚህ ትዕቢት ተሞልተው
ለመጀመሪያው ጊዜ ባሕር ማዶ የተሻገሩ ወንድሞቻችን የአው
ሮፓንና የአሜሪካን የኑሮ ደረጃ ከፍተኛነት ሲመለከቱ አይ
ናቶት ብቻ ሳይሆን "ዕፍረት" እንዳደረባቸው አይጠረጠርም

የኑሮ ደረጃ ወደደነደነበት አገሮች ሲደርሱ "ኩራታቸ
ው"ተሰባበሮ ወደቀ::ያገራቸውን ሁኔታ ካሉበት ዙሪያ ጋር
በማወዳደር ከፍ ያለ ፀፀትና ሀዘን ተሰማቸው::"ለካ አገ
ራቸው የድሃ አገር ናት፣በሽተኞች የሞሉባት ናት፣ዕውቀት
ዝቅ ያለባት አገር ናት::ለምን? ዓለም እንደዚህ መንደላ
ቀቅበጀመረበት ጊዜ?"እንደዚህ ባለ የሐሳብ ባሕር ውስጥ
መዋኘትና ከሕሊናቸው ጋር መታገል የጀመሩ አይጠፉም::

በተገናኙ ቁጥር የውይይቱና የንትርኩ ዋና አርእስት
ይኸው ያገር ጉዳይ ሆነ::ከመንፈሳቸው ጋር መታገል:በሐሳ
ብ ውስጥ መዋኘት...መንፈሳቸውን አሳረካውም::በወረ ሰ
ይሆን የአገር ግዴታቸውን "በተግባር ማሳየት አለባቸው":
ከእንግዲህ ወዲህ "ጠንክሮ መሥራት አለባቸው"::

ከ1952 — 1958 ዓ ም በአውሮፓ አገሮች በየቦታው ለተቋቋሙት ማኅበራት አንደኛው አንቀሳቃሽ ኃይል "የብቸኝነት ስሜትና አብሮ የመገኘት ፍላጎት" ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ "ለአገር መቆጨት" ያስከተለው "ስሜት" ነው ብንል ከዕውነቱ ብዙ የምንርቅ አይመስለንም::

የነዚህ ማኅበራት ቆርቋሪ ድንገት ጓብ ያለ ሐሳብ እንደመሆኑ መጠን የቆመበት ዓላማ ግልቀትና ስፋት የተወሰነ ነበር::አብሮ ከመሰብሰብና በስብሰባው ላይ በሚታወቁ አርእስቶች ከመወያየት ሌላ የተለየ ዓላማ አልነበራቸውም::ቢሆንም ለጊዜው አንድ ጋር የመሰብሰብን ዕድል ስለሰጡ አስብ ለአስብ የመለዋወጫ ሸንጎ ለመሆን ቻሉ::

በነዚህ ማኅበራት አማካይነት ተማሪዎች ስለሀገር ታሪክ:ስለሀገር ልምዱና ወግ:ስሳለው አስተዳደር መወያየት ጀመሩ::በዚያን ጊዜ የአብሳትን መንፈስ ያነቃቃ የነበረው እንደ "የተማሩ ያንሳሉ:ባለሥልጣኖች ጉብ ይበላሉ:ሕጉ በደንብ አልተሠራበትም:ቶሎ ተመልሶ አገርንና ወገንን ማገልገል ያስፈልጋል" ባሉ አርዕስቶች ላይ የሚደረጉት ውይይቶች ነበሩ::

አንዳንዱ ማኅበራት በራሳቸው አካባቢ ብቻ ተወስነው አልቆሙም::በሌሎች የአውሮፓ አገሮች የሚገኙትን አባላትና ማኅበራት ለመገናኘትና አንድ ዓይነት ቋሚ "መተሣሠሪያ" ለመፍጠር ይጣጣሩ ጀመር::እንደአጋጣሚ ሆኖ በርከት ያሉ ተማሪዎች — በተለይ ከብር ቴይን:ከጀርመን:ከፈረንሣይ — በ1958:እአአ:ብሩክሲል ላይ በተደረገው የዓለም አቀፍ ኤግዚቢሽን ላይ ተገናኙ::ይህን ዕድል በከንቱ ባያሳልፉ "የአንድነት ማኅበር" ለማቋቋም ተስማምተው ተለያዩ::

በዚህ ስምምነት መሠረት በ1960:እአአ:ቦን ላይ ስብሰባ ተደረገ::በስብሰባው ላይ ከብር ቴይን:ከፈረንሣይ:ከ



ጀርመን:ከጣሊያን:አንዳንዶችን ለመጥቀስ ያህል:በርከት ያሉ ተማሪዎች ተገኝተዋል::በዚህ ስብሰባ ላይ ሕገ ማኅበር ረቂቅ ከጸደቀ በኋላ "በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር" ተመሠረተ::

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በእያንዳንዱ አገር ያሉ — ቅርንጫፍ — ማኅበራት በሙሉ የተከተሉት የአውሮፓውን ማኅበር ዓላማና የሥራ ትልም ስለሆነ የእያንዳንዱን ማኅበር ታሪክ ማውሳት አስፈላጊ አይሆንም::ስለዚህ ከዚህ ቀጥለን የአውሮፓውን ማኅበር ተግባር በጭሩ እናሠፍራለን::

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር በነዚህ አሥር ዓመታት ውስጥ:በጠቅላላ አነጋገር:በአራት ዋና ዋና የትግል ደረጃዎች አልፍአል ለማለት ይቻላል::

የመጀመሪያው ደረጃ "የአቤቱታ" ወይም "የልመና" ዘመን ነበር::በዚያን ጊዜ ማኅበረተኞች በሙሉ የአገራቸውን በአሰቃቂ ሁኔታ ላይ መገኘት ቢገነዘቡትም የጉዳቱ ምንጭ ምን እንደሆነ ገና አላወቁትም ነበር::ችግሩ ከ"ገንዘብ ማጠር የመጣ ነው":ጉዳቱ "የተማሩ ሰዎች እጥረት ነው" "ባለሥልጣኖች ሰነፎች ናቸው":"ሕጉ በሚገባ አልተሠራበትም" በማለት እነዚህ ይታረሙ ዘንድ ለመንግሥቱ "በማክበር ያመለክቱ" ነበር::እርሻ እንዲስፋፋ:እንዱስትሪዎች እንዲከፈቱ:ትምህርት ቤቶች በብዛት እንዲሠሩ:ጎዳናዎች እንዲዘረጉ አሁንም ለመንግሥቱ "በትህትና ያሳስቡ" ነበር::የመንግሥቱን ጠቅላላ አቋምና ባህሪ በምንም ዓይነት ከጥያቄ አላገቡትም:እንዳለ ቢቀበሉት የሚያመለክቱት አንዳንድ ጉድለቶችን በመልካም ፈቃዱ እንዲያርም ብቻ ነበር::ይህን ለመረዳት በ1961 ፓሪስ ላይ:በ1962 በርሊን ላይ:በ1963 ኦበርናይ ላይ የተደረጉትን ጉባዔዎች ውይይት ማስታወስ ይበቃል:: (ዓመተ ምህረቶች የተመለከቱት እአአ ነው)

ይህ የመጀመሪያው የትግል ደረጃ ነበር::የይዘቱ ዝቅ

ተኛነት የማይካድ ቢሆንም ያስከተለው ዕውቀት — ለሚቀጥለው ትግል — በትንሹ የሚገመት አልነበረም።በትህትና የቀረቡት ምክሮች ሁሉ "በማይሰማ ጆሮ" ላይ ወደቁ።እንዲያውም "ልጆቻችን ባለጉ እኮ! ለትምህርት እንጂ መቼ ፖለቲካ እንዲያወሩ ላክናቸው?" የሚል ገስጻን ያስከተሉበት ጊዜ ነበር።

ምክር እንደሬት የሚመረው፡ጠቃሚ ወቀሳን እንደስድብ የሚቆጥረው ባላባታዊ መንግሥት እነዚህን ጠቃሚ ምክሮች ለማዳመጥ አልቻለም።ጆሮውን አቃጠሉት፣ሕሊናውን አስበረገጉት

በባላባታዊው መንግሥት በነዚህ ማሳሰቢያዎች ላይ የወሰደው እርምጃ ለብዙ አባሎች ጠቃሚ ትምህርትን ሰጠ።ብዙዎቹ መንግሥቱ ያለውን በጎ ፈቃዱ ብቻ ሳይሆን የራሳቸውንም አቋም ጭምር መመርመር ጀመሩ።"የመንግሥቱ መሪዎች የአገሪቱን ሁኔታ ለማሻሻል ፍላጐት አላቸው ወይ? ማኅበራችንስ በመንግሥቱ ላይ የወሰደው አቋም ትክክል ነው ወይ?" አንዳንዱ አባላት በነዚህ ጥያቄዎች ብቻ አልተገቱም።የአገራቸውን ጠቅላላ ሁኔታና ታሪክ ማጥናት፡የዓለምን ሁኔታ በደንብ መመልከት ጀመሩ።

የሁለተኛው ደረጃ የነዚህ ጥያቄዎችና ምርመራ ውጤት ነበር ለማለት ይቻላል።ይህን ደረጃ ዓይነተኛ የሚያደርገው "የጥገና ለውጥ" ፍላጐት ገኖ መታየት ነው።እርግጥ ነው ይህ ደረጃ በጠቅላላ ጠባዩ ከመጀመሪያው ደረጃ አይለይም።ሁለቱም ይሻሻል ነው የሚሉት።ነገር ግን ሁለተኛው ደረጃ ያቀረባቸው ጥያቄዎችና የሰነዘራቸው ማሳሰቢያዎች ይዘት ትንሽ ጠለቅ ያለ ነበር።ይህን ቀጥሎ በምናቀርበው ሀተታ እንረዳዋለን።

እዚህ ላይ በጥሩ ለማመልከት የምንፈልገው የትግሉን አስተዳደግ ነው።የመጀመሪያው የትግል ደረጃ ዝቅተኛ ነበ



ር።ግን በመጠኑ ምርመራንና ዕውቀትን አስከተለ።የተገኘው ዕውቀት ደግሞ ወደሚቀጥለው የትግል ደረጃ መራ።ከፍ ብለን እንደጠቀስነው ማኅበራችን ያደገው በዚህ ዓይነት ዘዴ ነው።ማለት በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚደረገው ትግል ለሚቀጥለው መሠረትና መነሻ እየሆነ።በመግቢያችን ላይ እንዳመለከትነው ይህ የማንኛውም "አስተዳደግ" ቋሚ ሕግ ነው

"የጥገና ዘመን" አንዱ ሁለት ዓመታት ያህል ወስዷል ይህ ዘመን ልክ እንዳለፈው ጊዜ የኢትዮጵያ ሥርዓተ ማኅበር በደንብ ያልተጠናበት፡ያገዛዙ ባሕርይ በደንብ ያልተመረመረበት፡የታሪክ እርምጃ በደንብ ያልታወቀበት ጊዜ ነበር። "በጥገና ዘመን" ጎልተው የታዩት "የመሪዎች ችሎታ ማነስ፡የባለሥልጣኖች ቀጥተኛ አለመሆን፡የፍርድ መዛነፍ ...፡የመንግሥቱ መሪ፡የኃይለሥላሴ፡ዲክቴተርነት" ነበሩ።የቀረቡትም ጥያቄዎችና ማሳሰቢያዎች እነዚህኑ አስተያየቶች የተመረኮዙ ነበሩ።እስቲ እንመልከታቸው።

"ነገሩን ያበላሸው የኃይለሥላሴ ፈላጭ ቆራጭነት ነውና የተስተካከለ የሥልጣን ክፍያ ይደረግ፣ችሎታ የሌላቸው መሪዎች እየተነቀሉ በቦታቸው የተማሩ ወጣቶች ይተኩ፣ባለሥልጣኖችና ሀብታሞች የቀረውን ሕዝብ እንዳይጨቁኑት ራሱን የቻለ ፍርድ ቤት ይቋቋም፣የማያዳሉና ሕግ አዋቂ ዳኞች በሕዝቡ ይመረጡ፣ዳኞችና ባለሥልጣኖች ከሕዝቡ ጉቦ እንዳይበሉ ከፍተኛ ቁጥጥር ይደረግ፣የጋዜጣና የሐሳብ ነፃነት ይሰጥ፣መሬት ላራሹ የሚለው ደንብ በሥራ ላይ ይዋል ...።"

እንደምንመለከተው ማሳሰቢያዎቹ በሙሉ የሚጠይቁት የመንግሥቱን በመላ መሻሻል ነው።እንደመጀመሪያው ጊዜ አንዳንድ ነገሮች ብቻ በደንብ እንዲሠሩ አይደለም የሚጠይቁት፣የመንግሥቱ አቋም ከላይ እስከ ታች በደንብ እንዲጠገን ያሳስባሉ።የማሳሰቢያ አቀራረቡም ለወጥ ያለ ነው።እንደበፊቱ "በማክበር እናመለክታለን" የሚለው ቀርቶ "የኢትዮ

ጵያዊነት መብትና ነፃነታችንን በመመርኮዝ አናሰስበለን" የ
ሚለው ቦታውን ወስዶታል::

ቀገናዊ ዘመን ጠንከሮ የታየው ቦለኛ ሳይ በ1964፡
እአአ፡በተደረገው 4ኛው ጉባዔ ሳይ ቢሆንም በ1963ቱ የ
ኦበርናይ ጉባዔ ሳይም ብቅ ብቅ ማለት ጀምሮ ነበር ለማለ
ት ይቻላል::

"የቀገና ለውጥ" መምሪያ አስብ የጠበቀ መሠረት የሌ
ለው እንደመሆኑ መጠን "የቀገና ለውጥ" ዘመን ረጅም ዕድ
ሜ ሲኖረው አልቻለም::በቀገና ለውጥ ዘመን የቀረቡት ማበ
ሰቢያዎችና ቀያቄዎች በመንግሥቱና በዶሃሪ ኃይሎች ሳይ ቱ
ጭትንና ቅጣን እንጂ ምርመራን አሳስከተሉም::የቀያቄዎቹ
መጠሳትና አፃማጭ ማጣት፡የአገሪቱ ችግር እየተበባበሰ መሔድ
የአዶሃሪዎች አንቀፋት ለመፍጠር መቆከር "የጊዜውን ወደ
ፊት ተራማጆች" ተገበር ሲያቃልል አብዛኛውን ተማሪ ደገፎ
በመንግሥቱ ሳይ በይበልጥ አሸፈተው::ማኅበረት ሁሉ በያሉ
ክት፡በአውሮፓው ማኅበር አነሳሽነት፡ከፍ ያለ ምርመራና ት
ነል ጀመሩ::ይህች አጭር ጽሑፍ እንዳትረዝም በመስጋት ዝ
ርዝር ሀተታ ባናቀርብም የ60 ዓ ም "ኩ ዴ ታ" እና የ
አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ያከናወኑቀቸው ፖለቲካዊ
ትገሉች ለአውሮፓው ማኅበር ከፍ ያለ ፖለቲካዊ ሕሊና መስ
ጠታቸውን መቀቀስ እንወዳለን::

በዚህ ጊዜ የተደረገው ምርመራና ትገል ሦስተኛውን የ
ትገል ደረጃ አስከተለ::ሦስተኛው ደረጃ "የምርመራና የተ
ቃውሞ" ዘመን ነበር::በዚህን ጊዜ የኢትዮጵያ ሥርዓተ ማ
ኅበር አቋም ተመረመረ::የዓለም ሁኔታ ተጠንቶ ዓይነተኛ
የሚያደርገው ጠባዩ ታወቀ::የታሪክ ነስጋሴ ዓይነተኛ ፈሊ
ቀ ምን እንደሆነ ለመገንዘብ ተቻለ::

በአገራችን ፍርዱ የተዛባው፡ዶህነት ዶንቧኑን በስፊው



የጣለው፡ትምህርት ያነሰው፡በሽታና መሃይምነት የነገሡት፡ዕ
ዱገት ታፍኖ የተያዘው... የመንግሥቱ በጉ ፈቃዱ በመጉደ
ሉ ብቻ ሳይሆን ከጠቀሳሳ ሥርዓተ ማኅበር ኢኮኖሚያዊ፡ፖለ
ቲካዊና ባሕሳዊ አቋም ጭምር የተነሣ መሆኑ ገልጽ ሆነ::
በዚህ ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ አገዛዙ የያዘው ቦታ "ለሕዝ
ብ ዕዱገት ምንም ጉጉት" እንደማይሰጠው መገንዘብ ተቻለ፡
ችሉታውም የመነመነ መሆኑን ለመረዳት አሩቅ መሔድ አሳስፈ
ለገም::

ምርመራው በዚህ ብቻ አልተወሰነም::የአገራችንን አቋ
ም ብቻ ሳይሆን የዓለምም ሁኔታ ተመረመረ::የታሪክ አርም
ጃ ተጠና::ይህ ጥልቅ ምርመራ አንዱ መሠረታዊ ነገርን አ
ስከተለ:—

> በየአገሩ በሙሉ በኢኮኖሚ ጥቅም የተለያዩ መደቦች
> እንዳሉ::እነዚህ መደቦች ሁልጊዜ በጥቅም እንደሚ
> ጋጩ::የሀብት ምንጭንና ኃይልን የያዙ መደቦችን
> በምክርና በመለማመጥ ለሕዝብ ጥቅም እንዲሠሩ ለማ
> ድረግ እንደማይቻል::

ይህ በጣም ጠቃሚ ትምህርት ነበር::ከዚህ መሠረታዊ
ትምህርት የተነሣ በዓለም በሙሉ በአንድ ወገን አዶሃሪ ኃ
ይሎችና የሕዝብ ጠሳቶች፡በሌላው የወደፊት ተራማጁ ኃይሎች
ና የሕዝብ ወገኖች እንደተሰለፉ ለመረዳት ተቻለ::

"የምርመራና የተቃውሞ" ደረጃ በደንብ የታየው በ
1965 ቯየና ሳይ በተደረገው 5ኛ ጉባዔ ሳይ ነበር::ይ
ህ ጉባዔ በኮሚቴዎች ተከፋፍሉ የዓለምን ጠቀሳሳ ሁኔታ፡የ
ኢትዮጵያን የውጭና የውስጥ ፖለቲካ፡የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ፡
የኢትዮጵያን የትምህርትና የጤና ድርጅቶች፡የኢትዮጵያን ኅ
ብረተሰባዊ አቋም በተጠበጡ ዕውነቶችና ስታቲስቲኮች ሳይ
ተመርኩዞ በዝርዝር ካጠና በኋላ የሚከተሉትን ውሳኔዎች አ
ሳለፈ::

ኢትዮጵያን በሚመለከተው በኩል:—

...ለጥቂት ሰዎች ዱሉት የተፈጠረው መንግሥታዊ አቋም የኢትዮጵያን ሕዝብ ካለበት ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ሊያወጣው የማይችል መሆኑን በመገንዘብ ጉባዔው

1 በፊውዳሉ አገዛዝ የተመሠረተውን ይህን መንግሥት በጥብቅ ይቃወማል

2 ይህም መንግሥት እንዲለወጥ፡ለሀገሩ ዕድገትና ልማት ከሚጥሩት ድርጅቶችና አርምኛዎች ጋር አንድነቱን በመንፈስም በግብርም ይገልጻል::

3 ...የአሜሪካ መንግሥት በፍጥነት የጦር ጓዙን ጠቅልሎ እንዲወጣ ይጠይቃል:: ...የአሜሪካ የጦር ዕርዳታ፡የአሜሪካ የሰላም ጓዶች፡የአሜሪካ የራዲዮ ጣቢያ፡የካርታና የጂኦዴሲ ኢንስቲቱት በሙሉ ከኢትዮጵያ እንዲወጡ ይወስናል::

ጠቅላላውን ዓለም በሚመለከተው በኩል የቪየናው ውሳኔ በመግቢያው ላይ እንዲህ ይላል:—

ያለፉት ዓመታት ታሪክ የሚያሰስበን በዓለም ውስጥ በልዩ ልዩ ዓይነት መንገድ በተጨቆኑ ሕዝቦችና በኢምፔሪያሊስቶች መካከል ያለው ተቃራኒነትና ትግል እየተፋፋመ መሔዱን ነው::በተጨማሪም ለሙሉ ነፃነትና መብት የሚታገሉ ወገኖች በያለበት እየተስፋፉ በመሔድ ላይ ናቸው::

ለዓለም ሰላም ዕውነትና መሠረት ባለው አኳኋን ከተጨቆኑ ወገኖች ጋር ሆነን በመላው ዓለም ለበጎ ለውጥ መሥራት እንደምንችል እንገነዘባለን::

ይህ በውነቱ ታላቅ እርምጃ ነበር::አሁን የተደረሰበ



ት ደረጃ ማኅበራችን ለተጋድሎና ለውጊያ "ታጥቆ መነሣቱን" በግልጽ ያሳያል::የመጀመሪያው የቅዠት ዘመን አለፈ፤"የጥገና ለውጥ" ምንም ጥቅም እንደማይሰጥ ታውቆ "የተቃውሞና የተጋድሎ" ዘመን ተጀመረ:: "የመሠረታዊ ለውጥ" ፍለጋ ዘመን መሠረቱን ጣለ::ይህ መሠረት በተፋጠነ መንገድ እየጠከረ መሔዱን ኬንት ላይ የተደረገው 6ኛ ጉባዔ ውሳኔዎች በጉልህ ያሳያሉ::

እርግጥ ይህ ዘመን የከፍተኛ ትግል ዘመን እንደነበረ አይጠረጠርም::ማኅበራችንም መዓበሩ አይከዱም::ቢሆንም ብዙ ያልተመለሱ መሠረታዊ ጥያቄዎች ነበሩ::ለምሳሌ ያሁኑ ባላባታዊ መንግሥት በምን ዘዴ እንደሚጣል፤በቦታው ምን ዓይነት መንግሥት መተካት እንደሚገባው፤የተማሪዎች ተግባር ምን መሆን እንዳለበት::እነዚህና እነዚህን የመሰሰሉ ጥያቄዎች ገና አልተመለሱም ነበር::

ታሪካዊው 7ኛው ጉባዔያችን እነዚህን ጥያቄዎችና ያስከተሉዋቸውንም ጥርጣሬዎች አንድ ባንድ ለመመለስ ሞከረ:: ሰባት ዓመታት ሙሉ የተደረጉትን ትግሎች ተግባር ከመረመረና አስከዘሬ ድረስ የተደረጉትን ጥናቶች በደንብ ከቀሰመ በኋላ 7ኛው ዓመታዊ ጉባዔ የሚከተሉትን ውሳኔዎች አሳለፈ::

1 ... የሥራችን መነሻ ሁሉ ከገበሬውና ከሠራተኛው — ከተበደለው ሕዝብ — ጋር በመቀላቀል አሁን ያለውን ጊዜው ያለፈበትን ባላባታዊ መንግሥት መጣል መሆኑን ጉባዔው ተስማምቶበታል::

2 ... ለነገይቱ ኢትዮጵያ ተገቢ የሆነ ሕዝባዊ መንግሥት ማቋቋም አስፈላጊ መሆኑን ጉባዔው ተስማምቶበታል::

ውሳኔዎቹ፡7ኛው ዓመታዊ ጉባዔ 4ኛውን የትግል ደረጃ እንደከፈተልን፡በግልጽ ይናገራሉ::4ኛው የትግል ደረጃ ዘ

ረ የደረስንበትና "ረቮሉሽናዊ የትግል ደረጃ" ብለን የም
ነጠረው ነው::ረቮሉሽናዊ የሚያበኙት በጠላቶች ላይ ያሳለፉ
ቸው ውሳኔዎች ጥልቀት ብቻ ሳይሆን በትግሉ ውስጥ ለራሱና
ለአበሳት የሰጠው አቋም ጭምር ነው::

አስከዛሬ ድረስ ማኅበሩና አበሳት በሕዝቡ ላይ የነበ
ራቸው ዕምነት ይህንም ያህል የደነደነ አልነበረም::ከበላ
ባታቸው አቋም የወረሱትና በኢምፔሪያሊስቶች ከተቀረጹት ት
ምህርት ቤቶች የቀሰሙት ርዕዮተዓለም ሕዝቡን እንዲንቁና
የገበሬውንና የሠራተኛውን መደብ ታሪካዊ ድርጊት ዝቅ አድ
ርገው እንዲመለከቱ ስላደረጋቸው የራሳቸውን ነፃ አውጭነት:
አቀቂነትና መሪነት ሲያጋንኑ ይታዩ ነበር::

7ኛው ጉባዔ ይህንን የተሳሳተ አስተያየት በሚገባ አ
ረመው፤ ምንም ብንማር:ምንም አዋቂ ብንሆን ለራሳችን የም
ንሰጠው ግምት የበላይነት ወይም ከላይ ቁጭ ያለ መሪነት
ከሆነ ረቮሉሽናዊ አለመሆናችንን አስረድቶ ትክክለኛው ቦታ
ችን ከሕዝቡ ጋር መዋሀድ:ከሕዝቡ መማር:ከሕዝቡ ጋር ተሰ
ልፎ "ትክክለኛውን አመራር መስጠት" መሆኑን አብራራልን::
የረቮሉሽኑ ሕይወት:ምሰሶና አንቀሳቃሽ ግን ሕዝቡ ራሱ —
ገበሬውና ሠራተኛው —መሆኑን በሚያጠግብ አኳኋን ገለጸልን

7ኛው ጉባዔያችን በማኅበራችን ሕይወት ውስጥ አዲስ
የትግል ምዕራፍ ሲከፍት:ዘገሬብ ላይ የተደረገው 8ኛው ጉ
ባዔ ደግሞ ይህንኑ የትግል ምዕራፍ በመከተል የረቮሉሽናዊ
ዓላማውን መሠረት አጥብቆ ይዘቱን በስፋቱም ሆነ በጥልቀቱ
በይበልጥ አስፋፋው::በዚህ ጉባዔ ላይ የኢትዮጵያ ኅብረተ
ሰብ መደቦች ተዘርዝረው ወገንና ጠላት ተለየ::"የሕዝባዊ
ት ኢትዮጵያ" ፖለቲካዊ:ኢኮኖሚያዊና ሕብረተሰባዊ አቋም
በደንብ ተዘረዘረ::ይህ ጉባዔ የተለመውን ዓላማ ጥልቀትና
ያቀደውን የትግል ጉዳና ትክክለኛነት ለመገንዘብ ያሳለፋቸ
ውን ውሳኔዎች መመልከት ይበቃል::



የ8ኛው ዓመታዊ ጉባዔ ውሳኔዎች:—

1 ፊውዳሉን መንግሥት ከነበላይ ጠባቂው ከነኢምፔሪያ
ሊዝም በሕዝባዊ ትግልና ጦርነት ከሀገር ደምስስ
ድምጥማጡን ማጥፋት

2 በፊውዳሊዝምና በኢምፔሪያሊዝም መቃብር ላይ በላብ
አደሩ ጥቅም ላይ የተመሠረተ ሕዝባዊ መንግሥት ማ
ቋቋም::

ከውሳኔዎቹ ከተል አርጉ ሕዝባዊ ጦርነት ለማድረግ አ
ንድ የወደፊት ተራማጅ ድርጅት ማቋቋም አስፈላጊ መሆኑን
ከጠቀስ በኋላ የኛ የተማሪዎች ተግባር ከሕዝቡ — ከሠራተ
ኛውና ከገበሬው — ጋር መዋሀድ መሆኑን በጥብቅ ያሳስባል

እዚህ ላይ:ርቀን ከመሔዳችን በፊት:አንድ ሁለት ነጥ
ቦችን ለማብራራት እንወዳለን::

ኢትዮጵያ ድሃና የኢኮኖሚ ዕድገቷ የተዛባ መሆኗን:የ
ኢትዮጵያ ሕዝብ ከልክ በላይ የተጉሳቆለ መሆኑን ሁላችን
እናምናለን::ይህን የማይቀበል — ዓይናቸውን ጥቅም ከዘጋ
ው አድሃሪዎች በስተቀር — አለ ብለን አንገምትም::ኢትዮ
ጵያ በውጭ አገር ኃይል የተጠቃች መሆኗንም የሚቀበለው አ
ንደዚሁ ብዙ ነው::አገራችንም ከዚህ ሁኔታ እንድትላቀቅ
ከሞላ ጉደል የሁሉ ምኞት ነው::ልዩነት የሚመጣው "ማላቀ
ቂያው" ዘዴ ላይ ነው::

8ኛው ጉባዔ መንገዱን — ዘዴውን — ቁልጭ አድርጎ
አሳይቶናል::"ወደፊት መገስገስ የሚቻለው:ፍትህ የሚገኘው:
ዲሞክራሲ የሚነግሠው ..." ያሁኑ አገዛዝ ከበላይ ጠባ
ቂው ከኢምፔሪያሊዝም ጋር በሕዝባዊ የጦር ኃይል ከተገለበ
ጠና በቦታው የሕዝቡን ጥቅም የሚጠብቅ "ሕዝባዊ መንግሥት"
ከተቋቋመ በኋላ ነው::

አድሃሪዎች በመጥላት፣ወሊዋዮች በመፍራት በዚህ ትክክለኛ አቋም ላይ ልዩ ልዩ ወቀሳ ያቀርባሉ። የሚቀርቡት ወቀሳዎች ላይ ላዩን ቢያዩዋቸው ገንቢ ይመስላሉ፤ጠለቅ ብለው ሲመረምሯቸው ግን አፍራሽ መሆናቸውን ለመረዳት ብዙ አያዳግትም።

አንዳንዶች፣ጠላቶቻችን ኃይለኞች ስለሆኑ በጦር ማሸነፍ አይቻልምና ሌላ ዘዴ(!) ይላሉ። የተፈለገው ግብ በሌላ ዘዴ የሚደረስ ቢሆን ኖሮ ጥሩ ምክር ነበር። ግን "ግባችን" በሌላ በምንም ዘዴ እንደማይደረስበት ተደጋግሞ ተብራርቷል። አንደገና አንመለስበትም።

ይህን ምክር አቅራቢዎች ያልተገነዘቡት አንድ መሠረታዊ ነገር አለ። የፊውዳሉም ሥርዓት ሆነ ኢምፔሪያሊዝም "አርጅተዋል"። እንግዲህ ወዲህ መቀነስ እንጂ መጠመር አይችሉም። የፊውዳሉ ሥርዓት በብዙ ቅራኔዎችና ችግሮች ተወጥሮ ተይዞ መንቀሳቀሻ አጥቷል። አሁን የሚፍጨረጨረው የመውደቂያ ቀኑን ለማራዘም ብቻ ነው። ቅራኔዎች እየጠነከሩ፣ ችግሮች እየተባባሱ እንጂ እየተሻሻሉ ሊሔዱ አይችሉም።

ኢምፔሪያሊዝም በበኩሉ በውስጥም ሆነ በውጭ ተወጥሮ ተይዞአል። በውስጥ የጥቁር ነስሳዎች ድርጅትና እንዲሁም የሌሎች ወደፊት ተራማጅ ድርጅቶች ትግል እየተፋፋመ በመሔድ ላይ ነው። በውጭ የደቡብ ምሥራቅ እስያ ሕዝቦች ትግል መንቀሳቀሻ አሳጥቶታል። የደቡብ አሜሪካ ትግል ገና መጀመሩ እንጂ መደምደሙ አይደለም። በዓለም በሙሉ የኢምፔሪያሊዝምን — በተለይ ያሜሪካ ኢምፔሪያሊዝምን — ኃይል ለነፃነት፣ለዲሞክራሲና ለሰላም የሚዋጉ ኃይሎች መፈናፈኛ አሳጥተውታል። የኢምፔሪያሊዝም ኃይል እንደገበይ ካብ በመናድ ላይ ነው። ተዳክሞአል፤አያስፈራም።

አንዳንዶች ደግሞ ጦርነት መጀመር ደም ማፋሰስ ነው፤



ሕዝቡን ማበጣበጥ ነው ይሉናል። ለማን ይሆን ይህን የሚሉት? ለኢትዮጵያ ሕዝብ? ለማያውቅሽ ታጠኚ ይላል ያገር ተረት።

ዛሬ ይህን ተናገረሀል፤በዚህ ሥራ ተጠርጥረሀል፤... እየተባለ በየስር ቤቱ የሚወረወረው፣ሰውነቱ የሚከለሰው፣በየጓዳውና በየጓሮው የሚገደለው፣በየጉዳናው የሚረሸነው፣በቦምብ የሚደበደበውና ጋዝ የሚጣልበት በርካት ያለ ሕዝብ ነው። ይህ ደም ማፍሰስ አይደለምን?

ዛሬ በኢትዮጵያችን ውስጥ ከገበሬውና ከሠራተኛው የሚወለዱ ሕጻናት በጥቃቅን በሽታ ምክንያት በየምድጃው ስር ወድቀው ሲቀሩ የገዢዎቻችን ቤተሰቦች ግን ለመውለድ ከገበሬውና ከሠራተኛው በሚዘርፉት ገንዘብ ተሰፍረው ወደባሕር ማዶ ይበራሉ። ይህ ደም ማፍሰስ አይደለምን?

ዛሬ ሕዝባችን በሳል፣በወፍ በሽታ፣በወባ፣በተስቦ... ተሣሥሮ በሚማቀቅበት ጊዜ ምንም ሳይደረግለት የገዢዎቻችን ቤተሰቦች ለድካምና ለራስ ምታት በሕዝቡ ገንዘብ በተሠሩት ሀኪም ቤቶች ውስጥ አረፍት ያደርጋሉ። ይህስ ደም ማፍሰስ አይደለም?

ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንጀራ በቆሎና በደረቅ ጭብጦ አሯል። በምግብ እጦት ምክንያት ሰውነቱ መንምኗል፤ዕድሜው ይቀጫል። የገዢ ቤተሰቦቻችን ግን ምግብ ከምግብ እያማረጡ ይበላሉ። ውፍረት አያስቸገራቸው መርፌ ይወጋሉ። የሚበሉት ቅባት የደም ስራቸውን እየዘጋው የተለየ ሕክምና ያደርጋሉ ይህ ሁሉ የሚደረገው ከሕዝቡ በሚዘረፈው ገንዘብ ነው። ይህ ማፍሰስ አይደለምን?

ደም ማፍሰስ ማለት ነፍስ መግደል ከሆነ የኢትዮጵያ ሕዝብ ነፍስ ለብዙ ዓመታት፣ከሚደርስበት ስቃይ የተነሣ፣በ

ያለበት እንደዝንብ ረገፍአል፣አሁንም በመርገፍ ላይ ነው::
ታዲያ አሁን "የደም መፍሰስን" ለምን እንፈራለን::

እርግጥ የኢትዮጵያ ሕዝብ በከንቱ ደም ማፍሰስን አይ
ይፈልግም::ግን በገፍ የሚፈሰውን ደም ለዘለዓለም ለማቆም
ና ጭቆናን ለማቆም ሲል ደም ማፍሰስ ካለበት:ይህንን ግዳ
ጅ ያለአንዳች ግዴታ መቀበልና መፈጸም አለበት::ደም ካል
ፈሰሰ(!) ሥርየት የለም::

አገረመንገዳችንን ወጥተን ከዋናው አርእስታችን ራቅ
አልን መሰል::እንመለስ::

በዘገረብ የተደረገውን የ8ኛውን ጉባዔ ውጤት አየን::
የሚቀጥለው ጉባዔ ሉንድ ላይ ተደረገ::ይህ ጉባዔ የ8ኛው
ን ጉባዔ ውጤት ሙሉ በሙሉ የተቀበለ ሲሆን:በተጨማሪ ለው
ሳኔዎች ሰፊ መሠረት ለመስጠት የኢትዮጵያን ሶሺዮ ኢኮኖሚ
አቋም በዝርዝር አጠና::8ኛው ጉባዔ ሳስተላለፋቸው ውሳኔ
ዎች ተጨማሪ መረጃዎችንና ማብራሪያዎችን አቀረበ::የተማሪ
ዎች ጊዜያዊ ምን መሆን እንዳለበት አመልክቶ የአጭርና የ
ረጅም ጊዜ ፕሮግራም ለመንደፍ ቻለ::

በጭሩ ማኅበራችን እስከዛሬ የተጓዘው የትግል ጎዳና
ይህ ሲሆን በበርሊን የተደረገው:10ኛው ዓመታዊ ጉባዔ የ
ዚሁ ትግል ውጤት ነው::

10ኛው ጠቅላላ ጉባዔ "ምን ዓይነት ለውጥ:ለኢትዮጵ
ያ?"በሚል አርእስት ተወያየ::የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ወደኋ
ላ መቅረት:የሰፊውን ሕዝብ ችግርና ሥቃይ:የጥቂቶችን መን
ደላቀቅ:የባዕዳን ኃይሎችን በአገሪቱ ውስጥ መፈንጨት በአ
ዲስ መረጃዎች ጭምር እንደገና አረጋገጠ::በዚህ ላይ በመ
መርኮዝ ሰፊው ሕዝብ ከችግር:ከድንቁርና:ከበሽታ ሊላቀቅ
የሚችለው:የአገሪቱ ኢኮኖሚ ሲደራጅ የሚችለው:አገሪቱ ብሔ



ራዊ ነፃነቷን መጎናፀፍ የምትችለው በመሠረታዊ ለውጥ ብቻ
መሆኑን ዘርዝሮ ገለጠ::

ይህንን መሠረታዊ ለውጥ ለማምጣት ባላባታዊው መንግሥ
ትና የበላይ ጠባቂው የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም በሕዝባዊ ጦ
ርነት መሸነፍ እንዳለባቸው እንደገና አረጋገጠ::ይህ ሕዝ
ባዊ ጦርነት በሚወለደው ድል ላይ "ሕዝባዊ መንግሥት" መ
ቋቋም እንዳለበት ገልጾ ይህም ሕዝባዊ መንግሥት ሊይዝ የ
ሚገባውን የፖለቲካ:የኢኮኖሚና የሶሺል መስመሮችና የዕድገ
ት ዋና ዋና መልኮች ተንትኖ አቀረበ::

የበርሊኑ ጉባዔ — 10ኛው ጉባዔ — የባላባታዊው መ
ንግሥትና የበላይ ጠባቂው የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ብዝበዛ
ና ጭቆና ያንገፈገፋቸውን የኅብረተሰብ መደቦችና ክፍሎች
የሚጠቀልል ሰፊ ፀረኢምፔሪያሊስትና ፀረፊውዳል የትግል ድ
ርጅት መቋቋም አስፈላጊነት በሙሉ ልብ ተቀበለ::

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር የደረሰበት ሬ
ቮሉሽናዊ ደረጃ የተገኘው:እንዲያው:ከብዙ ትግልና ጥረት
በኋላ ነው::ከተበታተኑ ማኅበሮች ወደ አንድ የተጠቃለለው:
ከደካማነት ወደ ጠንካራ ድርጅት የተዛወረው:አድሃሪ ኃይሎ
ችን አሸንፎ ሬቮሉሽናዊ አቋምን ያገኘው በአንድ ሌሊት ወ
ይም በጥቂት ሰዎች ምኞት አይደለም::አድሃሪና ወደፊት ተ
ራማጅ ኃይሎች ለረጅም ጊዜ ያደረጉት ትግል ውጤት ነው::

ማኅበራችን ይህንን ሬቮሉሽናዊ አቋም በአሥር ዓመታት
ውስጥ ደርሶበታል::ነገር ግን የማኅበሩ ዓላማ ነፃና ሕዝ
ባዊት ኢትዮጵያ እንድትቋቋም ሲሆን ይህንን ከፍጻሜ ለማድ
ረስ ወደፊት ያለው ትግል መራራ:ረጅምና ከፍ ያለ እንደሚ
ሆን መዘንጋት የለበትም::

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከሚጠቁትና ከሚበዘብዙት ጠላቶች —

በኃይለሥላሴ ከሚመራው ባላባታዊ መንግሥትና ከበላይ ጠባቂው ከአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም — ጋር ለመታገል ድርጅት ያስፈልገዋል:: ዛሬ እነዚህን ጠላቶች በመታገል ላይ ያሉት ሕዝቦችና የሕዝብ ድርጅቶች በትግል በመዋሀዱና በመተሣሠር ይህን ረቮሉሽናዊ የትግል ድርጅት አንድ ቀን መፍጠራቸው እንደማይቀር ቢታወቅ ወደፊት የሆኑ ቀዳሚ ተግባር ይኸንን ቀን ለማፋጠን ያለማቋረጥ መታገል ነው:: ለዚህ ተግባር የተማሪዎች ትግል ዕድገትና አሥረኛው ጉባዔ አበረታች ምሳሌና ትምህርት ሊሆኑን ይገባል::

እንታገል(!) እናሸንፋለን::

የሰፊው ሕዝብ ትግል ያሸንፋል!

የፊውዳሉ ሥርዓትና ኢምፔሪያሊዝም ይውደም!



## <u>የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴው ሪፖርት</u>

በሊቀ መንበሩ አማካይነት የቀረበ

ወንድሞችና እህቶች፣ወዳጆች

በዚህ በአሥረኛው ጠቅላላ ጉባዔያችን ላይ ካለፉት ጥቂት ዓመታት ይበልጥ በርከት ያሉ ተሳታፊዎች መገኘታቸው ማኅበራችን ከጥቂት ዓመታት ወዲህ በወሰደው ረቮሉሽናዊ መስመር እያደገ መሔዱን የሚያረጋግጥ ነው:: ያውሮፓው ማኅበራችንም ሆነ ሌሎቹ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበራት ረቮሉሽናዊ ሆነው አልተወለዱም:: ረቮሉሽናዊ የሆኑት በአድሃሪና በረቮሉሽናዊ ርዕዮተዓለሞች መካከል ከተደረገው ረጅም ትግል በኋላ ነው::

ዛሬ በረቮሉሽናዊ ትግላችን የደረስንበት ከፍተኛ ደረጃ አድሃሪው ፊውዳሉ መንግሥትና የበላይ ጠባቂው የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ፀረሕዝብና ፋሽታዊ የሆነውን ዕውነተኛ ጉዳቸውን በይፋ እንዲገልጹ አስገድዷቸዋል:: ባለፉት ሁለት ዓመታት ብቻ አገር ቤት በሚገኙት የትግል ጓደኞቻችን ላይ ያወረደው የእሥራትና የግርፋት መአት፣እልቂት አድሃሪው መንግሥት እንደተርበደበደ በግልጽ ያሳያሉ:: ምክንያቱም ግልጽ ነው:: የኢትዮጵያ ተማሪዎች የሚከተሉት ረቮሉሽናዊ ዓላማ የሕዝቡን ፍላጎትና ምኞት በትክክል እንደሚገልጽ በደንብ ስለሚያውቅ ነው::

ታህሣሥ 20 ቀን፣1962 የገንበር ቀደሙ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ማኅበር ፕሬዚዴንት፣ወንድማችን ጥላሁን ግዛው፣በመንግሥቱ የነፍስ ገዳይ ጓድ ተገደለ:: በማግስቱና በሚቀጥሉት ቀናት ከ50 የሚበልጡ ተማሪዎች እየታደኑ ተረሸኑ:: አድሃሪው መንግሥትና የበላይ ጠባቂዎቹ በዚህ ዓይነቱ ድርጊት በሕዝቡ ዘንድ እየተፋፋመ የሚሔደውን የረቮሉሽን ማዕበል ለመግደልና ለማገድ የሚችሉ ይመስላቸዋል:: እንደዚህ ዓይነቱ የአረመኔ ተግባር ቆራጥነታችንን ያ

ጠንክረዋል እንጂ ምን ጊዜም ትግላችንን ሊያበርደው ወይም ሊያደክመው አይችልም::

ትግላችን ያለምክንያት ከየትም የፈለቀ አይደለም::የተማሪዎች ትግል የፈለቀውና የሚዳብረው በዓለም ላይ — በኢምፔሪያሊዝምና በተበዝባዥ አገሮች መካከል — ካሉት ቅራኒዎችና ባገራችን ውስጥ በአድሃሪና በተራማጅ ኃይሎች መካከል ባሉት ቅራኒዎች መፋፋም የተነሣ ነው::እነዚህ ቅራኒዎች ትክክለኛ መፍትሔያቸውን እስካገኙ ድረስ የረቮሉሽኑ እሳት ሊወድም አይችልም::

የዓለምን ሁኔታ ዛሬ ዓይነተኛ የሚያደርገው በተበዝባዥ ዓለም —አፍሪካ፡እስያና ደቡብ አሜሪካ— እና በአሜሪካ በሚመራው የዓለም ኢምፔሪያሊዝም መካከል በልዩ ልዩ መልክ የሚካሄደው ትግል ነው::

አሁን ደርጅተውና ጠንክረው የሚገኙት ኢምፔሪያሊስት አገሮች እዚህ ደረጃ የደረሱት ለብዙ መቶ ዓመታት ከተበዝባዥ ሕዝቦችና አገሮች በዘረፉት ሀብትና ጉልበት ነው::እነዚህ ተበዝባዥ አገሮች ዛሬም በኢምፔሪያሊዝም የጥቅም ክልል ውስጥ እንዲኖሩ ለማድረግ ይሞክራሉ::

በጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ የተያዙት አገሮች ኢኮኖሚ የሚቀየሰው ለብሔራዊ ዕድገት ሳይሆን ለኢምፔሪያሊስት አገሮች ጥቅምና ዕድገት እንዲውል ታስቦ ነው::እነዚህን ተበዝባዥ አገሮች እንደድሮው በቀጥታ መግዛትና ማስተዳደር አይቻልም፣አያስፈልግምም::ነገር ግን ለዚሁ ተግባር በተመለሉና በተዘጋጁ 'የአገሬው' ወኪሎች አማካይነት ብዝበዛው ይቀጥላል::

በተበዝባዥ አገሮች የሚገኙት ዋና ዋና የማዕድንና የሌሎችም ጥሬ ዕቃ ምንጮች በሙሉ የተያዙት በኢምፔሪያሊስቶ



ች ነው::ከነዚህ ምንጮች የሚገኙት ሀብቶች ሁሉ — ማዕድን፣ሰብል... — የትላልቅ ኢምፔሪያሊስት ከበርቴዎችን ፋብሪካዎች ለመመገብና ለማዳበር ወደ ኢምፔሪያሊስት አገሮች ይጋዛሉ::

የጅ አዙር ቅኝ ግዛቶች የውጭ ንግድ ከኢምፔሪያሊስት አገሮች ጋር የተሳሰረ ከመሆኑም በላይ አንድ ወይንም ሁለት ሸቀጦችን በመሸጥ ላይ ብቻ የተመሠረተ ነው::በዚህ የዓለም ገበያ ላይ በሚደረገው ለውጥ ጥሬ ዕቃ የሚሸጡት አገሮች ለሸቀጣቸው የሚያገኙት ዋጋ እየቀነሰ ሲሔድ የኢፔሪያሊስት አገሮች የሚሸጧቸው ሸቀጦች ዋጋ እየጨመረ ይሔዳል::ከዚህ የተዛባ ለውጥ የተነሣ ተበዝባዥ አገሮች በየዓመቱ የሚገፈፉት ገንዘብ በቀላሉ የሚገመት አይደለም::በተጨማሪ ኢምፔሪያሊስቶች በተበዝባዥ አገሮች ውስጥ እንዳንዱ ቀላል እንዱስትሪዎችን በመክፈት በነዚህ አገሮች የሚገኙትን የሰው ልጅ ጉልበት በሚያስቀቅ አኳኋን ይጠቀሙበታል

እንደዚህ ያለው የኢኮኖሚ ግንኙነት ተበዝባዥ አገሮችን የኢምፔሪያሊስቶች የፖለቲካ ጥገኛ ጭምር አድርጓቸዋል:: የተበዝባዥ አገሮች ገዥ መደቦች፣ከፍ ብለን እንዳየነው፣ ለካፒታሊስት ታላላቅ ከበርቴዎች የኢኮኖሚ ጥገኛ በመሆን አገሮቻቸውን ጭምር ለጅ አዙር ቅኝ ተገዥነት አሳልፈው ሰጥተዋል::በዚህ አኳኋን ኢምፔሪያሊስት አገሮች ተበዝባዥ አገሮችን አጥብቀው ለመያዝ ችለዋል::በብዙ አገሮችም የጦር ኃይል በማከማቸት ጥቅማቸውን ይጠብቃሉ::ለብሔራዊ ዕድገት የሚታገሉ መሪዎች በተነሱ ቁጥር ከሥልጣን ሲያስወግዷቸው በየጊዜው ሤራ ሲመቱ ይታያሉ::

ከዚህም በላይ ኢምፔሪያሊስቶች የበሰበሰ ባሕላቸውን ለማሠራጨት ከፍ ያለ የባሕል ወረራ ያደርጋሉ::ዓለምን በነሱ አምሳል የተፈጠረ በማስመሰል የሌሎችን አገሮችና ሕዝቦች ታሪካዊ ዕድገት እንዳልነበረ ለማድረግ ወይንም ለመቀ

የር ይሞክራሉ::ዕድል በገጠማቸው ቁጥር የሕዝቦችንና የመ
ደቦችን ታጋይ መንፈስ ለመስበርና የተገዥነት ጠባይ እንዲ
ስፋፉ ለማድረግ ይጥራሉ::

ከሁለተኛው የኢምፔሪያሊስት ጦርነት ወዲህ ብዙ ሕዝበ
ዊ መንግሥታት መቋቋማቸው ኢምፔሪያሊዝምን አድክሞታል::ይ
ህን በመገንዘብ ኢምፔሪያሊስቶች እነዚህን የሕዝበዊ መንግ
ሥታት አገሮች ለመጠቀምና ቢቻላቸውም በቀጥታ ለመውረር ይ
መኛሉ::ለዚህ ዓላማ የጁ አዘዞር ቀኝ አገሮችን ለጦር ወረ
ራ ምሽጎች አድርገዋቸዋል::

የተበዘበዙ ዓለም ሕዝቦች የኢኮኖሚ፣የፖለቲካና የባህ
ል ጭቆና አስመርሯቸው ለነፃነት ይታገላሉ::ኢምፔሪያሊስቶ
ችም፣ይህ ትግል በሞት አፋፍ ላይእንደጣላቸው በመረዳት፣የ
ዕውር ድንብራቸውን ቢፍጨረጨሩና ቢቀጉ ይታያሉ::

በተበዘበዙ አገሮች ፀረኢምሬያሊስት ትግል ውስጥ የጀ
ግናው የቪየትናም ሕዝብ ትግል ከፍተኛውን ደረጃ ይዞ ይገ
ኛል::የቪየትናም ሕዝብ የፈረንሣይን ኮሎኒያሊዝምና የጃፓ
ንን ወረራ ተቃግቶ በጦር ሜዳ ላይ አሸንፎአል::እነዚህ
ሁለት ቀንዳም ወራሪዎች ድል ከሆኑ በኋላ የአሜሪካን ኢም
ፔሪያሊዝም የቪየትናምን ደቡብ ክፍል ቆርሶ የራሱ ቀኝ ገ
ዛት ሊያደርገው ሞከረ::የ1954ን — እንደአውሮፓ አቆጣ
ጠር — የጀኔቭ ስምምነት በመጣስ ቪየትናምን በጦር ኃይል
ወረረት::ነገር ግን ጀግናው የቪየትናም ሕዝብ ይህ ነው
በማይባል ጀግንነትና ቆራጥነት 600000 የአሜሪካን ወራ
ሪ ወታደሮችና ከሚሊዮን የሚበልጡ የአሸንጉሊት አገሮችን
ወታደሮች በመቋቋም በጦር ሜዳ ሆነ በፖለቲካ ሸንጎ ድልን
እየተጐናፀፈ ነው::የአሜሪካ ኢምፔሪያሊስቶች የሚለፍፉት
ቪየትናማዊያንን በቪየትናማዊያን የማጋደል —"የቪየትናማይ
ዜሽን"— ፖለቲካ ከሸፍባቸው ይታያል::

በካምቦዲያ ለብዙ ጊዜ ገለልተኛ ለመሆን ይሞክር የነ



በረው የኖሮደም ሲያኑክ መንግሥት በአሜሪካን ኢምፔሪያሊስ
ቶች ሤራ ተገልብጦ ለኢምፔሪያሊስቶች አገልጋይ የሆነ አገ
ዛዝ ሠፈረ::ይህ አልበቃ ብሎ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊስቶች
ካምቦዲያን በጦር ኃይል ወረሯት::ይህ ወረራ ያሜሪካ ኢም
ፔሪያሊዝምን ወንበዴነት በይፋ ከማጋለጡም በላይ የካምቦዲ
ያን ሕዝብ በያለበት በወራሪዎቹ በአሜሪካ ወታደሮችና በ
ብሔራዊ አድሃሪ ኃይሎች ላይ በቁጣ እንዲነሣ አድርጓታል::

በላኦስ የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም የሚያደርገውን ወረራ
ለመከላከል የሕዝቡ ትግል እያደገ ይሔዳል::

ዛሬ የቪየትናም፣የላኦስና የካምቦዲያ ሕዝቦች የአሜሪ
ካ ኢምፔሪያሊዝምንና ብሔራዊ ቡችሎችን በመቋቋም ከምንም
ጊዜ ይበልጥ አንድነታቸውን አጠንክረዋል::ትግላቸው በቀር
ቡ የመጨረሻ ድልን እንደሚጐናፀፍ አይጠረጠርም::

በምዕራብ እስያ ጽዮናዊያን ከኢምፔሪያሊዝም ጋር በመ
ተባበር 3 ሚሊዮን የሚሆኑ ፍልስጥኤማዊያንን ከገራቸው ከ
ፍልስጥኤም ካባረሯቸው ከሃያ ዓመት ይበልጣል::አሁን ባለ
ንበት ጊዜ እየጠነከሩ የሚሔዱትን — በተለይ በብዙዎቹ በ
አረብ አገሮች ላይ ከተደረገው ከትልቁ ወረራ ወዲህ — የ
ፍልስጥኤም የነፃነት ተቀጊዎች ለማጥፋት ኢምፔሪያሊስቶችና
ጽዮናዊያን በመዶለትና ትልቅ ሤራ በመሥራት ላይ ናቸው::
የፍልስጥኤም ሕዝብ በተባበሩት መንግሥታት በሚደረገው ክር
ክር ወይንም ታላላቅ መንግሥታት በሚወስኗቸው አርምጃዎች
ነፃነቱን ያገኛል ማለት የህልም እንጀራ ነው::የአረብ አ
ድሃሪ ኃይሎች የሚወጥኑትን ተንኮል ሁሉ አጋልጦ ከኢምፔሪ
ያሊዝምና ከጽዮኒዝም ጋር እስከ መጨረሻው በጦር ኃይል ከ
መታገል በስተቀር ድልን ለመጐናፀፍ ሌላ የሚያዋጣ መንገድ
የለም::

በአፍሪካ የፖርቱጋልን ኢምፔሪያሊዝም በመቃወም በሞዛ

ምቢክ፣በአንጎላና በጊኒ—ቢሳው የሚደረገው ሕዝባዊ ትግል
እየጠነከረ ይሔዳል::በዚምባብዌ፣በአዛኒያ፣በደቡብ አፍሪካ
የነፃነት ተዋጊዎች በትግል ሜዳ ላይ ተሰማርተዋል::

በሰሜን አሜሪካ የአፍሮ አሜሪካዊያን ትግል ተፋፍሞአ
ል::የጥቁር ገሥላ የትግል ድርጅት ከተቋቋመ ወዲህ ትግሉ
ረቮሉሽናዊ መሥመር ይዞአል::ያሜሪካን ትላልቅ ከበርቴዎች
ወኪል የሆነው የኒክሰን መንግሥት የዚህን ድርጅት መሪዎች
እያደነ በማሰርና በመግደል ትግሉን ያበረደ ይመስለዋል::ይ
ህ ገን መሠረት የሌለው ተስፋ ነው::

በጭቁኑ፣በመላው ዓለም በተጨቆኑት ሕዝቦችና በኢምፔሪያ
ሊዝም መካከል የከረረ ትግል በማካሄዱ ላይ ነው::በዚህ
ትግል ለነፃነት፣ለዲሞክራሲና ለወደፊት እርምጃ የሚዋጉት
ኃይሎች እየጠነከሩ ሲሔዱ የኢምፔሪያሊዝም ዓለም—አቀፍ ኃ
ይል እየቀነሰ ሲሔድ እናያለን::

<u>የኢትዮጵያ ሁኔታ</u>

በገራችን በኢትዮጵያ ያሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ከብሔራዊ
አድሃሪ ኃይሎች — ከታላላቅ ባላባቶችና ከታላላቅ በለሥል
ጣኖች — ጋር በመተባበር አገራችንን የጅ አዙር ቅኝ ገዘ
ት አድርጓታል::ዛሬ በገራችን ተስፋፍተውና አይለው የሚገ
ኙት ኢምፔሪያሊዝምና ፊውዳሊዝም ለሕዝባችን መሰቃየትና መ
ጉብቀል ዋና ምክንያቶች ናቸው::

ኢትዮጵያ ሰፊ የተፈጥሮ ሀብት ያላት አገር መሆኗ የ
ታወቀ ነው::ነገርግን የሕዝቧ የኑሮ ደረጃ ከዓለም ሕዝቦች
ሁሉ ዝቅተኛ ሆኖ ይገኛል::ባንዱ በኩል ፊውዳሊዝም፣በሌላ
በኩል ኢምፔሪያሊዝም ያገሪቱን ኢኮኖሚ እንዳይዳብር አፍነ
ው ይዘውታል::



ከሕዝቡ 90 በመቶው በገብርና የሚተዳደር ነው::ከገ
በሬዎች ከ70 በመቶ የማያንሱት መሬት ስለሌላቸው ጭጥራቸ
ው ኢምንት ለሆነ ሥራ ፈት መሸገሮች በጢሰኛነት ወይም
በገባርነት ያገለግላሉ::እነዚህ በጣት የሚቆጠሩ ዘራፊዎች
— ንጉሡና ቤተሰቡ፣ከፍተኛ የአስተዳደርና የጦር ኃይሎች፣
ታላላቅ ባላባቶችና ታላላቅ የቤተክህነት መሪዎች — ከሚታ
ረሰው መሬት ከ75 በመቶ የሚበልጠውን ርስት፣ጉልት፣ሁዳዴ
ወዘተ.... እያሉ ይዘውታል::እነሱው ያወጡት ሕገ ጢሰኛ
ው ገበሬ ከሚያፈራው ምርት እስከ 75 በመቶ ድረስ እንዲ
ወስዱ ይፈቅድላቸዋል::በነዚህ ዘራፊዎች፣ለነዚሁ ዘራፊዎች
ጥቅም መጠበቂያ፣የተቋቋመው የፊውዳል መንግሥት በተጨማሪ
የገቢ ቀረጥ፣የ'ትምህርት' ታክስ፣የ 'ጤና' ታክስ እያለ የ
ተረፈችውን ይወስድበታል::በዚህ ዓይነት የሚዘረፈውና የሚ
በዘበዘው ገበሬ እንኳንስ እርሻውን ለማሻሻያ ትርፍ ሊያገ
ኝ ይቅርና ራሱንና ቤተሰቡን በሕይወት ለማቆየት እንኳ ያ
ዳግተዋል::በዚህ ሁኔታ ብዙዎች በረሃብ ሲያልቁ ሌሎች ሥ
ራ ፍለጋ ወደ ከተማ ይጎርፋሉ::በቆረቆዘው ኢኮኖሚ ውስጥ
ሥራ ስለማይገኝ ወደከተማ የጎረፉትም እዚያው ያልቃሉ ወይ
ንም ለማኝና ቤት አዳሪ ሆነው ይንገላታሉ::

ባገራችን የሀብት ዋና ምንጭ የሆነው ገብርና በዚህ ዓይነ
ት በፊውዳል ሥርዓት እንዳይዳብር ታፍኖ ተይዞአል::በሌላ
በኩል ኢምፔሪያሊስቶች አገራችንን — እንደሌላ ተበዝባዥ
አገር ሁሉ — እነሱ የሚፈልጓቸውን ጥሬ ሸቀጥ አቀባይና
አላቂ የንግድ ሸቀጦቻቸውን ማራገፊያ አድርገዋታል::

ድሮ የሕዝቡን ፍላጎት በመጠኑ ያረኩ የነበሩት የጁ
ጥበብ ሠራተኞች — ሸማኔዎች፣ቀጥቃጮች፣አንጣሪዎች... —
እና ነጋዴዎች ዛሬ ከሰረው በገራችን የሚገኙት የኢንዱስት
ሪና የንግድ ድርጅቶች በኢምፔሪያሊስቶች፣በተለይም በአሜሪ
ካ ኢምፔሪያሊስቶች፣ተይዘዋል::እነዚህ ባዕዳን ዘራፊዎች
ለሠራተኛው በሕይወት ቆሞ እንዲሔድ የምታስችለውን ያህል

ብቻ ደመወዝ እየከፈሉ የሠራውን ዋጋ ይዘርፉታል፡፡ፊውዳሉ መንግሥት ኢምፔሪያሊስቶች በተመቻቸው መንገድ ብዝበዛቸውን እንዲያካሒዱ በሩን በሰፊው ከፍቶላቸዋል፡፡ፊውዳሉ መንግሥት በሚያወጣቸው ልዩ ልዩ ሕግጋት ሠራተኛውን አፍኖ አገሩን አሥሮ ለካፒታሊስት ዘራፊዎች አሳልፎ ሰጥቶታል፡፡

የኢትዮጵያ የውጭ ንግድ የተመሠረተው አንድ ሸቀጥ — ቡና — ወደውጭ — በተለይ ወደአሜሪካ — በመሸጥ ላይ ቢሆን ይህ ሁኔታ የአሜሪካ ኢምፔሪያሊስቶች አገራችንን የፖለቲካ ጥገኛቸው እንዲያደርጒት መንገድ ከፍቶላቸዋል፡፡ይህ ብቻ ባይሆን ያሜሪካ ኢምፔሪያሊስቶች ዛሬ ያገሪቷን የውስጥና የውጭ ፖለቲካ በጃቸው አስገብተዋል፡፡ያሜሪካ ኢምፔሪያሊዝምና የእሥራኤል ጽዮኒዝም አገራችንን በምዕራብ እስያ ለሚያደርጉት ወረራና ለመላው አፍሪካ ለሚወጥኑት ፀረረቮሉሽናዊ ተግባራቸው የምታገለግል የጦር ምሽግ አድርገዋታል፡፡

ከላይ የተጠቀሱት ሁኔታዎች ኢምፔሪያሊዝምና ፊውዳሊዝም የሕዝቡ ዋና ጠላቶች መሆናቸውን ያሳያሉ፡፡እነዚህ ሁለት ኃይሎች በሕዝባዊ ኃይሎች ካልተደመሰሱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዛሬ ከሚሰቃይበት የድህነት፣የድንቁርናና የበሽታ ማጥ ሊወጣ አይችልም፡፡እየተፋፋመ የሚሔደው የገበሬ፣የሠራተኛና የተማሪ ትግል ለዚህ መሪ ሀሳብ ትክክለኛነት ዋና ምስክር ነው፡፡

ከብዙ ዓመታት ጀምሮ በኤርትራ ውስጥ ሕዝባዊ ትግል እንደሚካሔድ ማንም ያውቀዋል፡፡እንደዚሁም በባሌ ሕዝቡ ከብዙ ዓመታት ጀምሮ ካድሃሪው መንግሥት ጋር ይታገላል፡፡በቅርቡ በጐጃም ውስጥ አድሃሪው መንግሥት መሬት ይለካል በሚል ምክንያት በገበሬዎች ላይ ግብር ለመጨመርና የገበሬዎችን መሬት ለመንጠቅ ያደረገውን ሙከራ በመቃወም ሕዝቡ ጦሩን ይዞ ተነሣ፡፡በነዚህና በሌሎችም ቦታዎች በፊውዳሉ መንግሥት ላይ የተነሣሣው ሕዝብ ጭቆናና ብዝበዛ ስለመረረው



ነው፡፡አንዳንድ ጊዜ፣በንዳንድ ቦታዎች ትግሉ የነገድ ወይም የሃይማኖት ትግል መስሎ ቢታይ አድሃሪ ኃይሎች የዚህን ዓይነት ስሜት ለመቀስቀስና ለማጋነን ከሚያደርጉት ሙከራ የፈለቀ ነው፡፡

ኢትዮጵያ ብዙ ልዩ ልዩ ቋንቋዎች የሚነገሩበት፣ልዩ ልዩ ሃይማኖቶች የሚመለኩበት፣ሕዝቡ ልዩ ልዩ ባሕል የሚከተልበት አገር ናት፡፡ይህ ሁኔታ የበለጸገ ብሔራዊ ባህል ለማስገኘት ይጠቅማል እንጂ ሕዝቡን በወንድማማችነት ለመኖር የሚያግደው አይደለም፡፡ዛሬ ግን አድሃሪው መንግሥት አንዱን ሃይማኖት፣አንዱን ባሕል፣አንዱን ቋንቋ ብቻ በሕዝቡ ላይ በኃይል ለማስፈርና ሌሎችን ለመደምሰስ ይጣጣራል፡፡በዚህ ዘዴ በሕዝቡ መካከል የመጠላላትንና የመለያየትን መንፈስ ለመፍጠር ይሞክራል፡፡እንዲህ ያለው የከፋፍለህ—ግዛ ተግባር ግን እንደማያዋጣው የተረጋገጠ ነው፡፡ሕዝቡ በኅብረት የሚመራው ፀረፊውዳልና ፀረኢምፔሪያሊስት ትግል አንድነቱን ያረጋግጥለታል፡፡

የሠራተኛውን ትግል ደግሞ እንመልከት፡፡ምንም እንኳን የሠራተኛው መደብ አዲስና በቁጥርም አነስተኛ ቢሆን ካሁኑ የኢምፔሪያሊስቶችን ብዝበዛና የፊውዳሉን ሥርዓት ጭቆና በመቃወም ትግሉን ጀምሯል፡፡የሠራተኞች ማኅበራት መቋቋም የዚሁ ትግል ውጤት ነው፡፡በሁኑ ጊዜ ኢምፔሪያሊስቶች አንዳንድ አበሳ በይ የሠራተኛ ማኅበራት መሪዎችን በመደለል ብሔራዊውን የሠራተኛ ማኅበር እንደ I.C.F.T.U. ካሉ ፀረረቮሉሽናዊ የሠራተኛ ድርጅቶቻቸው ጋር አያይዘዋቸዋል፡፡የሆነ ሆኖ ተራው ሠራተኛ ምን ጊዜም ሊደለል አይችልም፡፡የሚገርፈው የችግር አለንጋ፣ጭቆናውና ብዝበዛው ፋታ የሚሰጥ አይደለምና፡፡ይኸንን ለመረዳት ሠራተኞች በየጊዜው "ደመወዝ ይጨመር፣የሠራተኞች መብት ይከበር" እያሉ በሰላማዊ ሰልፍና ሥራ በማቆም የሚያደርጉትን ትግል መመልከት ይበቃል

የኢትዮጵያ ተማሪዎች ትግል ን ብንመለከት የተማሪው

ትግል በገሪቱ ካለው ጠቅላላ ሁኔታ የመነጨ መሆኑን አንገ
ነዘበለን::የተማሪ ማኅበሮቻችን የማያወላውል ረቮሉሽናዊ
አቋም ከያዙ አንዱ አምስት ዓመት ሆኖአል::በዚህ ጊዜ ው
ስጥ በኢትዮጵያ በሰሜን አሜሪካና በአውሮፓ የሚገኙት ማኅ
በሮቻችን ትግላቸውን በኅብረት ሲያካሒዱ ቆይተዋል::ከከፍ
ተኛ ደረጃ የደረሰውን ትግል ለማቀናበር የዛሬ ሦስት ዓመ
ት ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር ተመሠረተ::

የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር ረቮሉሽናዊ ጎዳና ከመረ
ጡ ወዲህ በየጊዜው አያሌ የትግል አርምጃዎችን ወስደዋል::
ብዙም ድልን ተጐናጽፈዋል::በነዚህ አርምጃዎች ተማሪዎች
ከገበሬውና ከሠራተኛው ጎን መሠለፋቸውን አረጋግጠዋል::ፊ
ውዳሊዝምና ኢምፔሪያሊዝም የሚፈጽሙዋቸውን ወንጀሎች አጋል
ጠዋል::

የዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር ተግባር
በሚከተሉት መሪ ሀሳቦች ላይ የተመሠረተ ነው::

1 የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላቶች ፊውዳሊዝምና ኢምፔሪያሊ
ዝም ናቸው::

2 አነዚህ ጠላቶች ሊወገዱ የሚችሉት በሕዝባዊ የጦር
ትግል ብቻ ነው::

3 አንደዚህ ያለውን ሕዝባዊ ትግል ለማቀናበርና ለመ
ምራት ፀረፊውዳልና ፀረኢምፔሪያሊስት የሆነ የትግ
ል ድርጅት ያስፈልጋል::

4 የተማሪዎችና የምሁራን ተግባር ከገበሬውና ከሠራተ
ኛው ጎን ተሰልፎ የሕዝቡ ወገን የሚያሸንፍበትን
መንገድ መፈለግ ነው::

ይህ የዘንድሮው ዓመታዊ ጉባዔያችን አነዚሁኑ መሠረታ
ዊ ሀሳቦች የተከተለ ነው::



“ምን ዓይነት ለውጥ ለኢትዮጵያ” በሚል አርእስት በ
ምናደርገው ስሚናር ካለመሠረታዊ ለውጥ ሌላ ለኢትዮጵያ ሕ
ዝብ የሚያዋጣ ለውጥ አንደሌለ አንረዳለን::ይህ መሠረታዊ
ለውጥ አንዴት ሊመጣ አንደሚችል ጠልቀን አንመረምራለን::
በጥናታችን ኢምፔሪያሊስቶች ሊወጥኑ የሚችሉትን የፖለቲካ
ሽንገላአናጋልጣለን::

ይህ ጉባዔ ትግላችንን ወደፊት አንደሚያራምደው አይጠ
ረጠርም::

— ፊውዳሊዝም፣ኢምፔሪያሊዝምና አድሃሪ ኃይሎች ሁሉ
ይውደሙ::

— የኢትዮጵያ ሕዝብ ያሸንፋል::

— የኢትዮጵያ ተማሪዎች አንቅስቃሴ ለዘለዓለም
ይኑር::

## በ10ኛው ጉባዔ ላይ ከሰሜን አሜሪካ ሦስት ጓዶች ነበሩ

በዚህ ዓመቱ ጉባዔያችን ላይ ከሰሜን አሜሪካ ሦስት ጓዶች በሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበርን በመወከል በመሀከላችን ለመገኘት በመቻላቸው የተሰማን ደስታ ከፍተኛ ነው::በሰሜን አሜሪካ የሚገኙ ጓዶቻችን ወደዚህ ዓመታዊ ጉባዔ ያለማቋረጥ ወኪል ሲልኩ ሦስት ዓመት ሆኗል::ባለፉት ሁለት ዓመታት ሲልኩ የቻሉት አንዳንድ ወኪል ብቻ ነበር::አሁን ግን በአንድ ጊዜ ሦስት ጓዶች በመሀከላችን መገኘት መቻላቸው የሚያመለክተው የአንድነታችንን መጠንከር ብቻ ሳይሆን የማኅበሮቻችንንም እየደረጀ መሔዱ ጭምር ነው::

በኢትዮጵያ ያሉ ጓዶቻችንም የዚህ ጉባዔ ተሳታፊ ለመሆን በቻሉ ምን ያህል በተደሰትን ነበር::ግን የፋሽስቱ መንግሥት ጭቆና ለጊዜው ስላበቸገረና ሳንዳንዱ ቴክኒካዊ ፕሮብሌሞችም እንደዚሁ ለጊዜው መፍትሔ ማግኘት ስላልተቻለ በዚህ ዓመትም የትግላችን ጓዶች የዚህ ጉባዔ ተሳታፊ ለመሆን ሳይችሉ ቀርተዋል::ይህን እንቅፋት ለመወጣት እንጣጣራለን፤ በቅርቡም እንደምናሸንፍ ተስፋ አለን::

ከሰሜን አሜሪካ የተላኩት ጓዶቻችን — የሸረግ ሕይወት፤ ሰናይ ልኬ፤ ሐጐስ ገብረኢየሱስ — በየኮሚቴው ውስጥ እየተገኙ ስለትግላቸው፤ ስለችግራቸው፤ በየጊዜው ስለሚያገኙት ድል ... በሰፊው በማጫወት የሰጡን ትምህርት በጣም ጠቃሚ ቢሆን ሁሉንም በዚች አጭር መጽሔታችን ውስጥ ለማስፈር ባለመቻላችን አያዘንን ከመካከላቸው አንዱ — ሐጐስ ገብረየሱስ — በጉባዔው መክፈቻ ቀን ያሰማንን ነገር ከዚህ በታች ለአንባቢዎች እናቀርባለን::

## የጓድ ሐጐስ ንግግር

ጓዶችና እንግዶች፤

ከሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበርና ከዓለም አ



ቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ — እንደምታውቁት ባለፈው ዓመት በሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር የዓለም አቀፍ ማኅበራችንን ሥራ ተረከቦአል — የወንድምነትና የአንድነት ሰላምታ አቀርባለሁ::በሰሜን አሜ የኢት ተማ ማ ወደዚህ ማኅበር ዓመታዊ ጉባዔ ወኪሎችን መላክ ከጀመረ ይኸው ሦስት ዓመታት ሆኑት::እኔም በነዚህ ሦስት ዓመታት ውስጥ ሁለት ጊዜ — መጀመሪያ በዘገሬብ፤አሁን በበርሊን — በሰሜ አሜ የኢት ተማ ማ ወኪል ለመሆን ዕድል በማግኘቴ ልዩ ደስታ ይሰማኛል::ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የማኅበራችን አንድነት እየጠነከረ ሔዷል፤ የጋራ ዓላማዎቻችን እያደጉና እየደረጁ መሔዳቸውን ቀጥለዋል::ይህም ታላቅ ደስታ ይሰጠኛል::

ከሦስት ዓመት በፊት የዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር መቋቋም የኢትዮጵያ ወጣቶችና ተማሪዎች የጋራ ዓላማ ማደግ፤ኅብረትና አንድነት መጠንከር ካስከተላቸው ወና ዋና ክንውኖች አንዱ ነው::ኢትዮጵያን ከጠባቧ የፊውዳልና የኢምፔሪያሊስት ጭቆና ነፃ ለማውጣት በአንድነት ቆርጠን የተነሳን በመሆናችን የተወሀድን ነን::በዚህ ትግላችን ውስጥ በአረመኔው መንግሥትና በኢምፔሪያሊዝም በተገዙ ገዳዮች እጅ የብዙ ሀገረ ወዳድ ወገኖቻችን ደም ፈስአል::የብዙ ቆራጥ ታጋዮች ሕይወት አልፍአል::ብዙዎችም በእሥር ቤት ስቃይ ደርሶባቸዋል::አሁንም በመሰቃየት ላይ ያሉ ጥቂቶች አይደሉም::

ትግሉ እየከረረ በሔደ መጠን — ይህም መሆኑ አይቀርም — ብዙ ቆራጥ ሀገረ ወዳዶችና የሕዝብ ወገን ጀግኖች ይሰቃያሉ፤ይሞታሉም::ከዚህ የተለየ ነገር ይሆናል ብለን አራሳችንን አናታልልም::ጠላቶቻችን—የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላቶች—በፋሽስታዊ ኃይል — በተቀጠሩ ገዳዮች በመጠቀም፤በብዛት በመግደል፤በማሰርና በማሰቃየት — እንቅስቃሴያችንን በጭራሽ ለመቅጠትና ለማውደም እንደሚመኙ አይጠረጠርም::ይህ ከዱሃ

ሪ ኃይሎች የማይለይ ጠበይ ነው::አድሃሪ ኃይሎች አንዳን
ድ የራጦችን በመግደል የሞጡበትን ሰበብ ጭምር ለመግደል
አንችላለን የሚል ከንቱ እምነት አላቸው::ስለዚህም በኢት
ዮጵያ ላይ የተዘረጋው የፊውዳል ፋሽስት ጭቆና የተማሪ መ
ሪዎችንና ሀገረ ወዳዶችን እንደያጠፉ ነፍስ ገዳዮችን ከመ
ግደል የተለየ ሌላ ምንም ነገር ሊያደርግ አይችልም::ለነ
ፍስ ገዳይ ወታደሮች፣ለሰላማዊ ሰልፍና ለሀዘን የተሰበሰቡ
ትን ተማሪዎች ጨፍጭፉ፣በሰንጃ ውጉ ከማለት የተለየ ሌላ
ትእዛዝ ሊሰጥ አይችልም::በታህሣሥ 19፣1962 የጓድ ጥ
ላሁን ግዛው መገደልና ተከታትሎም በመላ ኢትዮጵያ ወጣቶች
ላይ የወረደው እልቂት ጨቋኙ አገዛዝ ለረጅም ጊዜ ለዘረጋ
ው የጥፋት ፖለቲካ በቂ ምስሎች ናቸው::በለፉት አሥር
ዓመታት ውስጥ ብቻ በኤርትራ፣በውጋዴን፣በባሌ... እንደሁ
ም በቅርቡ በጉጃም የፈጸማቸውን የአረመኔ ተግባሮች ደህና
አድርገን እናውቃቸዋለን::በተለይ በናጌሌም ቦምብ ያጠፋው
ሕዝብና ያወደማቸው መንደሮች አስከመቼም የሚረሱ አይደሉም

የበሰበሰው መንግሥት በዚህ የጥፋት ፕሮግራሙ በማሸበርና
በማስፈራራት ሕዝቡን ረግጦና ተገዥ አድርጎ ለማስቀረት
እንደማይችል ደህና አድርገን እናውቃለን::የኢትዮጵያ ሕዝ
ብ፣እንደማንኛውም የተጠቃ ሕዝብ ሁሉ፣በፊውዳሊዝምና በኢ
ምፔሪያሊዝም ቀንበር ስር አስካለ ድረስ ቆራጥ ትግሉን መ
ቀጠሉ አይቀርም::ከዚህ ማንም ሊገታው አይችልም::የሚጠራ
ጠር ቢኖር ጀግናው የኢትዮጵያ ሕዝብ በየዕለቱ የሚያከናው
ነውን ደሚ ምሳሌ ይመልከት፣ይማርም::የተጠቃነውን የሀገሩ
ን ሕዝብ ጉዳይ የራሱ አድርጎ የተነሣውና ከሕዝቡ ጋር ለ
መዋሀድ የቆረጠው ሀገረ ወዳድ የኢትዮጵያ ወጣትና ተማሪ
ትግሉም እንደዚሁ ነው::እንደዚህም ሆኖ ይቆያል::እያደገ
ም ይሔዳል::

እዚህ ጉባዔ ላይ ለዚህ ለተቀደሰ ተግባር ያለንን ጥንካሬ
እንደገና እናድስ::እንዲያውም ከፍ እናድርግ::የሕዝብ ወ



ገንነታችንን እናጠንክር::ሕዝባችንንና ሀገራችንን ነፃ ለ
ማውጣት ያለንን እምነት እናጥብቅ::እንቅስቃሴያችንን ለማ
ስደግና ለማስፋፋት እንችል ዘንድ የማኀበሮቻችንን ድርጅቶ
ች በበለጠ እናጠንክር::ከሁሉም በላይ ደግሞ ጠላቶቻችን
እኛን በስህተት መንገድ ለመምራት ና ለመከፋፈል በየጊዜው
ከሚወጥኑዋቸው ከሚያጠምዱዋቸው ወጥመዶች ውስጥ እንዳንገባ
እንጠንቀቅ::ዕውነተኛ ጠላቶቻችንና ወዳጆቻችን እነማን እ
ንደሆኑ አበጥረንና ለይተን በትክክል እንወቅ::

ጠላቶቻችን ፊውዳሊዝም፣ኢምፔሪያሊዝምና የነዚህ ደጋፊዎች
ሁሉ ናቸው::ይህ በቅድሚያ ግልጽ ሆኖ ሊታወቅ ይገባዋል::
ወዳጆቻችን እነዚህን የተያያዙና የተወሳሰቡ ጠንቆች የሚከ
ላከሉና የሚቃወሙ ሁሉ ናቸው::ከዚህ የተለየ ምርጫ የለም
ማንም ደግሞ በነዚህ መሀከል የገለልተኛነት አቋም አለ ብ
ሉ እንዳይሳሳት::በዚህና እነዚህን በመሰሉ ነገሮች አሳሳ
ቾች እንዳያደናግሩን እንጠንቀቅ::የመረጥናቸው ተግባሮች፣
የምንቆጋለት ዓላማ ለሀብትና ለሀብተኞች፣ላልቆረጡና ለወ
ላዋዮች ስፍራ አይሰጡም::

ይህ ጉባዔ እንዲያጠናው የቀረበው አርእስት ለኢትዮጵያ ም
ን ዓይነት ለውጥ? የሚል ነው::ጥልቅና ጠቅላላ፣ሰፊና የ
ተቀናበረ ትንተናን የሚጠይቅ ታላቅ ጥያቄ ነው::ነውንና
የበሰለ ምርመራን ይጠይቃል::ይህ ጥያቄ፣የምንፈልገው ምን
ድነው? እንዴትስ እዚያ ለመድረስ እንችላለን? የሚለውን
ጉዳይ በቀጥታ ይመለከታል::የት እንዳለንና ወዴትስ ለመድ
ረስ እንደምንፈልግ ለራሳችንና ለሌሎች መግለጽ አለብን::
ይህንንም በምናደርግበት ጊዜ በመሠረተ ቢስ ሀሳብና በስሜ
ት ከመገፋት መራቅ አለብን::እርገጠኞች መሆን አለብን::
ማለት ሀሳባችንና ፕሮግራማችን በሳይንሣዊና በትክክለኛ አ
ስተሳሰብ የተመሠረተ መሆን አለባቸው::ያለአንዳች ፍርሀት
ና ያለማወላወል ማንኛውንም ጥያቄ እየጠየቅን እንመርምር፣
ሀሳባችንን በሙሉ ለመግለጽ፣የሌሎችን አስተያየት በጥሞና

ለማዳመጥ፣በሎጂክና በትክክለኛነት ለማስገንዘብና ለመገንዘ
ብ፣አስፈላጊ የሆነው የዕውነተኛነትና የትክክለኛነት ጠባይ
ይኮረን::ሆኖም — ይህም ማስጠንቀቂያ በጣም አስፈላጊ ነ
ው — ይህ ሎጂክና ትክክለኛነት ከዓላማችንና ከአቅጣጫችን
የተለየ መሆን የለበትም::እኛ የምንከተለው ሎጂክና ትክክ
ለኛነት፣ለምሳሌ ያህል፣ከፋሽስትና ከኢምፔሪያሊስት ሳይንስ
የተለየ ብቻ ሳይሆን ተቃራኒም ነው::የኛ ከመረጥነው ርዕ
ዮተ ዓለምና ለመድረስ ከምንፈልጋቸው ግቦች ጋር የተስማማ
ነው::የተስማማም መሆን አለበት::ስለዚህም የኛ ሳይንስ
የሚለካው — ሁልጊዜ — በጠቀሳሳው ለሰው ልጆች፣በተለይም
ለላብ አደሩ ሕዝብ ዕውነተኛ ፍላጎትና ደህንነት በሚሰጠው
አገልግሎቱ ብቻ ነው::

በመጨረሻ ላስታውሳችሁ የምፈልገው ሰሜን አሜሪካ ያሉት ጓ
ደኞቻችሁ በዚህ ወቅት የናንተን በመሰለ ተግባርና ትጋት
ላይ መገኘታቸውን ነው::በሰሜ አሜ የኢት ተማሪዎች ማኅበ
ር በዚህ ዓመት የፈጸማቸውን ልዩ ልዩ ተግባሮች ለዚህ ጉ
ባኤ ለማስታወቅ በሚከተሉት ቀናት ውስጥ ዕድል ይኖረኛል::
እዚህ ላይ ልጠቅስ የምወደው ከኒ ሌላ የሁለት በሰሜን አ
ሜሪካ የኢት ተማ ማኅበር አባሎችን — የሸረገ ሕይወትና
ሰናይ ልኬ — እዚህ ጉባኤ ውስጥ መገኘት ነው::በሰሜ አ
ሜ የኢት ተማ ማኅበር ሦስት አባሎች አንዱ ላይ በዚህ ማ
ኅበር ጉባኤ ውስጥ መገኘት እላይ ለጠቀስኩት ያንድነታችን
መጠንከር ዓይነተኛ ምስክር ነው::እነዚህ ጓዶች በሰሜን
አሜሪካ የሚገኙ ወገኖቻችን ስለሚያደርጉት ሙያና ስለሚያጋ
ጥማቸው ችግር በምንወያይበት ጊዜ በበለጠ ያስረዱናል::

በአሁኑ ዓመት ከ'ኦገስት' 28 እስከ 'ሴፕቴምበር' 2
የሚደረገውን በሰሜ አሜ የኢትዮ ተማ ማኅበር 18ኛ ጠቅላ
ላ ጉባኤ ተግተው በማዘጋጀት ላይ ይገኛሉ::ጉባኤው የሚደ
ረገው አዋናው የዓለም ኢምፔሪያሊዝም እምብርት መናገሻ በ
ሆነው በዋሽንግተን ዲ ሲ ከተማ ነው::እንደምታስታውሱት



ባለፈው ዓመት አረመኔው ኃይለሥላሴ ለ8ኛው ጊዜ አሜሪካን
ን ለመባለም ሔዶ ነበር::እዚያ የሚገኙት ወንድሞቻችን እ
ሱንና ኢምፔሪያሊስት ገብረአበሮችን ከፍ ባለ ሁኔታ ተቋቁ
መዋቸው እንደነበረና የፊውዳሉን መንግሥት ኢምባሲ ለጥቂት
ሰዓቶች ያህል ነፃ አውጥተው እንደነበረ ታስታውሳላችሁ::
በትግሉ ተሳታፊዎች ብዙዎችም በያንኪ ፖሊስ እንደተደበደቡ
ና ሃያ አምስት ያህሉም ታስረው እንደነበረ ሰምታችኋል::
ከነዚህ ውስጥ በተለይ አሥራ አራቱ በጥብቅ ተከሰው በዋሽ
ንግተን አሻንጉሊት ፍርድ ቤቶች ሲንገላቱ አንድ ዓመት ቆ
ዩ::በመጨረሻ ግን፣አሳሪዎቻቸውንና ከሳሾቻቸውን ለረጅም
ጊዜ በፍርድ ከተጓተቱ በኋላ፣ከአንድ ወር በፊት ድል በማ
ድረጋቸው ከኢምፔሪያሊስቶች ቅጣትና እሥራት ነፃ ለመውጣት
ቻሉ ብዬ ላበስራችሁ ከትልቅ ደስታ ጋር ነው::ይህ ለትግ
ላችን በጣም ጠቃሚ ድል ነው::በትግላችን የተገለጸውን ኅ
ብረትና እንዲሁም ደግሞ ሁለቱ ጠበቆች ያደረጉትን ጥረት
ልናስታውስ ይገባል::

— የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ለዘለዓለም ይኑር
— የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ ለዘለዓለም ይኑር
— ፊውዳሊዝምና ኢምፔሪያሊዝም ይውደም::

## የአንድነት ድጋፍ

ደጋግመን እንደተናገርነው ባለንበት ወቅት ፀረፊውዳልና ፀረ ኢምፔሪያሊስት ትግል በመላው ዓለም በመካሄድ ላይ ነው የአሜሪካ ጭቆናና ዘረፋ ዓለምአቀፍ እንደመሆኑ መጠን ጠላቶችና ተቀናቃኞች እንደዚሁ በዓለም ላይ ሁሉ ይገኛሉ፡፡ፊውዳሊዝም አርማ አግዶ፣አደንቋሪ፣አረዷች . . . እንደመሆኑ መጠን የወደፊት ተራማጅ የሆኑ ሁሉ ይጠሉታል፣ይወጉታልም፡፡ዛሬን ፊውዳሊዝምንና ኢምፔሪያሊዝምን እንደጥግምት ወጥሮ የያዛቸው እነዚህ የወደፊት ተራማጅ ኃይሎች በያሉበት ሁኔታው በፈቀደላቸው አቅምና ዘዴ የሚያደርጉት ትግል ነው፡፡የኢምፔሪያሊዝም ኃይል እንደእምቧይ ካብ መናዱ የጀመረው በነዚህ "ተቀናቃኝ ድርጅቶች" ተጋድሎ ነው፡፡

የወደፊት ተራማጅ ኃይሎች ሁሉ፣የትም ሆኑ የት፣ዓላማቸው አንድ ነው፡፡ኢምፔሪያሊዝምን፣ፊውዳሊዝምንና አድሃሪ ኃይሎችን ሁሉ ከዓለም ገጽ ማጥፋት፡፡ዴሞክራሲንና ሰላምን መሥርቶ የወደፊት ግስጋሴን ማፋጠን፡፡ይህ ዓላማ የወደፊት ተራማጅ ድርጅቶችን ሁሉ እንደሰንሰለት አስተሳስሮ የማይበገር አንድነት ይሰጣቸዋል፡፡በትግላቸው እንዲዋሀዱ ያደርጋቸዋል፡፡

የኢትዮጵያ ተማሪዎች አንቀሳቃሲ ረቮሉሽናዊ ጉዳና ከመረጠበት ጊዜ አንስቶ ከወደፊት ተራማጅ ድርጅቶች ጋር መቀራረብ ጀምሮአል፡፡በማጋለጥ ትግሉ ጊዜ — ሰላማዊ ሰልፍ በሚያደርግበት ጊዜ፣ኢምባሲዎችን ነፃ በሚያወጣበት ጊዜ — ገዴታዊ ድጋፋቸውን ያገኛል፡፡በጋዜጦቻቸው የኢትዮጵያን ዕውነተኛ ሁኔታ የሚያብራሩ ጽሑፎችን ለማውጣት ይችላል፡፡በየዓመቱ በሚደረገው ጉባዔ ላይ በቀን ሕሊና ላይ የተመሠረተ ትብብራቸውን ያገኛል፡፡የድጋፉ ዓይነት ብዙ ነው፡፡ግን አንዱም እንደ ምፅዋት—መሰል አርዳታ አይቆጠርም፡፡እንደ "የጋራ ትብብር" እንጂ፡፡



"የጋራ ትብብር" በሚለው መሠረታዊ አስብ በመመራት ሳውሮፓው ማኅበራችን አሥረኛ ጉባዔ በርከት ያሉ የወደፊት ተራማጅ ድርጅቶች ወኪሎቻቸውን ልከዋል፡፡መምጣት ያልቻሉ ደግሞ የአንድነት መግለጫ ደብዳቤ ወይም ቴሌግራም ሰደዋል በጉባዔው ላይ ከተደረጉት የወኪሎች ንግግር አንዳንዶችንና እንደዚሁም ከደረሱን የአንድነት መግለጫ መልእክቶች ግማሾችን ከዚህ በታች ለአንባቢዎች እናቀርባለን፡፡

መልእክቶች የደረሱን በልዩ ልዩ ቋንቋ ቢሆን ቀጥለን የምናሰፍረው ትክክለኛውን የአማርኛ "ትርጉም" ነው፡፡

## መልእክቶች

ኦገስት 4፣1970
ፓሪስ

ጓዶች — ደብዳቤ

የማላጋሽ ተማሪዎች ማኅበር የወንድምነትና ፀረኢምፔሪያሊስት ሰላምታውን ለጉባዔው ተሳታፊዎች ያቀርባል፡፡

ጓዶች፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ፣በተለይም የኢትዮጵያ ተማሪዎች ከፊውዳሊዝምና ከኢምፔሪያሊዝም ጋር የሚያደርጉት መራራና የማያቋርጥ ትግል በማካሄድ ላይ መሆናቸውን እናውቃለን

የማላጋሽ ተማሪዎች ማኅበር የኢትዮጵያ ሕዝብ ዞሮ ዞሮ የመጠረሻውን ድል እንደሚጐናፀፍ አይጠራጠርም፡፡

በበኩሉ የማላጋሽ ሕዝብ እንደዚሁ ከፈረንሣይ ኢምፔሪያሊዝምና ከማላጋሽ አድሃሪዎች ጋር ትግሉን ይቀጥላል፡፡

ለጉባዔያችሁ ሙሉ ከንውን እንመኛለን፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ ያሸንፋል::

ፀረኢምፔሪያሊስት የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብና የማሳጋሽ ሕዝብ አንድነት ለዘለዓለም ይኑር::

ዓራ ራማአንድራአይቮአናን

---

'ኦገስት' 10 ፤ 1970
በርሊን
— ቴሌግራም—

የኩርድ ረቮሉሽን አንድነት ኮሚቴ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከውስጣዊ ጭቆናና ከውጭ አገዛዝ ጋር ለሚያደርገው ትግል አንድነቱን ይገልጻል::

በአሁኑ ጊዜ ረቮሉሽናዊ አንቅስቃሴ የሚያስሐብ ደረጃን በመተሳሰፍ ላይ ነው::ያሜሪካ የጦር ኃይል በኢትዮጵያ ውስጥ እያደገ መሔድ የጽዮናዊያንን የወረራ ምኞትና ምሽግ እያጠነከረው በመሔዱ ትግሉን እስከ አረብ ፔኒንሱላና እስከ አደን ዱረስ እንዲስፋፋ የሚያስችለው ኃይል ሰጥቶታል: ይህ ሁኔታ የፍልስጥኤምን፣የኢትዮጵያንና የኩርድን ሕዝቦች የጦር ትግል አንድነት እንደሚያጠነክረው አይጠረጠርም::

በኢምፔሪያሊዝምና በጽዮናዊያን፣እንደሁም በረቮሉሽናዊ መስል አድር ባዮች ከዳት የተጠቁና በዚህ ዓለም ክፍል የሚገኙ ሕዝቦች "የትግል አንድነት" ለዘለዓለም ይኑር::

የኩርድ ረቮሉሽን አንድነት ኮሚቴ ጉባዔያችሁ ጥሩ ውጤት ያገኝ ዘንድ ምኞቱን ይገልጻል::

እናሸንፋለን::
የኩርድ ረቮሉሽን አንድነት ማኅበር



ኦገስት ፤ 1970
ኮፐንሀገን
— ደብዳቤ
ረዘም ያለ ደብዳቤ በመሆኑ አልፈን አልፈን ዋና ዋናዎቹን አባቦች ብቻ አንጠቀሰላን::

ውድ ጓደች

... በሰበሰባው መከፈቻ ላይ ወኪል ለመስደድ ባለመቻላችን ቅር ይለናል::በዚህ መልዕክታችን በውጭ አገር የሚገኙ የኢትዮጵያ ተማሪዎችና የኢትዮጵያ ሕዝብ ከብሔራዊ አድሃሪ ኃይሎችና ከኢምፔሪያሊዝም ብዝበዛና ጭቆና ነፃ ለመውጣት የሚያደርጉት ትግል እንዲቃናላቸው የወንድምነት ምኞታችንን ለጉባዔው ተሰታፊዎች ለመግለጽ እንፈልጋለን::

ስለዓለም ሁኔታ ያለንን አስተያየት በጥቂቱ እንድንገልጽ ፍቀዱልን::

ዛሬ ዓለምን አጠያለን ስንመለከት ዋናው ቅራኔ ... በኢምፔሪያሊዝምና በእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ በሚበዘበዙት ሕዝቦች መካከል ሆኖ እናገኘዋለን::

ይህ ዋና ቅራኔ ሊሉትን የበሸል ቅራኔዎች ሁሉ — በኢምፔሪያሊዝምና በቀድሞ የቅኝ አገዛዝ መንገዱ በሚበዘበዙ ሕዝቦች መካከል፣በራሳቸው በኢምፔሪያሊስት አገሮች መካከል በእያንዳንዱ ኢምፔሪያሊስት አገርና በእያንዳንዱ በእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ በሚተዳደር አገር መካከል ያሉትን ቅራኔዎች — የሚመራውና የሚወስነው ይህ ዋና ቅራኔ ነው::

እንደሚታየን፣ኢትዮጵያ በሚጠቁትና በሚበዘበዙት አገሮች ውስጥ አንዷ ናት::... የኢምፔሪያሊስት "የሥራ ክፍያ" እንድ ዓይነት አዝርዕ — ቡና — ማፍራትን ብቻ ስ

ጥቷታል:: . . . አገሪቱ ያላትን የተፈጥሮ ሀብት ሰፉ ትና
ምች አቀማመጥ ለመጠቀም ቢሉ ኢምፔሪያሊስቶች ኢትዮጵያን
የአፀ አዙር ቅኝ ገዛት አድርገዋታል::ይህም ኢትዮጵያ ነ
ፃ እንድትወጣ ለሚደረገው ትግል ድጋፍ እንድንሰጥ ልዩ ገ
ዴታ ይጥልብናል::

ከሁለተኛ የዓለም ጦርነት በኋላ ብዙ የብሔራዊ ነፃነ
ት እንቅስቃሴዎች ድል እንደተጐናጸፉ አላየንምን? የባዕድ
ቅኝ ገዥዎች ተሸቀንጥረው ተጥለዋል::የኃይል መሠሪያቸው
ተሰብሯል::ይህ የኢምፔሪያሊዝምን ኃይል አደከመውን? የዓ
ለም አቀፉን የላብ አደር ረቮሉሽን ወደፊት አራመደውን?
የለም::እንደዚህ ያለ ነገር ፍጹም አላደረገም::

በትንሹዋ ቡርዧ መደብ አመራር የብሔራዊ ነፃነት እንቅስቃ
ሴ የግል ባንዲራ፣ብሔራዊ መዝሙርና የግሉ ጦር ኃይል ያለ
ው ነፃ መንግሥት ቢያቋቁምና ነገር ግን የኢምፔሪያሊዝምን
ኃይል ባያዳክመው ቢቀር እንደግፈዋለንን? ይህ ዓይነት ብ
ሔራዊ የነፃነት እንቅስቃሴ በተባለው አገር ውስጥ የአፀ
አዙር ብዝበዛን ቢያስከትል — ይህ ደግሞ ኢምፔሪያሊዝምን
ለጊዜው ማጠንከሩ አይቀርም — እንደግፈዋለንን? እንደግፈ
ዋለን::ልንደግፈውም ይገባል::ነገር ግን ድጋፋችን ሙሉ
በሙሉ ሊሆን አይችልም::እንነቅፈዋለን::በዚያ አገር ወይ
ም በዚያ የዓለም ክፍል ሌላ እንቅስቃሴ ቢኖርና ለብሔራዊ
ነፃ አውጭ ትግሉ የላብ አደሩን አመራር የሚያጐናጽፍ ከሆ
ነ፣ከኢምፔሪያሊዝም ጋር፣ሠርቶ አደሩን ሁሉ አንቀሳቅሶ፣በ
ግማሽ መንገድ ሳይቆም እስከመጨረሻው ከተታገለ በግልጽ እ
ንደግፈዋለን::

ውድ ጓዶች

ጉባኤያችሁ የወደፊት ተራማጅ ኃይሎች አንድነትንና
ረቮሉሽናዊነት የጠበቀ መሠረት መጣያ እንዲሆንላችሁ እንመ



ኛላችኋለን::ወደአገራችሁ የምትመለሱበትንና በኢትዮጵያ ው
ስጥ በሚደረገው ትግል ውስጥ የምትሰተፉበትን ቀን የሚያቃ
ርብላችሁ እንዲሆን እንመኛለን::

የተጨቆኑትና የተራቡት ያሸንፋሉ

---

'ኦገስት' 7 ፣ 1970
ፕራግ

— ቴሌግራም

የወንድምነት ሰላምታ::ለስብሰባው ሙሉ ድጋፍ::ከኢት
ዮጵያ ጋር የጋለ አንድነት::ጉባዔው ይቃና::

በአውሮፓ የአፍሪካ ተማሪዎች ኅብረት

---

'ኦገስት' 9 ፣1970
ስዊድን

— ቴሌግራም

ከተጨቆነውና ከተበዘበዘው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ያለ
ንን የጠበቀ አንድነት ለመግለጽ እንፈልጋለን::ኢምፔሪያሊ
ዝም የጋራ ጠላታችን ነው::በጋራ ትግላችንም ይሸነፋል::

ረቮሉሽናዊ ሰላምታ
የአንጐላ ሕዝብ የነፃነት ሕንቅ
ስቃሴ ከበብ

'ኦገስት' 7 ፤ 1970
ፕራግ

— ቴሌግራም

በስብሰባው ላይ ለመካፈል ባለመቻላችን እናዝናለን:: የኢትዮጵያ ሕዝብና ተማሪዎች ከኢምፔሪያሊዝም፣ከፊውዳሊዝምና ከአድሃሪ ኃይሎች ጋር የሚያደርጉትን ትግል በጥብቅ እንደግፋለን::የኢትዮጵያ ተማሪዎች ለዲሞክራሲና ለመሠረታዊ ሰብአዊ መብቶች ለሚያደርጉት ትግል አንድነታችንን እንገልጻለን::ለጉባዔው ሙሉ ውጤት መልካም ምኞት::

ዓለም አቀፍ የተማሪዎች ኅብረት
ጽሕፈት ቤት

---

'ኦገስት'4 ፤ 1970
ኡፕሳላ — ስዊድን

— ደብዳቤ

ለአዲሲቱ ኢትዮጵያ ለምታደርጉት ትግል የአንድነት ሰላምታ::

የኡፕሳላ አፍሪካ ክበብ

---

'ኦገስት'2 ፤ 1970
ማልሞ — ስዊድን

— ደብዳቤ

ጓዶች

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር በበርሊን በሚ



ደረገው አሥረኛ ዓመታዊ ጉባዔ ላይ በመከፈቻው ዕለት፣በኦገስት 10፣1970፣ እንድንገልጹ የተደረገልንን ጥሪ ተቀብለናል::ስለዚህም ለዚህ አስፈላጊና ረቮሉሽናዊ ስብሰባ አንድ ተመልካች መልእክተኛ ለመስደድ መሳካችንን እናስታውቃለን::

ጥልቅ ምስጋናችንን እየገለጽን፣ረቮሉሽናዊ ሰላምታችንን እናቀርባለን::

የሱንድ አፍሪካ ክበብ
— ቀዳሚ ፤ የሱንድ ደቡብ አፍሪካ ኮሚቴ —

---

'ኦገስት'10 ፤ 1970
ኒውዮርክ

— ቴሌግራም

የአውሮፓው ማኅበር ጉባዔ የተሳካ ይሆን ዘንድ የጋለ ምኞታችንን እንገልጻለን::

ኢሱና

---

'ጁላይ' 25 ፤1970
ዘገረብ

— ደብዳቤ

ውድ ወዳጆች

ስለአሥረኛው ጉባዔያችሁ መደረግ ለበጧችሁን ዜና እናመሰ

ገናለን።

በጉባዔው መክፈቻ ቀን ወኪሎቻችንን ለመስደድ በለመቻላችን በጣም እናዝናለን።

በአገሪቱ ውስጥ ማንኛውንም ዓይነት መሠረታዊ ለውጥ ለማምጣት መነሻው የባላባታዊውና የኢምፔሪያሊስት ብዝበዛ መጥፋት መሆን እንዳለበት አንጠራጠርም።

ከሰላምታ ጋር
የዩጎዝላቪያ ተማሪዎች ክላብ

---

'ጁላይ' 28፣ 1970
ማንቸስተር — ኢንግላንድ

ውድ ጓደኞችና ወንድሞች — ደብዳቤ

"የአፍሪካ ሶሻል ሊግ" በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር አሥረኛ ጉባዔ መክፈቻ ላይ ወኪል ለመላክ በይችልም፣ከኦገስት 9–17፣1970 ለሚሰበሰቡት ወንድሞችና ጓደኞች ሁሉ የጋለና የወንድምነት ሰላምታውን ይልካል፡

ይህን አጋጣሚ ጊዜ ምክንያት በማድረግ፣እራሱን አዋርዶ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ገዘተኛና ገባሪ የሆነውን፣የኢትዮጵያን ሰፊ ሕዝብ በትልቅ ስቃይና ድህነት ላይ የጣለውን፣ቡችላውን፣ፋሽስቱንና ጠካኙን የኃይለሥላሴን መንግሥት እናወግዛለን።

የኃይለሥላሴ ባላባታዊና ጠካኝ መንግሥት፣በኢምፔሪያሊስት ጌቶቹ በመደገፍ፣ከልክ በላይ ለሚበዘብዙት፣ለሚጠቁኑትና ከሰውነት ደረጃ ለወጡት የኢትዮጵያ ሠራተኞችና ገበሬዎ



ች ፍላጎትና ምኞት የቆሙትን ተማሪዎችና ምሁራን አንድ በአንድ በመጠረስ ላይ መሆኑን እናውቃለን።

"የአፍሪካ ሶሻል ሊግ" የሕዝባችንን መንታ ጠላቶች — ብሔራዊ ጭቆናንና በአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም የሚመራውን የዓለም ኢምፔሪያሊዝም — ለመውጋት ቆርጦ ተነስቷል።እናንተም ከነዚሁ በኃይለሥላሴ ባላባታዊ፣ፋሽስታዊ ጭቆናና በኢትዮጵያ የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ከተወከሉ ጠላቶች ጋር ለምታደርጉት በሀገር ፍቅር የተሞላ ትግል አንድነታችንን እንገልጻለን።

በዕውነተኛውና በኩሩው አፍሪካዊ ድምጻችን የሚከተለውን እንድንል ፍቀዱልን።

በአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም የሚመራው የዓለም ኢምፔሪያሊዝም ይውደም።

በአፍሪካችን ፋሽትና የቀለም ልዩነት ጭቆና ይውደሙ

ፊውዳሊዝም፣ካፒታሊዝምና አሰበች ሶሻሊዝም ይውደሙ

ድል ለረጅም ጊዜ ለተጠቃነው ለአፍሪካ ሕዝብ ይሁን

ድል ለአፍሪካ ብሔራዊ የነጻነት እንቅስቃሴዎች ይሁን

በአፍሪካ ድሉ ለዕውነተኛ ረቮሉሽናዊ ሐሳብና ትግል ይሁን

የመጠረሻው ድል ለጀግናው ሰፊ የኢትዮጵያ ሕዝብ ይሁን

'ኦገስት' 15 ፣ 1970
በርሊን

— ቴሌግራም

በኢትዮጵያ ላይ የሰፈረውን የፊውዳል—ፋሽስት አገዛዝና እንዲሁም ሕዝቡን በመጨቆንና በማሰቃየት የሚደረገውን ጭቆና በመቃወም የምታደርጉት ትግል በዓለም ከሚደረገው ፀረ ፋሽስት ትግል አንዱ ክፍል ነው::ለጠቅላላው ጉባዔያችሁ መልካም ውጤት እየተመኘን በዓላማችሁ ያለንን አንድነት እንገልጻለን::

— የዓለም ተማሪዎች ኅብረት

— ወገኔሳዊ ተማሪ ዴሞክራቶች

---

'ኦገስት' 11፣ 1970

ፓሪስ

— ቴሌግራም

ወደአሥረኛው ጉባዔያችሁ መልእክተኛ ለመላክ አልቻልንም::ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብና የኢትዮጵያ ተማሪዎች ጠቋኙን ፋሽታዊ የኃይለሥላሴ፣ፊውዳላዊ አገዛዝና የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝምን በመቃወም የሚያደርጉትን ትግል ያለማወላወል እንደገፋለን::ለጠቅላላው ጉባዔያችሁ መልካም ውጤት እንመኛለን::

በፈረንሣይ የጥቁር አፍሪካ ተማሪዎች ማኅበር



'ኦገስት' 10 ፣ 1970
በርሊን

— በጉባዔው ላይ የተነበበ ንግግር

ውድ ወዳጆች:

ዓለም አቀፉ ፀረኢምፔሪያሊስት ትግል አዲስ ደረጃ ላይ ደርሶአል::ኢምፔሪያሊዝም ወደኋላ በሚያስቀራቸው ሕዝቦች ላይ የጫነው ብዝበዛ ይበልጥ እየጠነከረና ገፈኛ እየሆነ ይሔዳል::የጀግናው የቬየትናም ሕዝብ፣የኢንዶቻይና፣የፍልስጥኤም፣የደቡብ አሜሪካ፣የኢራንና የኢትዮጵያ ሕዝቦች የነፃነት ንቅናቄዎች፣ከጭቆና ብዛት የተነሣ፣በኢምፔሪያሊዝምና በሦስተኛው ዓለም ሕዝቦች መካከል ያለው ቅራኔ እየከረረ መሔዱን ነው::

ኢምፔሪያሊስቶች ታሪክ ያመጣባቸውን መሸነፍ ለማዘግየት ሲሉ በተበዝባዦች አገሮች የሚገኙትን አድሃሪ ኃይሎች በገንዘብም ሆነ በጦር ኃይል መደገፍና የሕዝቦችን የነፃነት ትግል ለመደምሰስ የፖሊስ ኃይልንና ሌሎች የመጨቆኛ ኃይሎችን በጠበያቸው ያለ ነው::

ኃይለሥላሴና የኢራኑ ሻህ በአፍሪካና በእስያ በአድሃሪነት የላቁ ገዥዎች ናቸው::የኢምፔሪያሊዝም ቡችሎች እንደመሆናቸውም መጠን ለኢትዮጵያና ለኢራንሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ እርምጃ ዋና እንቅፋቶች ናቸው::

ከዚህም የተነሣ ሁለቱ ሕዝቦቻችን አድሃሪዎችንና ኢምፔሪያሊዝምን በመቃወም የሚያደርጉት ትግል በአንድ የጋራ ዓላማ የሚመራ ነው::ከነፃነት ታጋዮች ክፍል የሆኑት የተማሪዎች ድርጅቶችም ኢምፔሪያሊዝምን፣አድሃሪና ፀረረቮሉሽናዊ ኃይሎችን ሁሉ በመቃወም በአንድነት መታገል አለባቸው::እንግዲህ የጋራ ትግላችንን በአንድነት ለመምራት የሚያስፈልገውን

ድርጅታዊ መልክ መፍጠር የናንተና የኛ ቀዳሚ ተግባር ይ
ሆናል::

ኮሲስ የተባለው ዓለም አቀፍ የተማሪዎች ድርጅት ሙሉ
በሙሉ የኢምፔሪያሊስቶች መሣሪያ መሆኑ የታወቀ ነው::በም
ሥራቅ አውሮፓ አገሮች ተፅዕኖ ስር የሚገኘው አይ ዩ ኢስ
የተባለው የተማሪ ድርጅትም ቢሮክራሲያዊ ጠባዩን
ደጋግሞ አሳይቷል::ለጋራ ትግላችን የሚበጀውና ቁስትና የ
ሚሆነን የኛው የሆነ፣በኛው የተፈጠረ፣መልኩ ለረቮሉሽናዊ
የተስማማ አዲስ ድርጅት ብቻ ነው::

አሁን ከዚህ ቀጥሎ ባለፉት ወራት በኢራን ውስጥ ከተ
ፈጸሙት ድርጊቶች አንዳንዶችን በጭሩ በመጥቀስ የትግላችን
ን ቀና ቀና ተግባሮች ልገልጽላችሁ እወዳለሁ::

35 የአሜሪካ ሞናፖሎች በኢራን ውስጥ በልዩ ልዩ የ
ኢኮኖሚ ክፍሎች የአንድ ሚሊዮን ዶላር ካፒታል — ሀብት—
በሥራ ላይ ለማዋል አንድ የአሜሪካን 'ኮንሶርሲየም' ለማ
ቋቋም ማቀዳቸውን ገልጸዋል::ይህም ትርጉም ቀላል ነው::
የኢራን የርብታ ኃይሎች በሙሉ በአሜሪካ ኢምፔሪያሊስቶች
ተገዙ ማለት ነው::ይህን አጂግ አስጊ የሆነ ዱለት ተገን
ዝቦ ሰፊው ሕዝብ በተማሪዎችና በምሁራን መሪነት የተቃውሞ
እርምጃ ወስዷል::

በሥልጣን ላይ ለመቆየት ቢል ለኢምፔሪያሊስት የበላይ
ጠባቂዎች ማናቸውንም የቡችላ ተግባር የሚፈጽመው አድሃሪው
የሻሁ መንግሥት የኢምፔሪያሊስቶች የ'ኢንቬስትሜንት'—የል
ማት — ፕላን እንዳይቃወስ ለማድረግ የሕዝቡን ተጋድሎ ያ
በረደ መስሎት በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ሰዎች 'ሁከት ጫሪዎች'
በማለት አፍሶ ከእሥር ቤት ሰደደ::ከነዚህ ውስጥ ካራት
የበለጡ ምሁራን የሞት ፍርድ ሲፈረድባቸው ሁለቱ የነፃነት
ታጋዮች — ምሁር አሻቶሳ እይዳና መሐንዲስ ሐሰን አከባው



ዱ — እስኪሞቱ ድረስ በግፍ ተንብቁለዋል::

የኢራን ተማሪዎች ኮንፌደረሽን — ብሔራዊ ማኅበር —
ወደፊት ተራማጅና ዲሞክራሲያዊ ድርጅት እንደመሆኑ መጠን
በኢራን ውስጥ ሬቮሉሽናዊና ዲሞክራሲያዊ የሆኑትን ንቅናቄ
ዎች መደገፍ እንደዋና ተግባሩ አድርጎ ይመለከተዋል::ስለ
ዚህ ወዲያውኑ በሻሁ ፋርስ ውስጥ ያለውን የግፍና የጭቆና
አገዛዝ ለዓለም ለማጋለጥ የተቃውሞ እርምጃዎች — ለምሳሌ
በሚንሽን የሚገኘውን የኢራን ቆንሲል መያዝና ለብዙ ጊዜ
ያለ ምግብ ማቆየት ፣ እንደሁም ሌሎች እርምጃዎች — መው
ሰዱ ጀመረ::

ወዳጆቼ፣ እስካሁን ድረስ የሻሁን አድሃሪ የወታደር
አገዛዝም ሆነ ኢምፔሪያሊዝምን በመቃወም ባደረግነው ትግል
ታላላቅ ድሎችን ተጎናጽፈናል::ጠላቶቻችንም ጥያቄዎቻችንን
እንዲቀበሉ ተገደዋል::ነገር ግን ኢምፔሪያሊዝምና ቡችሎቹ
እስኪወድቁ ድረስ ረጅም የትግል መንገድ እንደሚቀረን እና
ውቃለን::የሆነ ሆኖ እናንተና እኛ እንዲሁም ሁለት ሕዝቦ
ቻችን የኃይለሥላሴንና የሻሁን አድሃሪ መንግሥታት ከዓለም
ኢምፔሪያሊዝም ጋር በመቃወም በበሰለ ጥንካሬ እስከመጨረሻ
ው ድረስ ለመታገል የምንችለው ኃይላችንን አንድ ያደረግን
እንደሆነ ነው::ታሪካዊ ተግባራችን ይህ ነውና::

የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝምን እንታገል::

አድሃሪውን የኃይለሥላሴን አገዛዝ እንታገል:

አድሃሪውን የሻህን አገዛዝ እንታገል::

የኢትዮጵያ የነፃነት ትግል ይኑር

የሦስተኛው ዓለም የነፃነት ትግል ይኑር

እንታገላለን፣እናሸንፋለን፣ኢምፔሪያሊዝም ይወ
ወድቃል::

የኢራን ተማሪዎች 'ኮንፌደረሽን'

## የማጋለጥ ትግል

አድሃሪው የኢትዮጵያ መንግሥት ከንቱ ዝናን ለመሸመትና በውጭ አገር ስሙን ለማጋነን፣በአገር ውስጥ ያለውን ድህነትና ጭቆና ከሰፊው የዓለም ሕዝብ ለመሸፈን ብዙ ወጭ ያደርጋል፡፡ተጋብዘው አገር ከጎበኙ በኋላ በሽልማት አጊጠው የሚመለሱ ጋዜጠኞች፡የኢትዮጵያ ሕዝብ በቢተ መንግሥት የሚኖር አያስመስሉ በማቅረብ፡የኢትዮጵያ ሕዝብ ችግር፡በሽታ፡ጭቆና የሌለበት አስመስሉ በማውራት፡የአገሪቱን ዕውነተኛ ሁኔታ በሞላ ጉደል ለመሸፈን ችለው ነበር፡፡

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማንበር እንደዋና ፕሮግራም አድርጎ ከወሰዳቸው ተግባሮች አንዱ አድሃሪው በሳባታዊ መንግሥት ከዓለም አድሃሪ ኃይሎች ጋር በመሸረክ የሚነዛውን ሀሰተኛ ፕሮፓጋንዳ በመቃወም የኢትዮጵያን ዕውነተኛ ገጽ ለዓለም ሰፊ ሕዝብ ማቅረብ ነው፡፡

አሥረኛው ጠቅላላ ጉባዔ ከተከፈተበት ጊዜ ጀምሮ እስከተፈጸመበት ድረስ ይህን ዓላማ ከሥራ ለማዋል አልቦዘነም ከስብሰባው በፊትና በስብሰባውም ጊዜ ለጋዜጦችና ለሬዲዮ ጣቢያዎች በሩ ያለ መግለጫ ሰጥቷል፡፡በስብሰባው መደምደሚያ ላይ በሰላማዊ ሰልፍ በማድረግ ለብዙ ሕዝብ የኢትዮጵያን ዕውነተኛ ሁኔታ ለማስታወቅ ችሉአል፡፡

ከዚህ በታች አንዳንድ የጀርመን ጋዜጦች፡የተሰጣቸውን ዜና በመደገፍ፡ያቀረቡቀቸውን ሀተታዎች ለአንባቢዎች ስናቀርብ እነዚህ ጽሑፎች ከብዙዎቹ ጥቂቶቹ ብቻ መሆናቸውን እያስታወስን ነው፡፡

### የጋዜጦች ሀተታ — ትክክለኛ ትርጉም

አሥረኛው ጠቅላላ ጉባዔ ከመጀመሩ ቀደም ብሎ፡እአአ



በ 4 8 70 እና በ7 8 70፡ ሁለት የበርሊን ጋዜጦች — ታገስ ስፒገልና ሮተ ፕረስ ኮርስፖንዳንስ — ስለጉባዔ መነገር አስታውቀው ነበር፡፡ሁለቱ ጋዜጦች የጉባዔውን አርእስት በመግለጽ የማኅበሩን ዋና ዓላማ አብራርተዋል፡፡በተለይም ሮተ ፕረስ ኮርስፖንዳንስ የተባለው የወደፊት ተራማጅ ኃይሎች ጋዜጣ "በበርሊን የምትገኙ የወደፊት ተራማጅ ኃይሎች፡የኢትዮጵያን ሕዝብ የነፃነት ትግል ደግፉ፡፡በበርሊን ከተማ ከሚሰበሰቡት የኢትዮጵያ ተማሪዎች ጋር ያላችሁን አንድነት ግለጹ፡፡" እያለ ጥሪ ከማድረጉም በላይ ስለ ጊዜው የኢትዮጵያ ሁኔታና ስለትግላችን ዓላማ በሩ ያለ ሀተታ ሰጥቷል፡፡ደጋግሞ ያስታወሰው ጉዳይ ኢትዮጵያ በኢምፔሪያሊዝም — በተለይም በአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም — የተያዘች መሆኗን ሲሆን፡ዛሬ ግን ፊውዳሉ የኢትዮጵያ መንግሥት ለኢምፔሪያሊስቶች ባይቀር እንዷል ተመቻቸው ነበር፡፡ኢምፔሪያሊስት አገሮች የኃይለሥላሴን መንግሥት ለመጣልና አዲስ አገልጋይ ለመመልመል ሤራ በመሥታት ላይ ያሉ ይመስላል ቢል ገልጾአል፡፡በጋዜጣው አነጋገር፡-

"ኢምፔሪያሊስት አገሮች ለአድሃሪው ለኃይለሥላሴ መንግሥት የሚያደርጉትን ገልጽ ዕርዳታ በማቆም ላይ ናቸው ይህም የሆነው የሕዝቡ ትግል እየተፋፋመ በመሔዱ ስለሆነ ይታወቃል፡፡ኢምፔሪያሊስቶች የሚፈልጉት ያለሥጋት ሊዘርፉ የሚችሉበትን የገበያ አካባቢ ነው፡፡ ...ፊውዳሉ የኢትዮጵያ መንግሥት ለጌቶቹ ለኢምፔሪያሊስት ኃይሎች በቂ የሸቀጥ ማራገፊያ ገበያ እንኳን ሊያበረክትላቸው አልቻለም፡፡ ... በበሰበሰ የፊውዳል አስተዳደር የታሰረው የኢትዮጵያ መንግሥት በፍጹም ሊያድግ የማይችል ወደኋላ የሚሔድ ሥርዓት ነው፡፡ኢምፔሪያሊስቶች የሚፈልጉት ሕዝቡን በሰፊው ለመዝረፍ የሚችሉበትን ሁኔታ ነው፡፡የኃይለሥላሴ መንግሥት ለዚህ ኢምፔሪያሊስቶች ለሰጡት ተግባር ብቁ ሆኖ አልተገኘም፡፡"

"እርግጥ ነው ኢምፔሪያሊስቶች የኃይለሥላሴን መንግሥት

ለመገልበጥ ማሧር ጀምረዋል፣ሊገለብጡትም ይችላሉ፡፡ግን የኢምፔሪያሊስቶች ፍላጎትና የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍላጎት በምንም ረገድ አይገናኙም፡፡ኢምፔሪያሊስቶች የሚፈልጉት እነሱን በተሻለ ሊያገለግላቸው የሚችል ቡችላ ነው፡፡የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚፈልገው ግን፡ብሔራዊ ነፃነቱን ሊያስከብርለትና በነፃ ሊያኖረው የሚችል መንግሥት ነው፡፡የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ፀረፊውዳልና ፀረኢምፔሪያሊስት የሚሆነው ከዚህ ነው፡፡የኢትዮጵያ ሕዝብ ፀረኢምፔሪያሊስት ትግል የተጠቁ ሕዝቦች ከሚያደርጉት ፀረኢምፔሪያሊስት ትግል ከቶ ሊነጠል አይችልም የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዓለም ፀረኢምፔሪያሊስት ኃይሎች ጋር ጎን ለጎን ተሰልፎ ዘረፋንና ጭቆናን ከኢትዮጵያ ምድር ሳይ ለማጥፋት ይታገላል፡፡የኢምፔሪያሊስቶች ተንኮል አያታልለውም፡፡

በጉባዔው ወቅት፡ጉባዔው ከተዘጋም ወዲህ ልዩ ልዩ ጋዜጦች — ዲ ቬልት፡ደር ሽፒገል፡ፍራንክፈርተ ሩንዱሸው ፡ በርሊነርኢክስትራ ዲነስት — ስለስብሰባችን፡ስለትግላችንና ስለትግላችን-ዓላማ ሰፊ ሀተታ አቅርበዋል፡፡

ምናልባት በጋዜጣ በኩል በተደረገው የማጋለጥ ትግል ውስጥ ከፍተኛውን ቦታ ይዞ የነበረው ጉባዔው ባለቀ ማግስት የተሰጠው የሁለት ሰዓት ተኩል መግለጫና ኢንተርቪው ነበር፡፡የበርሊን ጋዜጠኞችና የብርታኒያ ራዲዮ ጣቢያ ወኪል በተገኙበት ትግላችንን የሚመለከቱትን ዋና ዋና አንቀፆች በማንሳት ውይይት ተደርጓል፡፡ተገኝተው ከነበሩት የጋዜጣ ወኪሎች መካከል፡በተለይ 'የበርሊነር ኢክስትራ ዲንስት' ወኪል፡የተሰጠውን መግለጫ በሙሉ በማተም አቋማችንንና ዓላማችንን በሰፊው አስታውቋል፡፡

በተጨማሪ በጉባዔው ሰሞን በጠቀሳሳው አምስት 'ኢንተርቪዎች ተሰጥተዋል፡፡ከነዚህ ውስጥ አንደኛው ኢንተርቪው የ



ተሰጠው ለበርሊን ከተማ ቴሌቪዥን ሲሆን የተቀሩት ደግሞ ለልዩ ልዩ የራዲዮ ጣቢያዎች የተሰጡ ኢንተርቪዎች ናቸው፡ ከመካከላቸው የብርታኒያን ና የካናዳን የራዲዮ ጣቢያዎች ለመጥቀስ ይቻላል፡፡

## የማጋለጥ ሰልፍ

ከፍ ብለን እንዳመለከትነው የማጋለጥ ትግላችንን በጋዜጣና በኢንተርቪው ብቻ አልተገታም፡፡በጉባዔው መደምደሚያ ሳይ በምዕራብ በርሊን ከተማ መሀከል አንድ ትልቅ የማጋለጫ ሰላማዊ ሰልፍ ተደርጎ ነበር፡፡በሰልፉ ሳይ ብዙ የምዕራብ በርሊን ወደሬት ተራማጅ ሰዎችና ድርጅቶች ተሳትፈዋል፡፡ ይህ ሰላማዊ ሰልፍ በጀርመን ቴሌቪዥንና ራዲዮ አማካይነት በጀርመን አገር በሙሉ ተሳልፎ ስለነበር ትግላችንና ዓላማችን በሰፊው ሊታወቅ ችሉአል፡፡ሰልፉ ባለፈበት ጉዳና ገራና ቀኝ ቆሞ ለነበረው ሕዝብ መግለጫ በማደል የኢትዮጵያን አስቃቂ ሁኔታ፡አድሃሪው መንግሥት በወደሬት ተራማጅ ኃይሎች ሳይ የሚያደርገውን ጭቆና ለማስረዳት ተችሉአል፡፡

ከዚህ በታች በሰልፉ መጠረሻ ሳይ የተደረገውን ንግግር በከፊል፡በሰልፉ ጊዜ የተበተነውን ጽሑፍና እንዲሁም በሰልፉ ጊዜ ከተዘመሩት ግጥሞች አንዳንዶችን ለአንባቢዎች እናቀርባለን፡፡

## በሰልፉ ሳይ የተደረገው ንግግር በከፊል — ትክክለኛ ትርጉም፡፡—

ዛሬ፡በዓለም ሳይ በሙሉ፡የተጨቆኑትና የተበዘበዙት ሕዝቦች ሳብሔራዊ ነፃነትና ለዕድገት የሚያደርጉትን ትግል እያጠነከሩ ሔደዋል፡፡ትግላቸውም ከጊዜ ወደጊዜ ብዙ ትላልቅ ድሎችን በመጐናጸፍ ሳይ ነው፡፡

በየትም አሕጉር እንመልከት፡-የተጨቆኑትና የተበዘበዙት

ሕዝቦች በመሳ፡ሳብሔራዊ ነፃነትና ለዕድገት በመታገል ላይ
ናቸው፡፡ጠላቶቻችን ኢምፔሪያሊዝምና የኢምፔሪያሊዝም አገል
ጋይና ጥቅም ተካፋይ የሆኑት ብሔራዊ ቡችሎች ናቸው፡፡እነ
ዚህ ሁለት ጠላቶቻችን እስካልጠፉ ድረስ ሰላም ይገኛል ማ
ለት ዘበት ነው፡፡የኛም ትግል ፀረፊውዳል እና ፀረኢምፔሪ
ያሊስት ነው፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ከዓለም አቀፉ የፀረኢምፔሪያ
ሊስት ትግል ተነጥሎ ሊታይ አይችልም፡፡የዛሬይቱን ኢትዮጵ
ያ ስንመለከት፡ፊውዳሊዝምንና ኢምፔሪያሊዝምን መነጣጠል አ
ንችልም፡፡ምንም እንኳ የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ፊውዳል
ቢሆን፡ከዘመናት ጀምሮ የገባው የባዕድ ካፒታልና የኢምፔሪ
ያሊስቶች የፖለቲካና የወታደር ተፅዕኖ አገሪቱን የእጅ አ
ዙር ግዛት እንድትሆን አድርጓታል፡፡

ኢምፔሪያሊዝም ወደአገራችን መግባት የጀመረው በያዝነ
ው መቶኛ ዓመት መጀመሪያ ላይ ነው፡፡ከዚያን ጊዜ ጀምሮ
አገራችን ቀስ በቀስ በእጅ አዙር የቅኝ አገዛዝ ቀንበር
ስር ወደቀች፡፡ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወዲህ የኢምፔሪ
ያሊዝም ተፅዕኖ በጣም እያየለ ሔዷል፡፡የዛሬው የኢትዮጵያ
መንግሥት በኢምፔሪያሊዝም — በተለይ በአሜሪካ ኢምፔሪያሊ
ዝም ቁጥጥር ስር ያለና የርሱም አገልጋይ የሆነ መንግሥት
ነው፡፡የኢምፔሪያሊስት አገሮች፡በተለይ አሜሪካ፡በአገራችን
ውስጥ የሚገኙትን ዋና ዋና የኢኮኖሚ፡የፖለቲካ፡የትምህርት፡
የፕሮፓጋንዳ ... ድረጅቶች በእጃቸው አግብተዋል፡፡

የአሜሪካ መንግሥት በኢትዮጵያ ውስጥ "ቃኘው ጣቢያ"
የሚባል ትልቅ የጦር ሰፈር አለው፡፡የጦር ሰፈሩ ዋና ተግ
ባር ዜና ማስተላለፍና ስለላ መሆኑ ይታወቃል፡፡የናቶ አገ
ሮችም የመጠረሸው ምሽጋችን እያሉ የሚሸልሉበት የጦር ጣቢ
ያ ነው፡፡ ... ኢምፔሪያሊዝም እንደዚህ በግልጽ ገብቶ በ
እናት አገራችን ላይ የጦር ሰፈሩን ዘርግቷል፡፡ይህ የጦር



ሰፈር ለነፃነትና ለሰው ልጅ መብት ለሚታገሉት ለአፍሪካ፡
ለአረብ፡ለፍልስጥኤም ሕዝቦችና በጠቅላላው ለዓለም ሕዝብ
ትልቅ አደጋ መሆኑ አይጠረጠርም፡፡መብቱን ለተነሳውና ለሚ
ታገለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ደግሞ የአይን ውስጥ ጉድፍ ነው።

በኢምፔሪያሊስት የተያዘችው ኢትዮጵያ ከቶ ልታድግ አ
ልቻለችም፡፡ኢኮኖሚዋ በሙሉ እየተበላሸ በመሔድ ላይ ነው፡
አንድ በልቶ አደር ቀኑን ሙሉ ላቡን ሲያንጠፈጥፍ ውሎ የ
ሚያገኘው ገቢ በቀን አንድ ተኩል የጀርመን ማርክ ነው፡፡
የሚበዘበዘው ገበሬ የሚበላው አጥቷል፡፡ሠርቶ አደሩ በሙሉ
ምሬቱን የሚገልጽበት መንገድ ሁሉ ተዘግቶበታል፡፡የሥራ ማ
ቆም መብት የለውም፡፡የሠራተኛ ማኅበራት መሪዎች በፊውዳሉ
መንግሥት የተመረጡ አድር ባዮች ናቸው፡፡የፊውዳሉ መንግሥ
ት አገልጋይ እንጂ የሠረቶ አደሩ መብት ጠበቂዎችና ተከራ
ካሪዎች አይደሉም፡፡በተጨማሪ የኢምፔሪያሊስት አገሮች ሠ
ራተኛ ድርጅቶች አማካሪ እና ረዳት እየተባሉ ስለገቡ የሠ
ራተኛው ድርጅት መሪዎች ከነአካቴው ወደ ፀረሠራተኛ ድርጅ
ት በመለወጥ ላይ ናቸው፡፡

እንደዚህ ያለው የመረረ ሁኔታ ሕዝባዊ እንቅስቃሴዎች
ን በያለበት አስነስቷል፡፡ገበሬዎች፡ሠራተኞች፡ተማሪዎች በ
ሙሉ፡አገር ወዳድ አርበኞች፡የወደፊት ተራማጅ ኃይሎች በየ
ቦታው ተነስተዋል፡፡በተለይ ባለፉት ዓመታት ውስጥ ከፍተኛ
ትግሎች ተደርገዋል፡፡

አድሃሪው የፊውዳል መንግሥት፡የዘረፋ ሥርዓቱን ለመጠ
በቅ፡ተቆጥቶ የተነሣውን ሕዝብ በፖሊስና በወታደር በመጠፍ
ጠፍ ላይ ነው፡፡በዚህም አረመኔ ተግባሩ የሚረዱት የአሜሪ
ካ፡የምዕራብ ጀርመንና የእሥራኤል መንግሥታት ናቸው፡፡

የአሜሪካ መንግሥት ለአድሃሪ አፍሪካ መንግሥታት ከሚ
ያደርገው የጦር ዕርዳታ ከአምስ በመቶው በላይ ለአድ

ሃሪው የኢትዮጵያ መንግሥት ይጨፋል፡፡በልዩ ልዩ የአጀ አ
ዞር አገዛዝ አገልግሎት ውስጥ የሚገኙት አሜሪካኖች ቁጥር
ከሥር ሺህ በላይ ደርሶአል፡፡የፖሊስን፡የስለላን፡የመገናኛ
ክፍልን... የሚመሩትና አገልጋዮቹን የሚያሰለጥኑት ፅዩና
ዊያን፡አሜሪካኖችና ረዳቶቻቸው ናቸው፡፡የምዕራብ ጀርመን
መንግሥትም ያድሃሪው የኢትዮጵያ መንግሥት የፖሊስ ሠራዊት
አሠልጣኝና መሣሪያ አቀባይ ሆኗል፡፡የምዕራብ ጀርመን መን
ግሥት በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር የጀርመን ማርክ የሚያወጡ
የጋዝ ጢስ ፡ጠብመንጃ፡ሽጉጥ፡ጥይት...ሊሰጥ ተስማምቷል፡፡

የዘረው ሰላማዊ ሰልፋችን በተለይ ጀርመን አገር በመ
ሆኑ ምክንያት ልናስታውሰው የምንፈልገው አንድ ነገር አለ፥
ይኸውም በጀርመን አገር የሚገኙ የወደፊት ተራማጅ ኃይሎች
በሚያደርጉት የፀረኢምፔሪያሊስት ትግል ውስጥ የምዕራብ ጀ
ርመን መንግሥት ሳድሃሪው የኢትዮጵያ መንግሥት የሚሰጠውን
የጦር ዕርዳታ በግልጽ እንዲቃወሙና የትግላቸው ፕሮግራም
እንዲያደርጉት ነው፡፡በበኩላችን የኛ ትግል አ
ያደገ ሲሔድኢምፔሪያሊስቶች የሚሰጡትን የጦር መሣሪያ ካድ
ሃሪው መንግሥት ወታደሮችና የጦር ሰፈሮች እየነጠቅን የሕ
ዝብ መከላከያ እንደምናደርጋቸው አንጠራጠርም፡፡

በተማሪዎች ትግል የበረገገው አድሃሪ መንግሥት እንደ
አውሮፓ አቆጣጠር ታህሣሥ 28፡1969 የአዲስ አበባ ዩኒ
ቨርሲቲ ተማሪዎች መሪ የነበረውን ጥላሁን ግዛውን በአንድ
በደንብ በተደራጀ የነፍሰ—ገዳይ ቡድን አስገደለው፡፡ይህ
በሆነ በማግስቱ ከሃያ አምስት ሺህ በላይ ተማሪዎችና የከ
ተማ ነዋሪዎች በዩኒቨርሲቲው ቅጥር ግቢ ውስጥ ተገኝተው
ነበር፡፡የተሰበሰበው ሕዝብ የሙቀችን ጓደኛችንን አስከሬን
ወደ ቤተ ሰቦቹ ለመውሰድ በሚዘጋጅበት ጊዜ ቍጥራቸው ከፍ
ያለ ወታደሮች ወደዩኒቨርሲቲው ቅጥር ግቢ ገብተው የተሰበ
ሰበውን ሀዘንተኛ መበታተን ጀመሩ፡፡ወዲያውኑ የጥይትእሩም
ታ ከፍተው ከአምበ የሚበልጡ ወጣቶች ሲገደሉ ከመቶ የሚበ



ልጡትን አቁሰለዋል፡፡ብዙዎች ተማሪዎች ወደ እስር ቤት ተ
ወስደዋል፡፡በተለይ የምንጠራው ያለአንዳች ፍርድ በእስር
ቤት የሚሰቃየውን ቀለልኝ መኰንን ነው፡፡

ይህንን ሰላማዊ ሰልፍ ያደረግነው ለሙቀች ጓድ ጥላሁ
ንና በፋሽስታዊ ጭካኔ ለተረሸኑት እህቶቻችንና ወንድሞቻች
ን ነው፡፡የነሱ ሕይወት ያለፈው ፊውዳሊዝምንና ኢምፔሪያሊ
ዝምን በመቃጋት ላይ ባሉ ነው፡፡

በዚህ ሰላማዊ ሰልፍ ልንገልጽ የምንፈልገው ፊውዳሊዝ
ምንና ኢምፔሪያሊዝምን ለመቃጋት ያለንን የማያወላውልና የ
ማይበገር ቆራጥ አቋም ነው፡፡

ይህ ሰላማዊ ሰልፍ ከዓለም የፀረኢምፔሪያሊስት ኃይሎ
ች ጋር ያለንን የትግል አንድነት የሚገልጽና የሚያጠነክር
ነው፡፡

— ፊውዳሊዝም ይውደም፡፡

— ኢምፔሪያሊዝም ይውደም፡፡

— የተጠቁት ሕዝቦችና የወደፊት ተራማጅ ኃ
ይሎች የሚያደርጉት ፀረኢምፔሪያሊስት ትግ
ል ለዘለዓለም ይኑር፡፡

— ዓለም አቀፉ ፀረኢምፔሪያሊስት ትግል ለዘ
ለዓለም ይኑር፡፡

— አንድ ነን፡እናሸንፋለን፡እንታገላለን፡፡

---

## በሰልፉ ባይ የተበተነው ጽሑፍ — ትክክለኛ ትርጉም

## ፊውዳሊዝምና ኢምፔሪያሊዝም የኢትዮጵያን ሕዝብ ጠቁ ነው ይዘውታል::

1 ከሁለት መቶ የማይበልጡ ባለመሬቶች ከሚታረሰው መሬት ውስጥ ሰማኒያ በመቶ የሚሆነውን ይዘውታል::

2 ከሕዝቡ 90 በመቶው በእርሻ ተግባር ላይ ቢገኝ ከነዚሁ አራሾች ውስጥ 75 በመቶ ያህሉ መሬት የሌላቸው ጪሰኞች ናቸው::

3 ጪሰኞች ከምርታቸው ውስጥ እስከ 75 በመቶውን ድረስ ለፊውዳሉ በለመረት እንዲያስረክቡ የኢትዮጵያ ሕግ ይፈቅዳል::

4 ኢትዮጵያ ከድሆችና ምንም እድገት ከማያሳዩት አገሮች ውስጥ አንዷ ናት::ዓመታዊ የነፍስ ወከፍ ገቢ ሁለት መቶ የጀርመን ማርክ እንኳ አይደርስም::

5 አንድ ሠርቶ አደር የሚያገኘው ዕለታዊ የጉልበት ዋጋ አንድ ተኩል የጀርመን ማርክ ብቻ ነው::

6 ንግዱና እንዱስትሪዎች በመላ በባዕድ ባለገንዘቦች የተያዙ ናቸው::

7 በኃይለሥላሴ የሚመራው የኢትዮጵያ ፊውዳል መንግሥት የኢምፔሪያሊዝም — በተለይም የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም — ፍጹም አገልጋይ ሆኗል::

## በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ውስጥ መሃይምነት:በሽታና ድህነት ከልክ በላይ ተሰፋፍተው ይገኛሉ::

1 ከሕዝቡ 95 በመቶ የሚሆነው ማንበብና መጻፍ አይችልም::



2 ዕድሚያቸው ለትምህርት ከደረሰ ወጣቶች መካከል የትምህርት ዕድል የሚያገኙት አምስት በመቶ እንኳን አይሆኑም::

3 ከሚወለዱት ሕጻናት 60 በመቶ የሚሆኑት ሁለት ዓመት ባይሆናቸው ይሞታሉ::

4 በአገሪቱ የሚገኙት ሃኪሞች ቁጥር ለጠቅላላው ሕዝብ ሲከፈል ለመቶ ሺህ ሕዝብ አንድ ሃኪም ይደርሰዋል::

5 ቢያንስ በዓመት ውስጥ ከአንድ እስከ ሦስት ጠቅላይ ግዛት በረሃብ ይገረፋል::በችጋር የሚያልቀው ሕዝብ ቁጥር በብዙ ሺህ ይገመታል::

## የኢትዮጵያ ሕዝብ ፊውዳሊዝምንና ኢምፔሪያሊዝምን ይቃጋል::

1 በኤርትራ:በባሌ:በጎጃም:በኦጋዴንና በሌሎች ጠቅላይ ግዛቶች ውስጥ የገበሬ ትግሎች ተፋፍመዋል::

2 ሠርቶ አደሩ ሕዝብና ተማሪዎች ሥራ በማቆምና ሰላማዊ ሰልፍ በማድረግ ለመብታቸው ይታገላሉ::

## ይህን ሰላማዊ ሰልፍ የምናደርገው ለምንድነው?

1 አድሃሪው የኢትዮጵያ መንግሥት በገበሬዎች:በሠራተኞችና በተማሪዎች:በአገር—ወዳድ አርበኞችና በወደፊት ተራማጅ ኃይሎች ላይ የሚፈጽመውን ዐመጽ:ጭካኔና ብዝበዛ ለመቃወም::

2 ከኢትዮጵያ ገበሬዎች:ሠራተኞችና ተማሪዎች ጋር ያለንን የትግል አንድነት ለመግለጽና ለማጠንከር::

3 እአአ በ28 12 69 የተማሪዎች መሪ የነበረው ጓዱ ጥላሁን ግዛው እስካሁን ባልተገለፀ አኳኋን ተገደለ፡፡በማግስቱ ለጥላሁን ሀዘን በተሰበሰቡት ተማሪዎችና የከተማ ነዋሪዎች ላይ፡ባድሃሪው መንግሥት ትእዛዝ፡ጥይት ተኩስ ተከፍቶ ከ50 በላይ የሚሆኑ እህቶቻችንና ወንድሞቻችን ሕይወታቸውን አጡ የዚያኑ ለት በተደረገው አፈሳ ቍጥራቸው ያልታወቀ ጓዶች በእሥር ቤት ተወርውረው እስካሁን እዚያው ይማቅቃሉ፡፡

ይህን ሰላማዊ ሰልፍ የምናደርገው ይህን ሁሉ ግፍና ስቃይ ለማሳወቅና ለማጋለጥ ነው፡፡

---

<u>በሰልፉ ላይ የተዘመሩ ግጥሞች</u> — በከፊል

<u>ምን አለ</u>?

1 ምን አለ? ተሜ ምን አለ?
መሬት ላራሹ፡መሬት ላራሹ
ይሁነው አለ፡፡

2 ምን አለ? ሕዝቡ ምን አለ?
መሬቱ ለኔ፡መሬቱ ለኔ
ይገባል አለ፡፡

3 ምን አለ? ኃይሌ ምን አለ?
ኢትዮጵያን በብር፡ኢትዮጵያን በብር
ልሸጣት አለ፡፡

4 ምን አለ?ያንኪስ ምን አለ?
ኢትዮጵያን በብር፡ኢትዮጵያን በብር
ልውሰዳት አለ፡፡



5 ምን አለ? ተሜስ ምን አለ?
አገሬን ለሰው፡አገሬን ለሰው
አልሰጥም አለ፡፡

6 ምን አለ? ተሜ ምን አለ?
ድሉ የሕዝቡ፡ድሉ የሕዝቡ
ይሆናል አለ፡፡

<u>በለው፡በለው፤</u>

በለው፡በለው፤አትሰሙም ወይ? አትሰሙም ወይ?
የፈሰሰው ደም ያንተ አይደለም ወይ?

በለው፡በለው፤አትሰሙም ወይ? አትሰሙም ወይ?
ጨቋኝ ሲገዛህ ዝም ትላለህ ወይ?

በለው፡በለው፤አትሰሙም ወይ?አትሰሙም ወይ?
የሕዝብ ወታደር አይደለህም ወይ?

በለው፡በለው፤አትሰሙም ወይ?አትሰሙም ወይ?
የላብ አደር ልጅ አይደለህም ወይ?

---

በጠቅላላ እነጋገር አሥረኛው ጉባዔ አድሃሪውን መንግሥት ለማጋለጥ የወሰዳቸው የፕሮፓጋንዳ ትግሎች አጥጋቢ ነበሩ ለማለት ይቻላል፡፡ቢሆንም ለወደፊቱ የበለጠ ጥረት ማድረግ እንዳለብን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡የማጋለጥ ትግላችን ድል ሊጎናፀፍ የሚችለው አቋማችንን ሊያስታውቅ በሚችለው ዕድል ሁሉ በመጠቀም፡በማንኛውም ሰዓትና ቦታ አድሃሪውን የኢትዮጵያ መንግሥት ያጋለጥን እንደሆነ ነው፡፡ትግላችን እንቀጥል፡እናሸንፋለን፡፡

## የመሰነባበቻ ምሽት

ዕሁድ 16 7 70 — አአአ — የመለያያችንን ቀን ምክንያት በማድረግ በበርሊን ከተማ የሚማሩ ጓደኞችን "የመሰነባበቻ ምሽት" ገብዝ አደረጉልን::ሰሞኑን ጊዜ ከማጠሩ የተነሣ የሰሚናር አርዕስታችንን ነክ ባልሆኑ ነገሮች ሳይ በአንድነት የመጨዋወት፣የመወያየት... ዕድላችን የተወሰነ ነበር::ይህ ምሽት በሥራ ውጭ በአንድነት የመሰብሰብን ዕድል ሰለሰጠን ጓደኞች ሁሉ እየተነሡ እንደየችሎታቸው የአበቶችን ጠቃሚ ተረቶች በማውጋት፣በሽለላ፣በመዝሙር፣በዘፈን የአገርን ጉዳይ ከልዩ ልዩ አንጻር ሲመለከቱና ሲያቀርቡ አመሹ::የዚያንለት ምንም እንኳ በሰውነታችን በርሊን ብንሆን በመንፈስ ኢትዮጵያ እንደነበርን ለማንም ተመልካች ግልጽ ሆኖ ይታይ ነበር::

ሽለላው እንደመስታወት በመሆን የኢትዮጵያን ቁልቁለትና ሸንተረር፣ቆላና ወንዝ ከፊትህ ድቅን አርጉ ያሳዩሀል::

ገጥሞች የሐገራችንን ሕዝብ ጀብዱ እያስታወሱ ያሳህበትን ያስረሱሀል::

መዝሙሮች "ከዱር" የተወረሱ ወኔን እየቀሰቀሱ "በለው..በለው.. በለው" ያስኙሀል::

በዚያን ለት በሁላችን ላይ ሰፍኖ የነበረውን ስሜት በሙሉ ለመግለጽ አይቻልም::እንዲያው በደፈናው ከተሰሙት መዝሙርና ገጥሞች አንዳንዶችን ለአንባቢዎች ማቅረብ ይሻላል::ሊያስከትሉ የሚችሉትን ስሜት እነሱው ይፍረዱ::



## በምሽቱ ላይ ከተነበቡት መዝሙሮች አንዳንዶቹ

### 1 በሶቪየት ህብረት የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር የቀረበ

### ኩኩሉ አለ ዶሮ

አዝማች
ገፍ ለሚሠራብህ ለፋሽስት ዓላማ
ዓይንህ አተኩሮ ጆሮህ አየስማ
ኋህ ቀደደ ነጋ ቀን ሲመጣ ዞሮ
ያገር ልጅ ተነሣ ኩኩሉ አለ ዶሮ::

ጓደኛየን ጠራሁ ፀሐይ ቢያቃጥለኝ
ምናልባት ብልሀት እንዳለው ቢነግረኝ
እሱም አጫወተኝ ሃዘኑን የምር
ሰብረው እንዳስቀሩት ጥሳውን የምር::

አዝማች

አጥሩ ተደፈረ አትክልቶች ወደሙ
አሩምታ አዘነበ ወንድም በወንድሙ
የደም ጎርፍ ቀለለ በወንድምህ ቤት
በወረደው ዝናብ ደፍ አይሉበት::

አዝማች

በመኀቢያችን ዙሪያ ወድቀው ለቀሩት
ለሕዝብ ለነፃነት ሠርተው ሳለፉት
እንሣሳቸው እንጂ አጁህን ሳለም
ነፃነት እንዲያበቅል ያፈሰሱት ደም::

አዝማች

## 2 በፈረንሣይ የኢት ተማ ማ የተቀናበረ

### ግፍ ይደመሰሳል

ፊትህ ሳይከፈት ትጥቅህ ሳይፈታ
እኔ ልውደቅ ያልከው አገሬ ተነስታ
አደራህ ደርሶናል ምስሏህ ገብቶናል
አገሬን እንዳልከው አገሬን ብለናል

በትግልህ አርዓያ ሕዝቦችን ይነሳል
ጨለማ ይጠፋል ግፍ ይደመሰሳል
ጨለማ ይጠፋል ግፍ ይደመሰሳል

ወይም ነፃነቴን ወይም ሞቴን ብለህ
ደህና ሁኑ ብለህ ላትመለስ ወጥተህ
እንኳንስ ቀባሪ መቃብር ሳይኖርህ
ለክብር ለነፃነት ወድቀሃል ላገርህ

በትግልህ አርዓያ ...

በላብ አደር ቁጣ በገበረው አመጽ
በትግልህ አርዓያ ነፃነት ሲታነጽ
ብርሃን ያሸንፋል ሕዝቦችን ይነሳል
ጨለማ ይጠፋል ግፍ ይደመሰሳል።

---

## 3 በሶቪየት ኅብረት የኢትዮጵያ ተማ ማ የቀረበ

### ደህና ሁኚ

1 ጧት በማለዳ ከቤት ስወጣ
በይ ደህና ሁኚ፡ደህና ሁኚ፡ደህና ሁኚ፡ሁኚ፡ሁኚ



ጧት በማለዳ፡ከቤት ስወጣ
ሕዝቡ ሲረገጥ አየሁኝ።

2 ጀግናው አርበኛ፡የግፍ መጋኛ
በይ ደህና ሁኚ....
ጀግናው አርበኛ የግፍ መጋኛ
ይኸው መጣሁ በል ምረኛ።

3 አውጭ ጠብመንጃ፡ወልውይ ሳንጃ
በይ ደህና ሁኚ....
አውጭ ጠብመንጃ፡ወልውይ ሳንጃ
በቃኝ መሮ እንደጥጃ።

4 የሕዝብ ጠቋኝ፡የጠላት ታማኝ
በይ ደህና ሁኚ....
የሕዝብ ጠቋኝ፡የጠላት ታማኝ
እንግዲህ ይበል ወዮልኝ።

5 ያገር አድሃሪ፡ሕዝብ አጭበርባሪ
በይ ደህና ሁኚ
ያገር አድሃሪ፡ሕዝብ አጭበርባሪ
ቀንክን ቁጠር ከነመሪህ።

6 የላብ አደሩ ነኝ፡ወታደሩ
በይ ደህና ሁኚ
የላብ አደሩ ነኝ፡ወታደሩ
አቅ እስኪገባ አገሩ።

7 ካልተመለስኩኝ አ ታልቅሽ
በይ ደህና ሁኚ
ካልተመለስኩኝ አ ታልቅሽ
ታጠቂና አንቺው ተኪኝ።

## ከግጥሞች አንዳንዶች

### 1 በሰሜን አሜሪካ ጓደኞቻችን የቀረበ

### ለነፃነት ታገል

ገፉ የመረረው ከንቅልፉ የነቃ
ትዕግሥቱን ጨርሷል ከእንግዲህ በቃ።
ለመቶኛት እንደሁ ብዙ ዘመን ተኛን
ቀስቃሽ እንጠብቅ አውቀን ካልተነሳን።
የነፃነት ኑሮ ትርጉሙ ሳይገባን
እንደ እንስሳና እንደ ዕቃ ተቆጥረን
በባላባቶች ኃይል ታፍነን ተይዘን።
መብትን ለመጠየቅ ነቃ እንዳንል
የፋሽስቶች ቀንበር ከላይ ይጫናል።
ከዚህም ቀንበር ውስጥ ለመውጣት ፈልቅቆ
አሁን ነው መታገል ቀበቶን አጥብቆ።
አድሃሪው መንግሥት ሲጠቃን የኖረ
በቀላሉ አይወድቅም እሳት ካልተጫረ።
ፋኖ ተሰማራ ገባ ወደጫካ
ጠላትከን ደምስስህ በድል እስከትረካ።
የግል ጥቅምን ስሜትን አውድቆ
ለትግሉ መሥራት ነው ቶሎ ተሸቀዳድሞ።
ብልጭልጩን ኑሮ ምቾቱን በመርሳት
ቆርጦ መዋጋት ነው ጠመንጃ በማንሳት።
ከሕዝቡ ጋር አብሮ ሕዝቡን ያልመሰለ
አጉል አጭበርባሪ የትም የቀለለ
የጠላት መሣሪያ ሕዝቡን የበደለ
ለመኖር አይችልም ሁሌ እያታለለ።
ለጀመርከው ትግል እንዳይመጣብህ ጠንቅ
ቶሎ ተመራመርህ ጠላትህን ዕወቅ።
የትግሉ እንቅፋት ሆኖ ካገኘኸው
ጠላትህ ነውና ሳይቀድምህ ቅደመው።



የምትሠራ እንደሆንክ በሙሉ አንደበት
እስከ መጨረሻው ታገል ለነፃነት።
ድሃው የሚበላው የሚለብሰው አጥቶ
ሀብታም ሲንቀባረር በጥጋብ ደንፍቶ
እንዲህ ያለ ኑሮ ማን ይመኛል ከቶ
ሊያጠፋው ይገባል ሁሉም ተረዳድቶ።
ሰው ሆኖ ተፈጥሮ ሁሉም ባንድ አምሳል
አንደኛው ሳንደኛው እንዴት ይገዛል?
የባላባት መንግሥት እንዲኖር በደንብ
አፍኖ ይገዛል የጌታው መደብ።
የድሃውን ክፍል በዝብዞበዝብዞ
በራብ ይገላቀል አንጀቱን መርዞ።
ግፉን ከመገንዘብ በተመልካችነት
ነገ ዛሬ ሳይሉ መሆን ነው መሥዋዕት
በትግል ብቻ ነው የሚገኘ ነፃነት።
ማውራት አያረካም ሥራ ላይ እንገኝ
የትም እንበተን እንሁን መናኝ።
በቃላት ጦርነት በስድብ ውርጅብኝ
ጠላት እኮ አይወድቅም እናስብ እንደሞኝ።
ይልቁስ ወሬውን ትችቱን አቁመን
መሣሪያ እንገተን ጥይቱን አቅመን
የጨቋኞቹን ኃይል መደምሰስ አለብን።
መሥዋዕትነቱን በዚህ ያሳሰየ
የሕዝቡ ጠላት ነው አቋሙን የለየ።
አለሁልህ ማለት በአፍ መደለል
ያታሳይ ቋንቋ ነው ሁሉም ያውቀዋል።
ጊዜው ሳያመልጠን የውጊያው አዝመራ
ጠላትን እንገጥም በተራ በተራ
መጀመሪያ እናጥቃ ዋናውን ጠላት
የገሩሬውን ኃይል በሰው የሚጫወት
ወዝአደሩን ድሃ ወንዱን ሆነ ሴት
በችጋር አድቅቆ ሳይፈጀው በሞት።

በያንዳንዱ ሰዓት በየደቂቃው
ስንት ሺህ ሕዝብ ነው በረብ የሚያልቀው?
ድሃው ገበሬ ሕዝብ ኑሮን ሲተናነቅ
የጨቋኞች ቀንበር ክብደት ሲጠነቅ
አብሮ መታገል ነው ይህን ክፉ ጠንቅ፤
በከፈለው ቀረጥ መማርከን ረስተህ
ውለታውን ባትከፍል ወዴት ትሔዳለህ?
የትግሉ መሥራች ቀናው ግንባር_ቀደም
ወጣቱ ዜጋ ነው በለትኩሱ ደም፤

ገበር ተሰማራ፡ጓዴ ተሰማራ
እንደ ሆቺ ሚን፡እንደ ቼ ጉቬራ
ድልን አግኝተህ እስከትኮራ
ጠላትከን አብር ጋራ ለጋራ::

---

## 2 በበርሊን የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር የቀረበ

### እናት ኢትዮጵያ

እናት ኢትዮጵያ የኛ ማር ወለላ
ዓለም ስትራመድ ቀረሽ ወደኋላ::

የጥንት ልጆችሽ ነበሩ ጀግኖች
በገንዘብ ሳይሸጡሽ
ለባዕድ ነጮች

ጭብጥ የማይሞሉ ገዥ ጠላቶችሽ
ባዕድ አስገብተው አስበዘበዙሽ

አረመኔው መሪ ከነበሮቹ ጊዜው አልቆበታል
አንድ ሐሙስ ቀርቶታል
ገብረአበሮቹ ተጠንቀውለታል

የሠሩትም ወንጀል አስከሬቸው
እህል አያስበላ አያስተኛቸው::

ኢትዮጵያችንን ጠላት እንዳይበላት
ከመቼውም ይልቅ
ያሻናል ኅብረትና አንድነት::

መሣሪያ በመሆን ለጥንቱ ተፈሪ
አንድ ሐሙስ ለቀረው ለአሁኑ መሪ
ለገብረ አበሮቹ ለሱ አጫፋሪ
ማውደም ይገባናል ይህን ሁሉ አጭበርባሪ::

ዴሞክራሲ የለም በሃገራችን
መናገር አንችልም ሐሳባችንን
እስከ መቼ ድረስ እንታፈናለን
እንነሣ አንድ ላይ ነፃ እንወጣለን::

በደም የቆሸሸ እጅ አይጠራም በውሃ
ጊዜው ፈቅዶልሀል ተነሣ ገበሬ ድሃ

ጭብጥ የማይሞሉ ጥቂት ነቀዞች
ሕዝባችንን ፈጁት በአዳኝ ጓዶች::

ለተበዘበዘው ለውዱ ሕዝባችን
ለተዘረፈችው ለናት አገራችን
ነፃ እንዲወጣ
በሙሉ ሕዝባችን
መታገል አለብን
በአንድ ልባችን::

ዓለምን ስትቀድሚ ማራቶን ሮጠሽ
ከዘመኑ እርምጃ ምንቀ ተነጠልሽ::

የሰለጠነው ሕዝብ ሲወጣ ሰማይ
ኢትዮጵያ ቀረች እጭቃ ላይ::

ስምህን ሳላነሳው አላልፍም በውነቱ
ሳላመሰግንህም አላልፍም በውነቱ
ቆራጡ ወንድሜ ጄኔራል መንግሥቱ::

ወንድምህም ሞተ በቆራጥነቱ
ኢትዮጵያ እናቱን ነፃ ለማውጣት::

አጂግ ትክ የሚሉኝ ሦስት ጀግኖች ነበሩ
እንዳልረሳቸው ነው እንደያው ለነገሩ
ወርቅነህ ባዩና ያ ነጋሽ ዱንበሩ::

መስፍን በለሸና አንዳርጌ መሣይ
ደቀ መዝሙሮች የነቡ አውደልዳይ
እኛ ነን እያሉ በሰዉ በሳይ
ሕዝቡን አሰቃዩት
ዕለት በዕለት
ሕዝቡን አስጨነቁት ዕለት በዕለት
እየበዘበዙ መዶረሸ አሳጡት
እንዴ ይመለሳል ይህ ሁሉ ቅጭት::

መብትህ ተገፏል እስከናባቴው
እርስትህ ተወስዷል እስከናካቴው
የምትጠብቀው እነማንን ነው?

እጣማችን ቢያጣ እንቧ ይሳል በረ
ተነሥቷል በላቸው የኢትዮጵያ ገበሬ::

የፈለግነውን እዚህ ብንናገር
ሀሰት ነው ለማለት ማንም ሰው አይደፍር፤
ምስክራችን አገራችን ነች
እንደተፈጠረች እንዲሁ ያለች
ዓለም ስትለወጥ እሷ እዚያው ነች
ገገምተኛ ሆና የቀረቀዘች፤
ኢትዮጵያ በጄ ናት ቃሏን ያከበረች
እንደተፈጠረች
ቅጭ በላ የቀረች::